# ባለህበት የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደምትጀምር

J.C. Choate

World Evangelism Publications

© Copyright, World Evangelism Publications

This printing - 1,000 copies - 2024 – **Amharic**

**InDesign Layout**: Shane Fisher

**Translated by**: Belay Kebede Areri
**WhatsApp number**: 0913611000.
**Email**: ddcoc321@yahoo.co.uk

**Websites**:
www.worldevangelismlibrary.org
www.gospelgazette.com
www.worldevangelism.org
www.worldevangelismmedia.com

**Printed by**:
World Evangelism Publications
Winona, MS 38967

## ማውጫ

1. የእግዚአብሄር ዕቅድ ለሰው ልጆች................................ 4
2. መጽሐፍ ቅዱስ ያስፈልገሃል......................................7
3. መዳን ያስፈልገሃል............................................ 10
4. ወንጌልን እንዴት እንደሚታዘዙ.................................. 13
5. የጌታ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚገለጽ...................... 17
6. አንተ ለጌታ አስፈላጊ ነህ..................................... 20
7. ባለህበት ቤተክርስቲያን ለምን ያስፈልጋል .......................23
8. የጌታ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚጀመር...................... 26
9. እንዴት እንደሚጠመቁ........................................ 29
10. እንዴት እንደሚያመልኩ...................................... 32
11. የጌታ እራት አገልግሎት...................................... 35
12. እንዴት እንደሚጸልዩ........................................ 38
13. እንዴት እንደሚዘመር.........................................41
14. ስጦታ እንዴት እንደሚሰጥ.....................................44
15. የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ.................................... 47
16. እንዴት እንደሚሰበክ........................................ 50
17. እንዴት እንደሚደራጅ........................................ 52
18. መሰብሰቢያ ቦታ............................................... 55
19. የሴቶች ሚና ................................................... 58
20. ወንጌላዊያንን እንዴት እንደሚደግፉ............................61
21. እርዳታ ለሚስፈልጋቸው እንዴት እንደሚደግፉ...................64
22. እንዴት አብሮ እንዴሚሰሩ...................................... 67
23. እንዴት ይቅርታ እንደሚባባሉ................................. 70
24. ንጹህ አስተምህሮ እንዴት እንደሚኖር..........................73
25. የክርስትና ህይወት ስለመኖር....................................76
26. ችግርን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል...........................79

## ትምህርት 1

## የእግዚአብሄር ዕቅድ ለሰው ልጆች

ከዚህ ትምህርት ጀምሮ እርስዎ ባሉበት መንደር የክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንዴት መጀመር እንዳለብን መሪ ሃሳብ እንነጋገራለን። የጌታን ቤተክርስቲያን አስፈላጊነት፣ ባለንበት ቦታ የመኖሯ አስፈላጊነት እና ይህን ሁሉ እንዴት ማድረግ እንደሚቻል እንድንገነዘብ በሚረዱን መፅሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረን ነገር ላይ በመመስረት ስለሁሉም እንነጋገራለን።

በዚህ አጋጣሚ ጥናታችን እግዚአብሄር ለሰው ካለው እቅድ ጋር የተያያዘ ይሆናል። የእግዚአብሄርን ህልውና ማወቅ ብቻ ሣይሆን ፍጥረቶቹ እንደ ሆንን ብቻም ሳይሆን ለሰውም ሁሉን አቀፍ እቅድ እንዳለው ማወቅ አለብን።

እግዚአብሄር ሁልጊዜም ነበር፣ አሁንም አለ እናም ለዘላለም ይኖራል። እርሱ ሥጋዊ ወይም ምድራዊ አይደለም፣ ነገር ግን መንፈስ ነው፣ (ዮሃንስ 4፡24)። እርሱ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም በእናንተም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት ነው። (ኤፌሶን 4፡6)፣ ሰማይንና ምድርን መፍጠር ብቻ ሳይሆን ወንድና ሴትን በራሱ አምሣል በመፍጠር ፍጥረታትን አቀዳጅቷል። (ዘፍጥረት 1፡26፣ 27፣ 2፡7)

ሰው በድንገት ወደዚህ ዓለም አልመጣም፣ ያለ ዓላማ እና አቅጣጫ በዚህ ምድር ላይ አልተቀመጠም። ህይወቱ የዚህን ዓለም ተድላ ከመፈለግ ይልቅ በሚያምር መንገድ መዋል ነበረበት፣ ከዚህ ይልቅ ፈጣሪውን ለማክበር ነው። በጥንት ዘመን የነበረው መዝሙረኛው ዳዊት እንዲህ ብሏል። “እግዚአብሄር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ እወቁ ፣ እርሱ ሰራን እኛም አይደለንም፣ እኛስ ህዝቡ የማሰማሪያውም በጎች ነን፣ ወደ ደጆቹ በመገዛት፣ ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ፣ አመስግኑት፣ ስሙንም ባርኩ” ብሏል (መዝሙር 100፡3፣4)

ሰው ከመፈጠሩ በፊትም ቢሆን እግዚአብሄር ለእርሱ እቅድ ነበረው። አስቀድሞ ወስኗል፣ አስቀድሞ አስቧል፣ አስቀድሞ በአዕምሮው አቅዷል ወይም ፃድቃን እንደሚድኑ ዓመፀኞች እንደሚጠፉ ወሰነ፣ ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ሲናገር “እንግዲህ በጌታ እስር የሆንኩ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችዋለሁ፣ በትህትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሱ፣ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ። በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ። አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ” ይላል (ኤፌሶን 4፡1=6) እግዚአብሄር ፃድቃን እንዲድኑ ነገር ግን ክፉዎች እንዲጠፉ ወሰነ። ለእያንዳንዱ ሰው የትኛው ቡድን አባል እንደሚሆን የመወሰን ነፃነት ሰጥቶአል። አንዱ ከፃድቃን ጋር ለመቆጠር፣ በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም ለመዳን ከወሰነ በእርግጥ

ለመዳን ራሱን በመታዘዝ ለጌታ ማስገዛት እና ወደ ቤተክርስቲያን መጨመር አለበት (ማርቆስ 16፡15=16፣ ሐዋሪያት ሥራ 2፡47)። ይህን አለማድረግ ማለት ከሌላው ከሚጠፉ ቡድን ጋር መቆጠርን መርጧል ማለት ነው፣

የሰው ልጅ ሲወለድ ንጹህ ሆኖ ያለ ኃጥያት ነው የሚወለደው፣ ክፉ እና በጎውን መለየት እስከሚችል ድረስ ይህ ሰው ንጹህ እና ያለ ኃጥያት ነበር፣ ክፉና ደጉን መለየት ማወቅ ከጀመረ በኃላ የሚሰራውን የሚያውቅ ሲሆን ኃትያት መስራት ይጀምራል። ኃጥያት የእግዚአብሄርን ህግ መተላለፍ ነው፣ ኃጥያት አመፅ ነው፣ ስለዚህ ለኃትያቱ ሁሉ ተጠያቂ ኃላፊነት ይወስዳል፣ ይጠየቅበታል፣ ኃትያት አመፅ ነው፣ ዮሐንስ ሲናገር "ኃጥያትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል፣ ኃጥያትም ዓመፅ ነው" ይላል (1ኛ ዮሐንስ 3፡4) ጳውሎስ ስለነዚህ ሰዎች ሲናገር እንዲህ ይላል "ሁሉ ኃጥያትን ሠርተዋልና ፣ የእግዚአብሄርም ክብር ጎድሎአቸዋል" ይላል (ሮሜ 3፡23)

እግዚአብሄር ሰዎችን በኃጥያታቸው አየ፣ ኃጥያት ደግሞ ሞትን ያመጣል ፣ ስለዚህም ጳውሎስ እንዲህ ይላል "የኃጥያት ደመወዝ ሞት ነውና፣ የእግዚአብሄር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ህይወት ነው" ይላል፣ (ሮሜ 6፡23)፣ ከዚህም የተነሣ ከዚህ ኃጥያት ይድኑ ዘንድ እግዚአብሄር ልጁን ወደ ዓለም ላከ፣ ይህን "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሄር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሄር ወደ ዓለም አልላከውምና በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም" (ዮሐንስ 3፡16_17)

ሰው በራሱ ፅድቅ ሊድን አይችልም፣ በእንስሳት መስዋዕትም ሊድን አይችልም፣ "የኮርማዎችና የፊየሎች ደም ኃጥያትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና " (ዕብራዊያን 10፡4) ለዚህም ነው እግዚአብሄር ልጁን ወደ ምድር ልኮ በምድር ተመላልሶ ለሰው ልጆች ሁሉ ኃጥያት እንዲሞት ያደረገው፣ "ነገር ግን ገና ኃጥያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና፣ እግዚአብሄር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል፣ ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን"(ሮሜ 5፡8_9) ጴጥሮስም ክርስቶስ በሥጋው ኃጥያታችንን ስለ መሸከሙ እንዲህ ይላል "ለኃጥያት ሞተን ለፅድቅ እንድንኖር፣ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጥያታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ" ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 2፡24)። ክርስቶስም እንዲህ ብሏል "ስለ ብዙዎች ለኃጥያት ይቅርታ የሚፈሰው የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" ብሏል (ማቴዎስ 26፡28)።

እንዴት አድርጎ ነው የአንድ ሰው መሞትና የደሙ መፍሰስ ከኃጥያታችን ወይም ከጥፋታችን ሊያድነን የሚችለው? እዚህ ጋ ልናውቀው የሚገባ ከኃጥያታችን የሚያድነን የዔትኛውም ሰው ሞት ወይም የዔትኛውም ሰው ደም መፍሰስ አለመሆኑን ማወቅ አለብን፣ ነገር ግን የእግዚአብሄር ልጅ የሆነው፣

ምንም ኃጥያት የሌለበት ብቸኛ የክርስቶስ ኢየሱስ ሞት እና ደም ብቻ ነው ከኃጥያታችን ሊያድነን የሚችለው የቻለውም። እራሱን አሳልፎ ስለኃጥያቻችን የሞተው ደሙን ያፈሰሰው እሱ ብቻ ነው፣ ያ መስዋዕት ነው፣ ያ ደም ነው የኃጥያታችንን ሥርየት እንድናገኝ ያስቻለን።

ቀጥሎ ሊነሣ የሚገባው ጥያቄ ይህ የክርስቶስ ሞት ይህ የክርስቶስ ደም ከኃጥያታችን ሊያነፃን የሚችለው እንዴት ተደርጎ ነው? የሚል ነው። እንደ ቅዱሣት መጽሃፍት ይህን ለማግኘት ትዕዛዛቱን በመታዘዝ ነው። ክርስቶስ ተሰቅሎ ሞቶ ተቀብሮ ከመቃብር ከተነሣ ቦኃላ ለሐዋሪያቶቹ የሰጠው መመሪያ እንዲህ የሚል ነበር። “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፣ ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈርድበታል” አላቸው (ማርቆስ 16፡15፣16)፣ አንድ ሰው በክርስቶስ አምኖ ከኃጥያቱ ንሠሃ ገብቶ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መስክሮ፣ ለኃጥያቱ ሥርየት በውኃ ውስጥ በመቀበር ከተጠመቀ ቦኃላ ከዚያ ከክርስቶስ ደም ጋር ይገናኛል። ጳውሎስ እንዲህ ይላል “በውድ ልጁም እንደ ጸጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን፣ እርሱም የበደላችን ስርየት ነው” (ኤፌሶን 1፡7) እዚህ ላይ የክርስቶስን ደም እየገለፀ ነው።

በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ አሥራ አንድ ላይ ዘገባው የሚነግረን የተነገራቸውን የወንጌል ስብከት ሰምተው በመታዘዛቸው የኃጥያት ሥርየትን አግኘተው በደሙም ታጥበው እንደዳኑ ግልፅ አድርጎ ጴጥሮስ ይተርካል፣ ይህንን ትዕዛዝ ካልተቀበሉ ደህንነት በየትኛውም ቦታ እና ሁኔታ ሊገኝ አይቻልም።

ጌታን የታዘዙ እና የዳኑ ሁሉ በተመሣሣይ ጊዜ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ወይም አካል በመባል በሚታወቁ ይሰዎች ስብስብ ውስጥ ተጨመሩ፣ ሐዋሪያት ወንጌልን ሲሰብኩ በግምት 3000 ነፍሣት ሰምተው ተጠመቁ፣ ጌታም በእነዚህ ላይ የሚድኑትን ዕለት ዕለት ይጨምር ነበር። “ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር” (ሐዋሪያት ሥራ 2፡47)። ይህቺ ቤተክርስቲያን ሌላ ቤተክርስቲያን፣ በሰው የተመሰረተች ሳይሆን የጌታ ቤተክርስቲያን ናት፣ የክርስቶስ መንፈሳዊ አካሉ ናት እሱ የሞተላት ስሙን የለበሰች ናት፣ አንድ ቀን ተመልሶ መጥቶ የሚወስዳት ነቸ፣ ቤተክርስቲያን ማንንም አታድንም ግን ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ያድናል።(ኤፌሶን 5፡23) እናም አንድ ሰው ለመዳን እና ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ ወደዚህቸ ቤተክርስቲያን መጨመር አለበት (ኤፌሶን 5፡25~27)

እንደ ዳኑ ሰዎች፣ እንደ ክርስቲያኖች፣ እንደ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት እግዚአብሄር የሚፈልግብን በታማኝነት እንድናመልከውና የክርስትና ህይወት እንድንኖር ነው፣ በዚህ መታዘዛችህን ነው፣ ቤታችን በሰማይ የሚሆነው። ይሄ ነው የእግዚአብሄር ዕቅድ ለሰው ልጆች።

ክርስቲያን ከሆንክ እናም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተማርከው

የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ከሆንክ ሰላምታችንን እናቀርብልሃለን። ካልሆንክ የተነገሩትን ነገሮች በቁም ነገር እንድታስብና ጌታን እንድትታዘዝ እና ትክክለኛ ክርስቲያን እንድትሆን ልናበረታታህ እንወዳለን።

ጥናታችን ስንቀጥል ባለህበት ቦታ እንዴት ጌታን መታዘዝ፣ ክርስቲያን መሆን፣ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን በጣም ቀላል እንደሆነ እናሳያሃለን። በአንተ አከባቢ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ማህበር ከሌለ እንዴት ባለህበት ቦታ የጌታ ቤተክርስቲያንን መትከል እንደሚቻል መረጃ እንሰጥሃለን ፣ ጥናትህን ከእኛ ጋር ቀጥልና ለጥያቄዎቸህ መልስ ከሰጠን፣ ጽሑፎችን ልንሰጥህ ወይም ለጌታ እንድትታዘዝ እንድንረዳህ እባክህን አግኘን

## ትምህርት 2

## መፅሐፍ ቅዱስ ያስፈልግሃል

ቤተክርስቲያን በጣም አስፈላጊ ነው፣ እንዴት የዚህ ቤተክርስቲያን አባል እንደምትሆን እናሳይሃለን። እንደዚሁም ይህ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ማህበር በአንተ አከባቢ ከሌለ እንዴት ሊኖር እንደሚቸልም እናሳይሃለን።

እያወራን ያለነው ሌላ ቤተክርስቲያን አይደለም ፣ የታይማኖት ድርጅት ቤተክርስቲያን አይደለም፣ ሰው ሰራሽ ቤተክርስቲያንም አይደለም ፣ ይልቅ እያወራን ያለነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለምናነበው ቤተክርስቲያን፣ የክርስቶስ ስለ ሆነቸው ቤተክርስቲያን ነው የክርስቶስን ስም ስለለበሰቸው ቤተክርስቲያን ነው እያልን ያለነው ይህን በተመለከተ ብዙ የምንላቸው ነገሮች ስላሉ በሰፊው እናያለን።

እዚህ ጋ ልናስታውስህ የምንወደው እግዚአብሄር ለሰው እቅድ እንዳለው ነው፣ እዚህ ምድር ላይ ለዓላማ እንዳስቀመጠው፣ የሚሠራውን ሥራ እንደሰጠው እና ለነፍሱ ደግሞ ቤት እንዳዘጋጀለት ልናስታውስህ እንወዳለን። እነዚህ ነገሮች በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጠዋል፣ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተገለጡ ደግሞ መፅሐፍ ቅዱስ ወይም አዲስ ኪዳን ያስፈልግሃል ማለት ነው፣ ምክንያቱም ይህንን ማወቅ አለብህና ነው። ይህንን ስንልህ እውነት እግዚአብሄር ላንተ ያለውን እቅድ ማወቅ ከፈለግክ ልታገኘው ይገባሃል።

መፅሐፍ ቅዱስ ይኖርሃል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁኝ፣ መፅሐፍ ቅዱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ይሸጣል፣ በየቤተክርስቲያኑ ይኖራል፣ ከጓደኛም ታገኛለህ፣ እግዚአብሄር ላንተ ያለውን እቅድ ለማወቅ የጋለ ስሜት ካለህ አታጣም፣ ስለዚህ ሊኖርህ ይገባል፣ ከዚህ ትምህርት ጋር ያሉትን ጥቅሶች ሄደህ የምታረጋግጥበት መፅሐፍ ቅዱስ ሊኖርህ ይገባል፣ ለማንበብ ለማጥናት መፅሐፍ ቅዱስ ሊኖርህ ይገባል።

በመጀመሪያ ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር ቃል መሆኑን ማወቅ አለብህ። ለሰው ልጅ የመጨረሻ መገለጡ ወይም ፈቃዱ ነው።

በቅዱሣት መፅሐፍት የምነግሩንን ሁሉ መቀበል አለብን ፣ ጳውሎስ እንዲህ ይላል “የእግዚአብሄር ሰው ፊፁምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ፣ የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበት መፅሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በፅድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል” (2 ኛ ጢሞተዎስ 3፡ 16፣ 17) ከዚህ ከተፃፈው መቀነስ መጨመር ወይንም ሌላ መተካት አንችልም (ዮሐንስ ራእይ 22፡18_19፣ ገላቲያ 1፡6_9) ቃሉንም አድራጊዎች መሆን አለብን፡፡ (ያዕቆብ 1፡22) ምክንያቱም አንድ ቀን በዚሁ ቃሉ ይፈረዳልና (ዮሐንስ 12፡48)

ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱስ ሲኖርህ የእውነትን ቃል በቅንነት ማቅረብ ትችላለህ (2ኛ ጢሞተዎስ 2፡15) ይህም ማለት በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች እንዳሉ መገንዘብ አለብህ፣ ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን ፡፡ ብሉይ ኪዳን በርግጠኝነት ተጀምሮ የተጠናቀቀው በነቢዩ ሚልኪያስ የክርስቶስ አዳኝነት አስቀድሞ ተነግሯል፡፡ ብሉይ ኪዳን የአባቶችን እና የሙሴን ዘመናትን ይወክላል፡፡ በዚያን ጊዜ ለነበሩት ህዝብ የተሰጠው የእግዚአብሄር ህግ ለሙሴ ነበር፡፡ ቦኃላ ክርስቶስ መጣ አዲስ ፈቃድ ወይም አዲስ ህግ ሰጠ ይህን በማድረጉ የመጀመሪያውን አሮጌ አደረገው፣ የተሻለ ህግ እንዲኖረን አሮጌውን አስወግዷል፡፡ ዕብራዊው ፀሐፊ ስለ ክርስቶስ ሲናገር እንዲህ ይላል “እነሆ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለው ብሎአል፡፡ ሁለተኛውንም ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል፣ በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈፅሞ በማቅረብ ተቀድሰናል” ይላል (ዕብራዊያን 10፡9፣10)፡፡ አሁን የምንኖረው በክርስቶስ ህግ ሥር ስለሆነ አሮጌውን ህግ ልንጠብቅ አይገባንም፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን የኖሩ ሰዎች ገና ያልመጣውን የአዲስ ኪዳንን ህግ አይጠብቁም፣ እኛም ዛሬ ያለነው የብሉይ ኪዳንን እንድንጠብቅ አንገደድም፡፡ ሆኖም ብሉይ ኪዳን አሁንም የእግዚአብሄር ቃልና አገለግሎቱ የኖቤል ዓላማ ነው፣ የሰውን ታሪክ ያሳያል፣ እንዲሁም እግዚአብሄር ከህዝቡ ጋር እንዴት እንዳደረገ ያሳያል፣ ጌታን የሚታዘዙና ለእርሱ የተባረኩ ሰዎችን ምሣሌዎችን ይሰጣል፣ ነገር ግን በሌላ በኩል እግዚአብሄርን ያልታዘዙትን እና በእሱ ላይ ያመጹትን እንዴት እንደቀጣቸውም ይናገራል፡፡ ከሁሉም በላይ ስለክርስቶስ መምጣት እና ስለሞቱ መቀበሩ እና ትንሣኤው ብዙ ትንቢቶችን ይናገራል፡፡ ወደ አዲስ ኪዳን ስንዞር እነዚህ እንዴት እንደተፈፀሙ እንመለከታለን፡፡ ስለዚህ ብሉይ ኪዳን ብዙ ዓላማዎች አሉት፣ ነገር ግን እንደ ህግ ልንከተለው እና በሱ መዳንን ልንጠብቅ አንችልም፡፡

አዲስ ኪዳን የእግዚአብሄርን ለሰው ልጅ ያለው እቅድ የተገለጠበት ነው፡፡ የተጀመረው በክርስቶስ ልደት፣ በክርስቶስ ሞት መቀበርና ከመቃብር መነሣት ሲሆን ከዚያም ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚመሰረት ፣ ከዚያም ወንጌል እንዴት ወደ ዓለም ሁሉ እንደሚደርስ ነው፡፡

እነዚህን ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት የዕብራዊያን ፀሐፊ የሚለውን

እናንብብ "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሄር በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፣" (ዕብራዊያን 1፡1፣2)፣ በክርስቶስ ተአምራዊ መለወጥ ጊዜ እግዚአብሄር ከሰማይ እንዲህ ሲል ተናገረ "እርሱም ገና ሲናገር እነሆ ብሩህ ዳመና ጋረዳቸው፣ እነሆም ከደመናው ፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ" (ማቴዎስ 17፡5) ይህ እንግዲህ ክርስቶስን ብቻ መስማት እንዳለብን ስለመንገሩ ምንም ጥርጥር የለንም። ስለክርስቶስ ህግ ስለያዘው ኪዳንም ምንም ጥርጥር የለንም እርሱም አዲስ ኪዳን ነው፣

የእግዚአብሄርን ቃል ስናጠና በአዕምሮአችን ልንይዘው የሚገቡን ብዙ ነገሮች አሉ፣ ስለዚህ ቃሉን እንደመለኮታዊ ህግ ልንቀበለው እና ልናከብረው ይገባል፣ ልንቀበለው፣ ልንከራከርበት ወይም ልንጠይቀው እግዚአብሄር ተናግሯልና እሱ ጉዳዩን መፍታት አለበት

ሁለተኛ ፦ የእግዚአብሄር ቃል አይከፋፍለንም። በእርግጥ የመፅሐፍ ቅዱስን ትምህርት እንከተላለን የሚሉ ብዙ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን ፣ ነገር ግን በሚያስተምሩት እና በሚሠሩት ይከፋፈላሉ፣ ይህ ሊሆን ይችላል? በፍፁም አይችልም፣ ጌታ ሁላችንንም በቃሉ ተናግሮናል እናም ሁላችንም የተናገረውን አምነን ትምህርቱን ስንታዘዝ አንድ ያደርገናል፣ ያም ማለት ሁላችንም አንድ ትምህርት እናምናለን፣ ሁላችንም በአንድነት እንድናለን ሁላችንም የአንድ ቤተክርስቲያን አባላት እንሆናለን፣ ሁላችንም አብረን እንሰግዳለን እና አንድ ተስፋ እናደርጋለ ክርስቶስ እንኳን አንድ እንድንሆን ፀልዮአል ነገር ግን በእርግጠኛነት አንከፋፍለንም (ዮሐንስ 17፡2_23) አዲስ ኪዳንን አንብብ እና የጌታ ህዝብ አንድ እንደነበሩ ታያላችሁ። ዛሬ በእንደዚህ ዓይነት ትምህርት ያልሆነ በጌታ ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል?

ሦስተኛ ፦ የጌታ ቃል የመጨረሻ ነው። ዛሬ ለሰው አዲስ መልዕክት የለውም፣ በሚቀጥሉት ቀናትና ዓመታትም አዲስ መገለጥ አይሰጥም። ፈቃዱን ለሰው ልጅ ሁሉንም ገለጠ፣ ሌላ ነገር መናገር ቢፈልግ ኖሮ ይናገር ነበር። እርሱ ያለንን ብቻ ስለሰጠ ከዚያ ቦኋላ የሚሰጥ ሌላ የለም ብለን መደምደም እንችላለን አሁንም እግዚአብሄር ይናገረናል የሚሉ ብዙ አሉ ግን ለምን ዓላማ ነው የሚናገራቸው? በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለፀው ተመሣሣይ መልዕክት ከሰጠ ለምን በቀጥታ ለመንም መናገር አስፈለገው? ለአንዱ አዲስ መገለጥ ከሰጠ ለሌሎቻችንስ ? በእርግጥ እግዚአብሄር ተናግሮናል የሚሉ ሰዎች ሁልጊዜ እግዚአብሄር የተወሰነ መልዕክት እንደሰጣቸው ይናገራሉ ነገር ግን ከተፃፈው ጋር ይጋጫል። ይህ ማለት እግዚአብሄር ከራሱ ቃል ጋር ይቃረናል ማለት ነው። እንዲህ ብለን ማመንስ እንችላለን? በጭራሽ ! ስለዚህም ዛሬ ከቃሉ ውጪ ለሰው አይናገርም ብለን መደምደም አለብን። የእግዚአብሄር ፈቃድ ለማወቅ

ከፈለግን  ወደ መፀሐፍ ቅዱስ መሄድ አለብን ። አንድ ሰው  እግዚአብሄር የተለየ መገለጥ እየገለጠለት ነው ማለት እንዲህ ያለው ሰው ተታሏል ማለት ነው። "ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሠማይ መልአክ ከሰበክንላቸሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላቸሁ የተረገመ ይሁን" (ገላቲያ 1፡8)

አራተኛ ፦አንድ ቀን በጌታ ቃል ለፍርድ እንቀርባለን። ዬትኛው ቃል ነው ? በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው እውነት ቃል። እዚያ የምናነበው እኛ የምፈርድብን ህግ ይሆናል።  የተፃፈውን ብንክድ ብንቀበል በቃሉ መሠረት ይፈረዳል "የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፣ እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል" (ዮሐንስ 12፡48) እግዚአብሄር በሁኔታዎቻችን ቃሉን አይለውጥም፣ እርሱ ያዘዘውን ብቻ ለማድረግ በጣም መጠንቀቅ ያለብን ለዚህ ነው። የትኛውንም ትምህርቱን አሁን አለመቀበል ማለት በፊቱ በምንቆምበት በዚያ ቀን ይጥለናል ማለት ነው። ቃሉን አምነን ብንታዘዝ ብንኖርም በዚያ ቀን በእርግጥ ይባርከናል።

ጓደኞቼ፦ መፅሐፍ ቅዱስ እንዳለዎት ተስፋ አደርጋለሁ። ግን ከሌለዎት አንድ ለማግኘት ጥረት እንድታደርጉ አበረታታዎታለሁኝ ። የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለማወቅ ማንበብና ማጥናት ያስፈልግዎታል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ በልብህ እምነት ለመገንባት ማቴዎስን፣ ማርቆስን፣ ሉቃስንና ዮሐንስን አንብብ ለመዳን ምን እንደሚያስፈልግህ ለማወቅ የሐዋሪያት ሥራን መፅሐፍ አንብብ። ስለኃጥያታቸሁ ንሠሀ እንድትገቡ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ እንድትመሰክሩ እና ለኃጥያትዎ ሥርየት እንድትጠመቁ ከዚያም የጌታ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደምትተከል አንብብ፣ የክርስቲና ህይወት እንዴት መምራት እንዳለብን ለማወቅ እና የዘላለም ህይወት ተስፋን ለማግኘት አዲስ ኪዳንን ማንበብዎን ይቀጥሉ፣

## ትምህርት 3
## መዳን ያስፈልገሃል

ባላቸሁበት የክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንዴት መጀመር እንዳለብን ተከታታይ ጥናታችንን እንቀጥላለን፣ ክርስቲያን ከሆንክ እና የጌታ ቤተክርስቲያን ጉባኤ ባንተ አከባቢ ከሆነ እዚያ እንድታመልክ እናበረታታሃለን። በጣም ሩቅ ከሆንክ  ግን በምትኖርበት አከባቢ ጉባኤ እንድትጀምር እናበረታታሃለን።

ከነዚህ ሀሳቦቸ ጋር በመስማማት ፣ በዚህ ገዜ ትኩረታችን መዳን ያስፈልግሃል በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ይሆናል።

ድኜያለሁ ብለህ የምታስብ ከሆነ ምንም ባልናገርህም ዳሩ ግን ብዙዎቸ ሳይድኑ ድነናል ብለው የሚያስቡ በርካቶቸ አሉ። እነዚህ ክርስቲያን ነን ብለውም ያስባሉ፣ አንተም እንደዚህ ከሆንክ ክርስቲያን አይደለህም፣ እነዚህ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ካመኑና ከመሰከሩ እምነት ብቻ እንደሚያድናቸው

ይናገራሉ። ሌሎቹም እንዷዚሁ በጌታ ተቀባይነት አግኝተናል ይላሉ፣ በዚህ ትምህርት ላይ አንድ ሰው ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለበት ከመፅሐፍ ቅዱስ ከራሱ እናያለን፣ ይህንን ከተማርክ በኃላ አንተ የዳንክበት መንገድ ትክክል ይሁን አይሁን ማወዳደር ትችላለህ ። በሃሳብህ የዳንክ የመሰለህ ዳሩ ግን መዳንህ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ በታማኝነት የእግዚአብሄርን ቃል አንብበህ በትክክለኛው መንገድ እንድትድንና ቃሉ በሚያዝህ መንገድ እንድትድን አበረታታሃለሁ።

የሰው ልጅ በሙሉ ሲወለድ ያለ ኃጥያት ነው የተወለደው ዳሩ ግን ክፉ እና ደጉን መለየት በቻለበት ጊዜ ህግን መተላለፍ ኃጥያትን መሥራት ይጀምራል፣ የዬትኛውም ሀገር ህግ ህፃናቶች ወንጀል እንኳን ቢሰሩ እነሱን የመዳኝበት አንቀፅ የለውም፣ ነገር ግን በወጣትነት ዕድሜ ላይ ሲደርሱ መልካምና ክፉውን መለየት ሲችሉ ለሠሩት መጥፎ ሥራ ኃላፍነትን ይወስዳሉ፣ ይህም ጥፋት ወይም አመፅ በእግዚአብሄር ፊት ኃጥያት ሆኖ ይታያል። ኃጥያት የእግዚአብሄርን ህግ መተላለፍ ነው፣ ኃጥያትም አመፅ እንደሆነ ሐዋሪያው ዮሐንስ ይናገረአል (1ኛ ዮሀንስ 3፡4) አንድ ሰው አንዴ ኃጥያተኛ ከሆነ ምህረት ይቅር መባል ያስፈልገዋል፣ ይህንን ኃጥያቱን ለማስወገድ የእሱ መልካምነት፣ ዬትኛውም መስዋዕት ሊያስወግድለት አይችልም (ኤፌሶን 2፡8፣9) ከላይ እንደተገለፀው መልካም የሠሩ ሁሉ በራሳቸው ፅድቅ መዳን ስለማይችሉ ጠፍተዋል። ክርስቶስ ሲናገር ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰአማያት አይገባም የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ካልሆነ በቀር ይላል (ማቴዎስ 7፡21_ 23) አንድ ሰው ከዳነም በኃላ ልርጌታ ታማኝ ሆኖ መኖር እንዳለበት መፅሐፍ ይናገራል (ራዕይ 2፡10) ይህ ማለት ሰው ከዳነም በኃላ ቢጠፋ በንሠሃ መመለስ አለበት፣ ነው

በአካል አላውቅህም የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆንክ ወይም እንዳልሆንክ አላውቅም ፣ ድነህ ከሆነ ወይም አልዳንክ እንደሆን አላውቅም ነገር ግን ባለህበት ሁኔታ ውስጥ ልንረዳህ የምንችልበትን መንገድ እናስባለን።

ለምሣሌ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን የማታምን ከሆነ አንተ አልዳንክም፣ ክርስቶስ እራሱ እንዲህ ብሏል “ በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም፣ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሄር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል” ብሏል (ዮሐንስ 3፡18) እንደገናም እንዲህ ብሏል “እንግዲህ በኃጥያታችሁ ትሞታላችሁ አልኳችሁ ፣ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጥያታችሁ ትሞታላችሁና አላቸው” (ዮሐንስ 8፡24)። እምነት ብቻ ሊያድን ባይችልም፣ አንድ ሰው ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ካላመነ የጌታ ሊሆን አይችልም። ነጥቡ አንድ ሰው በክርስቶስ ካመነ በኃላ ፣ ለመዳን የጌታን ፈቃድ መታዘዝ አለበት።

በመቀጠል ፦አንድ ሰው ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ካመነ ነገር ግን ከኃጥያቱ ንሠሃ ካልገባ፣ በአፉ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን

ካልመሰከረ እንዲሁም ለኃጥያቱ ሥርየት ካልተጠመቀ ሊድን አይችልም። ክርስቶስ እንዲህ ብሏል "እላችኋለሁ አይደለም ነገር ግን ንሰሃ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ" አለ (ሉቃስ 13፡3) አንድ ጊዜ ደግሞ እንዲህ ብሏል "ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ"(ማቴዎስ 10፡32) ጳውሎስም እንዲህ ብሎ ነበር "ሰው በልቡ አምኖ ይፀድቃልና በአፉ፣ መስክሮ ይድናልና" (ሮሜ 10፡10)፣ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል "ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማርቆስ 16፡16) እነዚህ ምን ማለት ናቸው? ይህ ማለት አንድ ሰው ከኃጥያቱ ነፃ ሆኖ ለመዳን በክርስቶስ ማመን ከኃጥያቱ ንሰሃ መግባት፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን በአፉ መመስከር እና ለኃጥያቱ ሥርየት በውኃ ውስጥ በመቀበር መጠመቅ አለበት ፣ ይህን ሁሉ ያላደረገ ሰው በእርግጥ ጠፍቷል።

ከላይ የተገለጸው እውነት ብቻ ሳይሆን አንድ ሰው የክርስቶስ የሆነችው ቤተክርስቲያን አባል ካልሆነ ያ ሰው አልዳነም። አንድ ሰው የዬትኛውም ቤተክርስቲያን አባል ሊሆን ይችላል ዳሩ ግን እስካሁን የትክክለኛዋ ቤተክርስቲያን አባል አልሆነም። በርግጥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ የየትኛውም ቤተክርስቲያን አባል መሆን አስፈላጊ እንዳልሆነ የሚከራከሩ አሉ። እውነት አንድ ሰው የየትኛውም ቤተ እምነት አባል ወይም ሰው ሰራሽ ቤተክርስቲያን አባል ሳይሆኑ መዳን እና ወደ መንግሥተ ሰማያት መሄድ ይችላሉ ነገር ግን አንድ ሰው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ካልሆነ ሊድን አይችልም፣ "የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሌላ ቤተእምነት አይደለችምን? " ብለህ ትጥይቅ ይሆናል፣ መልሱ አይደለም ነው። ቤተክርስቲያን አዳኝ ባትሆንም ፣ ክርስቶስ የዳኑትን ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምራቸዋል። በበዓለ ሃምሳ ቀን ወንጌል ከተሰበከ እና ሦስት ሺህ የሚያህሉ ጌታን ከታዘዙ ቦኃላ ዘገባው እንደሚናገር "ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፣ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህሉ ነፍስ ተጨመሩ" ይላል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡41)፣ ከዚያም ቀጥሎ "ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእንርሱ ላይ ይጨምር ነበር" ይላል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47)

ከዚህ ገለፃ የምንረዳው አንድ ሰው የክርስቶስ የጌታ ቤተክርስቲያን አባል ካልሆነ እንዳልዳነ ነው። ምክንያቱም የዳኑትን ወደ ቤተክርስቲያኑ የሚጨምረው ጌታ ነውና፣ ጌታ ደግሞ ወደ ራሱ ቤተክርስቲያን ነው የሚጨምረው፣ በሌላ አንገጋገር በክርስቶስ ወደ ቤተክርስቲያን ያልተጨመረ ሰው አልዳነም ማለት ነው። በኤፌሶን 5፡23 ላይ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን አዳኝ መሆኑን ነው። ክርስቶስ ስንት ቤተክርስቲያን አሉት? አንድ ብቻ መሆኗን በኤፌሶን 4፡4 ላይ ይነግረናል።

ቀጣይ ሁኔታዎች ሊታሰብባቸው የሚገቡ ሌሎች እውነቶች ደግሞ እንደ አምልኮ፣ ክርስቲያናዊ ህይወት መኖር፣ የጌታን ስም መልበስ ወዘተ የሚሉት ይኖራሉ። ነገር ግን በእርግጠኝነት አንድ ሰው ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ

እንደሆነ ማመን፣ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ መፈፀምና መጠበቅ አለበት። ወንጌልን በቃሉ መሰረት መታዘዝና ለምዳን የጌታ ቤተክርስቲያን አባል ሁኑ፣ አሁን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልጠይቅህ እፈልጋለሁ። ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ታምናለህ? የክርስቶስን ወንጌልን ታዘሃል? የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ነህ? ከእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ ለአንዱ ወይም ለብዙዎች መልስህ አይደለም ከሆነ አልዳንክም ማለት ነው። በሓቀኝነት ድኜሃለሁ ለማለት ለእነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ መልስህ አዎን ብለህ መልስ መስጠት መቻል አለብህ። የእግዚአብሄር ልጅ ካልሆንክ እንድትድን ጌታን እንድትታዘዝ ላበረታታህ እፈልጋለሁ፣ አስታውስ ራስህን ማዳን አትችልም፣ እንዲሁም የሰዎች ትምህርት ሊያድንህ አይችልም። መዳን የምትችልበት ብቸኛው መንገድ ጌታ እንድታደርግ የሚፈልገውን ስታደርግ ብቻ ነው። ለእምነት እና ለታዛዥነት ምንም ሌላ ምትክ ሊኖር አይችልም፣ እና ስለቤተክርስቲያን ይህን ካዳረግክ ማለትም በሰዎች ትምህርት እና ሰው ሰራሽ መዳን ካመንክ በጌታ ቤተክርስቲያን መቀላቀል አትችልም ነገር ግን እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተምረህ አንዴ ጌታን ከታዘዝክ እና ከዳንክ እሱ ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምርሃል፣(የሐዋሪያት ሥራ 2፡47)

በጌታ ትዕዛዝ መሰረት ከዳንክ እሱ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ ባለው (ማቴዎስ 16፡18) ላይ ትጨመራለህ፣ እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አብያተክርስቲያናት አካል ናቸው፣ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ሁሉ የአብያተክርስትያናት አካል ናቸው በአንተ አከባቢ ሁለት ወይም ሦስት አባላት ያላቸው ቤተክርስቲያን ካሉ አንተም መዳንህን ነግረሃቸው የእነሱ አባል መሆንህን ነግረህ አብረህ አምለክ ትችላለህ፣ ምናልባት ካወቁ ሊቀበሉህ ይችላሉ፣ ነገር ግን ስለአንተ መረጃው ከሌላቸሀው ልትነግራቸው ይገባል።

አንተ ባለህበት አከባቢ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከሌለ አንተ እራስህ በዙሪያህ ያሉትን አስተምረህ በማገልገል እንደአንተው ጌታን እንዲታዘዙ አድርጋቸው አድራህን በማመቻመች ካሉት በዙሪያህ ካሉት የኃይማኖት ቡድኖች ጋር አትቀላቀል ዳሩ ግን በትጋት በማስተማር የአዲስ ኪዳንን ቤተክርስቲያን ፍጠርና እያስተማርክ የክርስቶስን ቤተክርስቲያንን ማብዛት አለብህ።

## ትምህርት 4
## ወንጌልን እንዴት መታዘዝ እንደሚቻል

በዚህ ትምህርት ወንጌልን ስለመታዘዝ እናጠናለን። ወንጌል ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ? ብዙዎች አያውቁም። ወንጌል ምን እንደሆነ ካላወቁ እንዴት ይታዘዛሉ ? መታዘዝ አይችሉም ለዚህም ነው ጊዜ ወስደን ወንጌልን መታዘዝ እንደሚቻል የምንወያየው፣

በመጀመሪያወንጌልምንእንደሆነእናስብ።ይህኡልጊዜየምንጠቀመመው

ቃል ነው ነገር ግን ስለ "ወንጌል" ማውራት ምን እንደሆነ ካላወቅን ምን ይጠቅማል፡፡ ወንጌል የሚለው ቃል የምስራች ወይም መልካም ዜና ተብሎ ይገለፃል፣ ሐዋሪያው ጳውሎስ ሲናገር "መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደተፃፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?" (ሮሜ 10፡15) ወንጌል ለምን መልካም ዜና ተባለ ? ምክንያቱም እሱ የክርስቶስ ሞት መቀበር እና ትንሣኤ የሚያወራ ስለሆነ ነው፣

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲፅፍ እንዲህ ይላል "ወንድሞቼ ሆይ የሰበኩላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችኋለሁ፣ በከንቱ ካላመናችሁ በቀር፣ ብታስቡት በምን ቃል እንደ ሰበኩላችሁ አሳስባችኋለሁ፣ እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ፣ እንዲህ ብዬ መፅሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለኃጥያታችን ሞተ ተቀበረም፣ መፅሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ" (1 ቆሮንቶስ 15፡1_4)፡፡

የክርስቶስ ሞት መቀበርና ከሞት መነሣት እንዴት መልካም ዜና ሊሆን ይችላል? እሱ መልካም ዜና ነው ምክንያቱም እሱ የሞተው ስለኃጥያታችን ነው እሱ የሞተው እኛ እንድንድን እና ዘላለማዊ የህይወት ተስፋ እንዲኖረን ነው፡፡ ነገር ግን እሱ የሞተው የመጨረሻ ሞት አይደለም ግን እኛንም ከሞት ለማዳን እሱ ከመቃብርም በሦስተኛው ቀን ተነስቷል፣ ይህም የእግዚአብሄር ልጅ ስለመሆኑ ማረጋገጫ እና ሰዎችን ደግሞ የማዳን ኃይል እንዳለው ማሳያ ነው፣ ጳውሎስ ሲናገር " ነገር ግን ገና ኃጥያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞቶአልና፣ እግዚአብሄር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" (ሮሜ 5፡8)፣ ጴጥሮስም "ለኃጥያት ሞተን ለፅድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጥያታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፣ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ" ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 2፡ 24)

ስለዚህ ሞት መቀበርና ትንሣኤው እንድንወያይ የሚናገሩ ብዙ ጥቅሶች አሉ ነገር ግን ይህ የእሱ ሞት መቀበር እና ከሞት መነሣት እኔና አንተን እንዴት ሊያድነን ይችላል?፣ በመጀመሪያ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ማመን እና እሱ እንደሞተ እንደተቀበረ እና ከመቃብርም እንደተነሣ ማመን አለብን ይህን ካላደረግን መዳን አንችልም ክርስቶስ እራሱ ሲናገር "እንግዲህ በኃጥያታችሁ ትሞታላችሁ አልኋችሁ ፣ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጥያታችሁ ትሞታላችሁና አላቸው" (ዮሐንስ 8፡24)

ይህንን በህይወት ዘመናችን ሁሉ እያመን ዳሩ ግን እንደጠፋን ነው፣ ምክንያቱም ማመን ብቻውን በቂ አይደለምና በወንጌል ማመን ብቻ ሳይሆን ለወንጌል መታዘዝም አለብን እንዴት ነው በወንጌል የምንታዘዘው ? ቅዱሣት መፅሐፍትን ማንበብ ስንቀጥል የወንጌል ትዕዛዛት እንዳሉ ተነግሮናል ፡፡ በመጀመሪያ መስማት አለብን ፣ ለዚህም ነው ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ወደ

ዓለም ሁሉ ሄዷው ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ ያዘዛቸው (ማርቆስ 16፡15)፣ ጳውሎስም እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሄር ቃል ነው (ሮሜ 10፡17)፣ ብሏል ። በትክክልም በአሁኑ ጊዜ እኛም የምናደርገው ይህንን ነው፣ የእግዚአብሄርን ቃል እናጠናለን ወንጌልን እንሰማለን ስለዚህም ምን እንደሆነ እናውቃለን፡፡ በመቀጠልም በወንጌል እናምናለን፡፡ ክርስቶስ ሲናገር “ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል” (ማርቆስ 16፡16)፣ የዕብራዊያን ፀሐፊም እንዲህ ብሏል “ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፡፡ ወደ እግዚአብሄር የሚደርስ እግዚአብሄር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና” (ዕብራዊያን 11፡6)

ከዚያም የንሠሃ ትዕዛዝ ይመጣል፡፡ ያ ማለት በቀላሉ አንድ ሰው እነዚያን የተሣሣቱ ነገሮቹን ማቆም አለበት ማለት ነው፣ አንድ ሰው መዳን ከፈለገ ንሠሀ ለመግባት ፈቃደኛ መሆን አለበት፣ ክርስቶስ ንሰሀ መግባት ወይም መጥፋት አንዱን ምረጡ ይለናል (ሉቃስ 13፡3) ጳውሎስም እግዚአብሄር ሰዎች ሁሉ ንሰሀ እንዲገቡ ማዘዙን ያውጃል (የሐዋሪአት ሥራ 17፡30) ጴጥሮስም ሰዎች ንሠሀ እንዲገቡና ለኃጥያታቸው ሥርየት እንዲጠመቁ ሰብኳል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38)

ቀጥሎ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መመስከር እንዳለብን ነው፣ ይህንን በአንደበታችን ካልመሰከርን እንደማንድን ይነግረናል፣ ይህንን በሰው ፊት አለማድረግ ማለት ጌታን መካድ እንደሆነና ጌታም የሚክዱትን በሰማይ ባለው አባቱ ፊት እንደሚክድ ተናግሯል (ማቴዎስ 10፡32)፣ ጳውሎስም ሲናገር “ሰው በልቡ አምኖ ይፀድቃልና፣ በአፉም መስክሮ ይድናልና” ብሎ በሮሜ 10፡ 10 ላይ ተናግሯልና፣ ፊሊጶስም ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ለመጠመቅና ለመዳን መመስከር እንዳለበት ነግሮት እሱም አድርጎታል (የሐዋሪያት ሥራ 8፡37)፡፡

በመጨረሻም አንድ ሰው ኃጥያቱ እንዲታጠብለት የኃጥያት ሥርየት እንዲያገኝ በውኃ ውስጥ በመቀበር መጠመቅ እንዳለበት ቃሉ ያስተምረናል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል” ብሏል፡፡(ማርቆስ 16፡16) ጴጥሮስ ለኃጥያት ሥርየት መጠመቅ እንዳለባቸው ሰብኳል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38)፣ ይህን ጥምቀት በተመለከተ ብዙ የቅዱሣት መፅሐፍት ጥቅሶች አሉን፣ ጥምቀት ወደ ክርስቶስ እንደሚጨምር (ሮሜ 6፡3፣ 5)፣ ጥምቀት በአካሉ ወይም በቤተክርስቲያን እንደሚጨምር (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13)፣ በጥምቀት ዳግም ልደት እና ወደ እግዚአብሄር መንግሥት መግባት እንደሚሆን (ዮሐንስ 3፡3፣5) ቃሎቹ ያስተምሩናል

ከዚህ በላይ የተገለፁት ሁሉ ከክርስቶስ ሞት መቀበር እና ከመቃብር መነሣት (ትንሣኤ) ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞተ፣ ሰውም ከኃጥያቱ ይሞታል፣ ክርስቶስ በምድር ሆድ ውስጥ ተቀበረ ሰውም በውኃ ውስጥ ይቀበራል፣ ክርስቶስ ከመቃብር ተነሣ፣ ሰውም ከውኃ ውስጥ ይነሣና

በአዲስ ህይወት ይመላለሣል (ሮሜ 6፡1_12) ይህ በጣም ውብ አይደለም ? ጳውሎስ ሲናገር "ነገር ግን አስቀድማቸሁ የኃጥያት ባሪያዎች ከሆናቸሁ፣ ለተሰጣቸሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባቸሁ ስለታዘዛቸሁ፣ ከኃጥያትም አርነት ወጥታቸሁ ለፅድቅ ስለተገዛቸሁ ለእግዚአብሄር ምስጋና ይሁን" ይላል (ሮሜ 6፡17_18) አስተምህሮው የሚያመለክተው የክርስቶስን ሞት፣ መቀበር እና ትንሣኤ፣ ለወንጌል መታዘዝ፣ ኃጥያተኞቸን የሚያመለክት ሲሆን ለኃጥያቱ ሲሞት፣ በጥምቀት ውኃ ውስጥ ሲቀበርና ከዚያም ከውኃው ውስጥ እንደሚነሣ እንደሚወጣ ያመለክታል። ያ ውኃ መቃብር እንደትንሳኤ የተገለፀው ከዚህ በፊት አንድ ሰው የኃጥያት አገልጋይ ነበር ነገር ግን እነዚህን የመታዘዝ ተግባራት ሲፈፅም ያ ሰው የፅድቅ አገልጋይ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ ጌታን ሲታዘዝ በሞት ላይ ያለውን እምነት ያውጃል፣ በዚህ መልኩ ከክርስቶስ ሞት፣ መቀበር እና ትንሣኤ ጋር ይገናኛል። ለወንጌል መታዘዝም በዚህ መልኩ ይፈፀማል ማለት ነው።

ሰው ወንጌልን መታዘዝ አለበት ምክንያቱም ጳውሎስ ሲናገር ጌታ አንድ ቀን ሲመጣ እግዚአብሄርን የማያውቁትንና ወንጌልን ያልታዘዙትን ይበቀላል ይለናል (1 ተሰሎንቄ 1፡7_9)፣ ጴጥሮስም ሲናገር "ፍርድ ከእግዚአብሄር ቤት ተነስቶ የሚጀምርበት ጊዜ ደርሶአልና፣ አስቀድሞም በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሄር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን? " ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 4፡17)፣ አንድ ሰው ለመዳንና ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ ለወንጌል መታዘዝ እንዳለበት ግልፅ ነው፣ ምክንያቱም እነዚህ ፀሀፊዎቸ ያመኑት እንኳን በጭንቅ የሚገቡ ከሆነ ያልዳኑት ጌታን የማይታዘዙት ለመታዘዝ ጥረት ካላደረጉ ምን ሊጠብቁ ይቸላሉ?

አንድ ሰው እንዴት ወንጌልን ሊታዘዝ ይቸላል? ቅዱሣት መፅሐፍት እንደሚነግሩን አንድ ሰው መፅሐፍ ቅዱስን አጥንቶ እውነቱን ማወቅ አለበት የእግዚአብሄርን በመስማት ክርስቶስን ወደ ማወቅ መምጣት ፣ እሱ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን በዚህኛውም ዓለምና በሚመጣውም ሰዎቸን ሊያድን የሚቸል ኃይል እንዳለው ማወቅ እና ማመን አለብን፣ ቀጥሎ ከኃጥያታቸን ንሰሀ መግባት አለብን ይህም ማለት ከመጥፎ ሥራቸንና ልምዳቸን ተስፋ ቆርጠን ወደ ትክክለኛው መንገድ መመለስ ማለት ነው፣ ይህ ማለት ደግሞ አንድ ሰው ንሠሀ ከገባ በኃላ ተመልሶ እግዚአብሄርን የሚቃወም ህይወት ውስጥ መግባት አለመቻል ማለት ነው፣ ከንሰሀ ቀጥሎ አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን በልቡ አምኖ በአፉም መመስከር አለበት በእውነቱ አንድ ሰው ይህንን እምነቱን ካልመሰከረ ሊድን አይቸልም ፣ በመጨረሻ ይህ ያመነ የመሰከረ ሰው ለኃጥያቱ ሥርየት በውኃ ውስጥ በመቀበር መጠመቅ አለበት፣ ይህንን ያደረገውን ሰው ጌታ ያድነዋል በቤተክርስቲያኑም ላይ ይጨምረዋል። ይህ ታዲያ ቀላል አይደለም?

## ትምህርት 5

### የጌታ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚገለፅ

ዋናው ትምህርታችን እንዴት ባለህበት አከባቢ የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን መጀመር እንደሚቻል ማስተማር ነው፣ አንተ ባለህበት አከባቢ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ካለ እጅግ በጣም አስደናቂና ደስ የሚል ነው። አንተ ባለህበት አከባቢ ከሌለ ግን መኖር አለበት። ወይም አንተ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ወደ ሌለበት ቦታ የምትሄድ ወይም የምዛወር ከሆነ እዚያም ሊኖር ይገባል። እዚያ ቦታ የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን መጀመር ያለብህ አንተው ልትሆን ይገባል። ከእኔ ጋር ወደዚህ ነገር የሚመሩንን ብዙ ነገሮች እንድታስብ እፈልጋለሁ
ይህንን በማስተዋል እንዲረዳን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚገለፅ ማሰብ ማወቅ አለብን።

ይህንን ግልፅ ለማድረግ በእርግጠኝነት ስለቤተክርስቲያን ምንነት ከመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ታነባለህ፣ ቤተክርስቲያን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ መኖሩን ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን መለያ ምልክቶችን ሁሉ በዝርዝር በመግለፅ ከሚታዩት እጅግ በርካታ በዓለም ላይና በዙሪያችን ካሉት የሚለይበትን እንድናውቅ ያስተምረናል መፅሐፍ ቅዱስ። ለምሣሌ አንተ ከነዚህ የኃይማኖት ቡድኖች አባል ከሆንክ ወይም ባንተ ዙሪያ ካሉት ሌሎች ቤተክርስቲያኖች ጋር ከመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ከተማርከው ቤተክርስቲያን ጋር በመለያ ምልክቶቹ አማካይነት ማወዳደር እና ትክክለኛ የመፅሐፍ ቅዱሱ ቤተክርስቲያን ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ማረጋገጥ ትችላለህ።

የአንዱም ሆነ የሌላው አባል ከሆንክ ስለቤተክርስቲያን ምን ልዩነት እንዳለው ማወቅ ትፈልግ ይሆናል። ቤተክርስቲያን አስፈላጊ አይደለችም፣ አታድንም እናም አንድ ሰው የየትኛውም ቤተክርስቲያን አባል ካልሆነ ወደ ሰማይ መሄድ ይችላል ብለህ ታስብ ይሆናል። አሁን ጥሩ እና ምክንያታዊ ይመስላል፣ ነገር ግን አይደለም፣ ቤተክርስቲያን አስፈላጊ ባይሆን ኖሮ ጌታ ለምን ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ ይላል? ቤተክርስቲያን አስፈላጊ ባይሆን ኖሮ ጌታ ለምን እራሱን አሳልፎ ይሰጥ ነበር? እውነት ነው ቤተክርስቲያን አዳኝ አይደለችም ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን በዳኑ ሰዎች የተዋቀረች ናት ነገር ግን ክርስቶስ የቤተክርስትያን አዳኝ ስለሆነ አንድ ሰው ለመዳንና ወደ መንግሥተ ሰማያትም ለመግባትም እሱ የመሰረታት ቤተክርስቲያን እና የራሱ የሆነች አባል መሆን ያስፈልጋል።

አሁን ወደ መፅሐፍ ቅዱስ እራሱ ሄደን ስለቤተክርስቲያን መለያ ምልክቶችን እንድንመለከት እፈልጋለሁኝ ብዙ የሚነሱ ስለአሉ አንተም ታያቸዋለህ

ከረጅም ዓመታት በፊት የእግዚአብሄር ነቢይ ኢሳያስ በትንቢት እንዲህ ብሎ ነበር "በዘመኑም ፊፃሜ የእግዚአብሄር ቤት ተራራ በተራሮች ራስ ላይ

ፀንቶ ይቆማል፣ ከኮረብቶቸም በላይ ከፍ ከፍ ይላል፣ አህዛብም ሁሉ ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ። ሕግ ከፅዮን የእግዚአብሄርም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣልና፣ ብዙዎቸ አህዛብ ሄደው ኑ ወደ እግዚአብሄር ተራራ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል፣ በጎዳናውም እንሄዳለን ይላሉ" አለ (ኢሣያስ 2፡2_3)

ነቢዩ ኢዩኤልም ከዘመናት በፊት እንዲህ ብሎ ተንብዮ ነበር "ከዚህም በኃላ እንዲህ ይሆናል መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሣለሁ ወንዶቸና ሴቶቸ ልጆቻቸሁም ትንቢት ይናገራሉ፣ ሽማግሌዎቻቸሁም ህልምን ያልማሉ፣ ጎበዛዞቻቸሁም ራዕይ ያያሉ፣ ደግሞም በዚያ ወራት በወብዶቸና በሴቶቸ ባሪያዎቸ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ" አለና ተናገረ (ኢዩኤል 2፡28_29)

ነቢዩ ዳናኤልም ጨምሮ እንዲህ አለ "በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፣ ለሌላ ህዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፣ እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለቸ፣ ታጠፋቸውማእቸ ለዘላለምም ትቆማለቸ" አለ (ዳናኤል 2፡44)

አሁን እነዚህ የእግዚአብሄር ነቢያት እያሉ ያሉት ምንድነው? እነዚህ የእግዚአብሄር መንፈሳዊ መንግሥት ወይም ቤተክርስቲያን ወደ ፊት እንደምትመሰረት እየተናገሩ ነው። ይህም የሚመሰረተው በኢየሩሣሌም እንደሆነና ከዚሁ ተነስቶ ወደ ዓለም ሁሉ እንደሚደርስ ተናገሩ። በኃይልም እንደሚመጣና ፈፅሞ እንደማይፈርስ ነገር ግን ለዘላለም ፀንቶ እንደሚቆም ነው የተናገሩት፣ ይህም በሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ 2 ላይ በኢየሩሳሌም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወንጌል ተሰበከና ከዚያ ወደ ዓለም ሁሉ ደረሰ እስካሁንም ፀንቶ እንደሚቆም የተናገሩት ተፈፀመ።

ክርስቶስ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ ብሎ (በማቴዎስ 16፡18)፣ እንደተናገረው በሐዋሪያቱ በኩል እንዳለው አደረገ። መንፈስ ቅዱስ አፅናኙን እንደሚልክላቸው ቃል በገባላቸው መሰረት (ዮሐንስ 16፡13)፣ ላከላቸው፣ ከሞት ከተነሣ በኃላ ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት እንዲህ ብሏቸው ነበር "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላቸሁ፣ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማሪያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላቸሁ አለ" (የሐዋሪያት ሥራ 1፡8) ይህም ደግሞ ተፈፅሟል።

በሐዋሪያት ሥራ 2 ላይ ስናነብ ቤተክርስቲያን የተመሰረተቸው በኢየሩሳሌም ከተማ ነው። ቀደም ሲል እንደተገለፀው የእግዚአብሄር ነቢያት የጌታ መንግሥት ወይም ቤተክርስቲያን የምትመሰረትበትን ቦታ የኢየሩሳሌም ከተማ ብለው ሰይመዋታል፣ የእግዚአብሄርም ቃል ከዚህቸ ከተማ ይወጣል ተባለ፣ ክርስቶስ ለሐዋሪያቱ እንዲህ ብሎ ነበር "እንዲህም አላቸው ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፣ በስሙም ንሠሀ እና የኃጥያት ሥርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአህዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ

ተፅፏል እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ” አላቸው (ሉቃስ 24፡46_48)፣ ጴጥሮስና ሐዋሪያቶች ለብዙ ሕዝቦች ከሰበኩ ቦኋላ ህዝቡ ልባቸው ተነክቶ ምን እናድርግ ? ብለው በጠየቁ ጊዜ ጴጥሮስ እንዲህ አላቸው “ጴጥሮስም ንሠሀ ግቡ ኃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ” አላቸው (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38)፣ በዚያን ቀን 3000 የሚያህሉ ነፍሳት ተጠመቁና ወደ ዳኑት ቤተክርስቲያን ተጨመሩ (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47)

በሐዋሪያት ሥራ 2 ላይ የምናነበው የጌታቸን ቤተክርስቲያን ጌታ ከሞት ከተነሣ ቦኋላ ከሣምንቱ በመጀመሪያ ቀን በጴንጤቆስጤ ቀን በግምት በ33 ዓ/ም ተመሰረተች

ሐዋሪያት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ወደ እውነት ሁሉ እንዲመራቸው ተቀበሉ፣በዚህም ኃይል ተአምራትን ማድረግ፣ እዚያ በተሰበሰቡት ብዙ ሰዎች ቋንቋ ወንጌልን በመስበክ ምስክረነታቸውንም ገለፁ (የሐዋሪያት ሥራ 1፡8፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡1_4፣ 9)

ቤተክርስቲያን በዳኑት ሰዎች የተዋቀረች የሆነችው ክርስቶስ በዳኑት ላይ ዕለት ዕለት ስለሚጨምር ነው(የሐዋሪያት ሥራ 2፡41፣ 47)የክርስቶስ መንፈሳዊ አካሉ የሆነችና ክርስቶስም ራስ የሆናት ይህቺው ቤተክርስቲያኑ ስለመሆኗ ጳውሎስ ሲናገር እንዲህ ይላል “እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፣ እርሱም በሁሉም ፊተኛ ይሆን ዘንድ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው” (ቆላስያስ 1፡18) እንደዚሁም ኤፌሶን 1፡22፣ 23 እና ኤፌሶን 5፡23፣ አንብብ፡፡ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተዋጀች ናት፣ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ሲናገር እንዲህ ይላል “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሄርን ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሣት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ” አላቸው (የሐዋሪያት ሥራ 20፡28) በሌላ ጊዜ ደግሞ ለነዚሁ ኤፌሶን ሰዎች ሲናገር “ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና” (ኤፌሶን 5፡23) ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ከሞተ እና እርሱ አዳኝ ከሆነ ይህ ማለት ክርስቶስ ለእሷ ትልቅ ቦታ ሰጧል ማለት ነው፣

ክርስቶስ የቤተክርስቲያን መሠረት ነው ተብሏል፡፡ ጴጥሮስና ሐዋሪያቱ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ከመሰከሩ ቦኋላ ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን በዚያ እውነት ወይም በዚያ ዓለት ላይ እንደሚሠራ ተናግሯል (ማቴዎስ 16፡ 18)፣ ጳውሎስም እንዲህ ብሏል “ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሰርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው” (1ኛ ቆሮንቶስ 3፡11) ጴጥሮስም ክርስቶስ የማዕዘን ራስ የዕንቅፋትም ድንጋይ የማሰናኪያም ዓለት ሆነ ብሏል (1ኛ ጴጥሮስ 2፡1_8)

ሁለቱም ቤተክርስቲያንና አባላቱ የሚለብሱት ስም የክርስቶስ ስም ነው፣

መዳን በሌላ በማንም የለምና (የሐዋሪያት ሥራ 4፡12) በዳኑት ሰዎች የተዋቀሩት የቤተክርስቲያን ጉባኤዎች የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ተብለዋል (ሮሜ 16፡ 16)፣ እንዲሁም የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ተብላለች (የሐዋሪያት ሥራ 20፡28)፣ እናም ጌታን የሚያከብሩ ገላጭ ስሞች ናቸው፣ እንዲሁም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላትም ክርስቲያን ተብለዋል (የሐዋሪያት ሥራ 11፡26፣ የሐዋሪያት ሥራ 26፡28፣ 1ኛ ጴጥሮስ 4፡16)

ወደ ቤተክርስቲያን መግቢያ በሐዋሪያት ሥራ ውስጥ ተደጋግሞ ተገልጿል፣ የተለያዩ የመለወጥ ምክንያቶችን ስናነብ፣ ሰዎች ወንጌልን ሲሰሙ በእግዚአብሄርና በክርስቶስ አምነው፣ ንሠሀ ገብተው፣ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መስክረው ለኃጥያታቸውም ሥርየት ተጠመቁ (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ 2፡47)

እንደ ክርስቲያኖች፣ ጌታን ያመልካሉ፣ ታማኝ ሆነው ክርስቶስ አንድ ቀን ወደ ቤተክርስቲያኑ እንደሚመለስና ቃል በመግባት ተናግሯል (ዮሐንስ 14፡ 1_3፣ ኤፌሶን 5፡27፣ 1 ኛ ተሰሎንቄ 4፡15_18)

ስለዚህ ቤተክርስቲያን በቅዱሣት መፃሐፍት ውስጥ በግልፅ ተለይቷል። አሁን ዛሬ የጌታን ቤተክርስቲያን እንዴት ማግኘት ይቻላል? እነዚህን ተመሣሣይ የመለያ ምልክቶች በመጠቀም፣ ቤተክርስቲያን የጌታ ነኝ ልትል ትችላለች፣ ነገር ግን እነዚህ ምልክቶች ከሌሊት ግን አይደለም፣ አንተ ባለህበት የቤተክርስቲያን ጉባኤ ከሌለ የእግዚአብሄርን ቃል በማስተማር። ሌሎችን በመለወጥ እና ከዚያ በመቀጠል መጀመር ትችላለህ።

## ትምህርት 6

## አንተ ለጌታ አስፈላጊ ነህ

በዚህ ጥናት ውስጥ የእኛ ዓላማ እንደገና አንተ ባለህበት አከባቢ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንዴት መጀመር እንደምትችል መወያየት ይሆናል። በቤተክርስቲያኒቱ ዙሪያ ያለውን አለመግባባት ማጥራት ከቻልን ሁሉም ነገር በቦታው ላይ እንደሚሆን እናምናለን። ቤተክርስቲያንን ከልክ በላይ ማጉላት አንፈልግም ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያቀርበው በተመሣሣይም የጌታ ቤተክርስቲያን በሚገኝበት አከባቢ ከሌለህ እና ቤተክርስቲያኒቱ አባል ከሆንክ ወይም አባል ለመሆን ከፈለግክ በመጀመሪያ ቤተክርስቲያንን ለመጀመር መሣሪያ እንድትሆን ልናበረታታህ እንወዳለን

በዚህ ርዕስ ላይ ወይም በዚህ ትምህርት ላይ ለጌታ አስፈላጊ እንደሆንክ ልናሰምርበት እንፈልጋለን፣

እግዚአብሄር ሰውን ፈጠረ ፣ በራሱ አምሣል ፈጠረው (ዘፍጥረት 1፡26፣ 27፣ 2፡7) ይህም መንፈስን፣ ነፍስን ሰጠው፣ የማትሞትንም ነፍስ (ማቴዎስ 16፡26)። ሰውን ከኃጥያቱ ለማዳን ልጁን በጭካኔ በመስቀል ላይ እንዲሞት

ሊሰጠን ፈቃደኛ ሆነ (ዮሐንስ 15፡13) ይህ ማለት እያንዳንዱ ሰው በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ነው፣ አንተም አስፈላጊ ነህ ማለት ነው።

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ሰዎች ተመልከት፣ ጌታ እንዲጠቀምባቸው ስለፈቀዱ ታላቅ ሰዎች ሊሆኑ ችለዋል። ስለ ኖህ፣ አብረሃም፣ ሙሴ፣ ዳናኤል፣ ኢሳያስ፣ ኤሊያስ፣ ኤልሳዕ፣ መጥመቁ ዮሐንስ እና እያንዳንዳቸው ሐዋሪያቶችና ሌሎች ብዙዎችን አስብ።

እንዲሁም ሐዋሪያው ጳውሎስን እና ጌታ ህይወቱን ሲቆጣጠር ምን ማድረግ እንደቻለ አስብ፣ የጀመረው የክርስቶስና የክርስቲያኖች ጠላት ሆኖ ነበር። አንዴ ከተለወጠ ቦኃላ ግን ጠንክሮ ሰርቷል፣ እና ምንም ጥርጥር አልነበረውም፣ በጌታ ላይ ከሠራው ጥፋት በእጥፍ ካሣ ከፍሏል የሚሲዮናዊ ጉዞዎቹን እና ወደ ክርስቶስ የለወጣቸውን ሰዎች ሁሉ አስብ፣ በሥራው እና በተለወጡት ሥራ ከሌሎቹ ሐዋሪያት እና ከተመለሱት ጋር ከሠላሣ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ወንጌል ወደ ዓለም ሁሉ የወሰደ ሰው ነው። ፊላጎቱ፣ ራስን መወሰኑ እና ቁርጠኝነት ሲኖር ጥቂት ሰዎች ወይም አንድ ሰው እንኳን ሊታመን የማይችል መልካም ነገርን ሊያከናውን ይችላል

በሐዋሪያት ሥራ 10 ላይ ከአንድ ሰው እና ከቤተሰቡ ጋር ያለውን አስፈላጊነት ተመልከት ቆርኔሌዎስ በሮማዊያን ጦር ውስጥ ነበር፣ ነገር ግን ጥሩ ሰው ነበር፣ እሱ ኃይማኖተኛ ሰው ነበር። እንዲሁም ሁልጊዜ የሚፀልይ እና ድሆችን ምፅዋዕት የመሰጥ ነበር፣ ታሪኩ ሲቀጥል እግዚአብሄር ጴጥሮስን ወደ ቆርኔሌዎስ እና ቤተሰቡ ላከላቸው፣ ይላል "ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ፣ ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በአህዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለፈሰሰ ተገረሙ። በልሣኖች ሲናገሩ እግዚአብሄርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና። በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ ፦ እነዚህ እንደእኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ውኃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚችል ማን ነው? አለ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው፣ ከዚህ ቦኃላ ጥቂት ቀን እንዲቀመጥ ለመኑት" (የሐዋሪያት ሥራ 10፡44_48)

በቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ የተለወጡበት ዋናው ምክንያት አህዛብ መሆናቸው እና የመጀመሪያዎቹ አህዛብ መሆናቸው ነው፣ ይህ ውይይት በዚያ ቀን ለክርስቶስ ጉዳይ ምን ትርጉም እንዳለው አስብ። የመጀመሪያዎቹ አህዛብ የተለወጡ በመሆናቸው፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስማቸው አህዛብ ክርስቲያን ለመሆናቸው እና በዚህ ስለመጠራታቸው ምንም ጥርጥር የለውም ። ይህ ብቻ ሳይሆን የነርሱን ፈለግ የተከተሉትን አህዛብ ሁሉ አስብ፣ ዛሬም አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ከአህዛብ የመጡ ናቸው።

አሁን ወደ ታዘዘው ኢትዮጲያዊው ሰው እንመለስ፣ ምንም እንኳን ፊልጶስ በሰማሪያ እሠራ የነበረና ብዙ ስኬቶችን ያስመዘገበ ቢሆንም ዘገባው

ሲናገር “የጌታም መልዓክ ፊልጶስን ፦ ተነስተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደ ሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው፣ ተነስቶም ሄደ፣ እነሆም ህንደኬ የተባለች የኢትዮጲያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘቧም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጲያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፣ ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳያስን መፅሐፍ ያነብ ነበር። መንፈስም ፊልጶስን ወደዚህ ሰረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው፣ ፊልጶስም ሮጦ የነቢዩን የኢሳያስን መፅሐፍ ሲያነብ ሰማና `በውኑ የምታነበውን ታስተውላለህን?` አለው። እርሱም `የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?” አለው፣ ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ፊልጶስን ለመነው፣ ያነበውም የነበረ የመፅሐፉ ክፍል ይህ ነበረ  እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፣ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፣ ህይወቱ ከምድር ተወግዳለችና ትውልዱንስ ማን ይናገራል? ጃንደረባውም ለፍልጶስ መልሶ “ እባክህ ነቢዩ ስለማን ይናገራል? ስለራሱ ነውን? ወይስ ስለሌላ? አለው። ፊልጶስም አፉን ከፈተ፣ ከዚህም መፅሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለጥ በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውኃ ደረሱ፣ ጃንደረባውም፣ እነሆ ውኃ፣ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድርነው? አለው። ፊልጶስም በፍፁም ልብህ ብታምን፣ ተፈቅዶአል አለው። መልሶም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ አለ። ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፣ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ፣ አጠመቀውም፣ ከውኃውም ከወጡ ቦኃላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው፣ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም፣ ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና። “ (የሐዋሪያት ሥራ 8፡26_39)።

ከዚህ ሰው የደህንነት ታሪክ የምናነበው ብዙ ታላላቅ ትምህርቶች ማግኘት ይቻላል፣ ይህ ሰው ለጌታ ብዙ አስፈላጊ ስለነበረ የጌታ መልአክ ፊልጶስ ኢትዮጲያዊውን እንዲያስተምር አደረገው፣ እርሱ ለጌታ እንዲታዘዝ እና በትክክለኛው መንገድ እንዲያመልክ ነበር፣ አሁን ይህ ኢትዮጲያዊ ሰው ማን ነበር? ከኢትዮጵያ እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ሊሰግድ የሄደ ኃይማኖተኛ ነው። ይህ ሰው ትሁት፣ ቅን እና ቁርጠኝነት ያለው ሰው መሆኑን እናያለን፣ እሱ ደግሞ የንግሥት ህንዴኬ ገንዘብ ያዥ የነበረ ታላቅ ባለሥልጣን ሰው ነበር። አሁን ለእውነት በመታዘዝ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ይህ ሰው በሀገሩ መሪዎች፣ በቤተሰቡ አባላት፣ ምን ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል ብለህ ታስባለህ፣ በአጠቃላይ በሚያውቁት ህዝብ ዘንድስ? እግዚአብሄር የእርሱን ዓላማ ለማስፋፋት ትልቅ አይቷል ብለን መደምደም አለብን፣ እናም ይህ ኢትዮጵያዊ ጌታን እንዳስደሰተ ምንም ጥርጥር የለኝም

አሁን አንተ ማን ነህ? ምንም አይደለሁም ብለህ ታስብ ይሆናል፣ ነገር ግን እንደ ብቸኛ ግለሰብ ትልቅ ቦታ የማትመስል ሆኖ ሳለ፣ ጌታን ከታዘዝክ እና

እራስህን ለእርሱ ከሰጠህ እሱ አንድ ሙሉ ሰው ሊያደርግህ ይችላል። ምናልባት ወጣት፣ ሽማግሌ፣ ሴት፣ ወንድ፣ ሀብታም፣ ደሀ፣ የተማርክ፣ ያልተማርክ፣ ወይም ሌላ ልትሆን ትችላለሕ ለጌታ ምንም ይሁን ምን ጌታ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ተራ ወንዶች እና ሴቶችን እንዴት እንስቶ ወስዷቸው ታላላቅ አገልጋዮች እንዳደረጋቸው ተመልከት፣ ታዲያ ያንን ካደረገ በአንተ ላይስ የማያደርገው ለምንድነው?

እኔ እያልኩ ያለሁት ይህ ነው። ጌታን የምትታዘዝ ከሆነ እና የእሱ ቤተክርስቲያን አባል ከሆንክ እና እራስህን ለእርሱ ከሰጠህ ማለትም ለእርሱ የምፀራ ከሆነ፣ ሰባኪ፣ አስተማሪ፣ ሚሲዮናዊ፣ ወይም ምናልባት በሌላም እሱን ማገልገል ትችላለሕ በዓላማው መስፋፋት ውስጥ ለእሱ ብዙ እንድፀራ የሚያስችል አቅም ይሰጥሀል፣ በጥናቱ ላይ እያሳሰብን እንዳለን፣ ቤተክርስቲያን በሌለበት ቦታ ላይ ከሆንክ ሥራውን ለመጀመር እዚያው ግንባር ቀደም መሆን ትችላለህ፣ አዎን ያንን ማድረግ ትችላለሕ ጌታ ካንተ ጋር ለመሆንና ጥረትህን ሊባርክ ቃል ገብቷል። እባክህን እነዚህን ነገሮች አስብ እና የእግዚአብሄር ፈቃድ በህይወትህ እንዲፈፀም ፀልይ።

## ትምህርት 7

## ባህበት ቤተክርስቲያን ለምን ያስፈልጋል

ይህ ሙሉ ተከታታይ ትምህርት አንተ ባለህበት የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንዴት መጀመር እንደሚቻል ጥያቄን ያመለክታል። ምናልባት አንተ የጌታ ቤተክርስቲያን አባል እና የአንዳንድ አጥቢያ ጉባኤ አባል ልትሆን ትችላለህ፣ በዚህ ሁኔታ ደስተኞች ነን፣ ነገር ግን ገና ክርስቲያን ካልሆንክ እና ባለህበት የቤተክርስቲያን ጉባኤ ከሌለ በእነዚህ ጥናቶች እንድትበረታታ፣ እንድትድን ጌታን እንድትታዘዝ እፀልያለሁ፣ ክርስቶስ ወደመሰረታት ቤተክርስቲያን እግዚአብሄር ይጨምርሃል። ምናልባት አንተ በምትኖርበት ቦታ የሚሰበሰብ አንድም የቤተክርስቲያን ጉባኤ ላይኖር ይችላል፣ ያ ከሆነ በማህበረሰባችሁ ውስጥ ቤተክርስቲያን እንድትጀምር የሚያስችልህን መረጃ ልንሰጥህ እንፈልጋለን

በመጀመሪያ አንተ ባልህበት ቤተክርስቲያን ለምን እንደሚያስፈልግ ልንነግርህ እንፈልጋለን ። እየተነጋገርን ያለነው ስለ ሌላ ቤተክርስቲያን አይደለም፣ ስለአንድ ዓይነት ቤተእምነት አይደለም። እንደእውነቱ ከሆነ አንተ በምትኖርበት ቦታ ብዙ ቤተ እምነቶች ሊኖሩ ይችላሉ ነገር ግን የምንናገረው ስለ ሰው ሰራሽ አቢያተ ክርስቲያናት አይደለም። ይልቁንም የምንናገረው በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ምናነበው ቤተክርስቲያን፣ የጌታ ስለሆነች ቤተክርስቲያን ነው፣ ክርስቶስ ስለሞተላት እርሱ አዳኟ ስለሆናት፣ እርሱ ራስ ስለሆናት የእርሱን ማለትም የክርስቶስን ስም ስለለበሰቻው ቤተክርስቲያን ነው የምናወራው።

የአንድ ኃይማኖት ድርጅት አባል መሆን እና አሁንም የጠፋ መሆኑን

ታውቃለህ? በሰው ሰራሽ አቢያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉት የአንዳቸውም አባል ሳትሆኑ መዳን እንደሚችሉ ይቀበላሉ፣ ለዛም ነው ጌታን ለመታዘዝ ለሚፈልጉ ለሌሎችም ስትል የጌታ ቤተክርስቲያን በማህረሰብህ ውስጥ መሆን አለበት የተባለው።

የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አስፈላጊ ናት፣ አዳኝ አይደለችም ነገር ግን ሰው ለመዳን የቤተክርስቲያኑ አካል መሆን አለበት፣ እንደእውነት ከሆነ አንድ ሰው ከዳነ፣ በሂደቱ ውስጥ ጌታ ቤተክርስቲያኔ ብሎ በጠራው የዳኑ አካል ላይ ይጨምረዋል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47) የሐዋሪያው ጳውሎስን ቃል ስማ “ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያኑ ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና” (ኤፌሶን 5፡23) አስተውል ክርስቶስ የአካሉ አዳኝ ነው እያለ ነው። ለመሆኑ አካል ምንድነው? እንደ ኤፌሶን 1፡22፣23 እና ቆላሲያስ 1፡18፣ አካል ማለት ቤተክርስቲያን ናት ስለዚህ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን አዳኝ ነው፣ ለመሆኑ ስንት አካል ወይም ቤተክርስቲያን አሉ? እዚህም ጋ ጳውሎስ ቤተክርስቲያንም ወይም አካል አንድ ብቻ ናት ይለናል (ኤፌሶን 4፡4) ነገር ግን አካል ቤተክርስቲያን ከሆነ እና አንድ አካል ካለ ይህ ማለት አንድ ቤተክርስቲያን አለ ማለት ነው፣ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን ትርጉም ይሰጣል፣ እናም አንተ ባለህበት ቦታ ላይ መገኘት ተገቢ ነው። እናም አንተ ባለህበት ቦታ ያ አንተ እና ሌሎችም አባላት መሆን ይችላሉ፣ ይህም እግዚአብሄርን ደስ ያሰኘዋል

ቤተክርስቲያን እንዲኖር የሚያስፈልግበት ሌላው ምክንያት አንተ እና ሌሎች የቤተክርስቲያን አባላት የምሰግዱበት ጉባኤ ለማቅረብ ነው። በአከባቢህ ጉባኤ ከሌለ ከሌሎች የኃይማኖት ቡድኖች ጋር አምልኮ ለመጀመር ደካማ ልትሆን ትችላለህ፣ ግን ይህ በእርግጠኝነት ለችግሩ መፍትሔ ሊሆን አይችልም።

ከሌላ ቤተክርስቲያን ጋር ለምን መስገድ እንደማትችል ላብራራ። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ከሆንክ ያ ማለት የአንዳንድ ቤተ እምነት ቡድን አባል አይደለህም ማለት ነው። የጌታ ቤተክርስቲያን ከእነርሱ ትለያለች የጌታ በመሆኗ የክርስቶስን ስም ለብሣለች አምልኮቷና ትምህርቷም የተለያዩ ናቸው። የጌታ ካልሆነ ቤተክርስቲያን ጋር እንዴት ማምለክ ትችላለህ ? የጌታ ያልሆኑ ቤተ እምነት ሲዘምሩ ሜካኒካል ሙዚቃ ስለሚጠቀሙ ከእነሱ ጋር መዘመር አትችልም። ጳውሎስ በልባችን መዘመርን እንዳለብን ተናግሯል (ኤፌሶን 5፡19) የዳኑ ሰዎች ስላልሆኑ ከእነሱ ጋር መፀለይ አትችልም። ጌታ ህዝቡን ለመስማት ቃል ገብቷል፣ ነገር ግን ኃጥያተኛውን አይደለም (ዮሐንስ 9፡31)። ከእነሱ ጋር ማጥናት አትችልም ምክንያቱም እነሱ የሚተዳደሩት በሰው ትምህርት ነው። ከእነርሱ ጋር የጌታ እራት ፣ እነሱ ግን እንደፈለጉ በወር በሁለት ወር በ6 ወር በዓመት ይወስዳሉ። እንዲሁም ገንዘብህን ለእነሱ ማዋጣት አትችልም ምክንያቱም እነሱ የሚያዋጡት የሐሰት ትምህርት ለመደገፍ ያገለግላልና።

በስህተታቸው እንዲቀጥሉ ልታበረታታቸው ስለማትችል እነሱን መገናኘት አትችልም። ከሌላ ቤተክርስቲያን ጋር ማምለክ የማትችልበት ምክንያት እነዚህ ናቸው።

እንደገና ቤተክርስቲያን በሌለበት ቦታ ከሆንክ ሌላው አደጋ ኃይማኖትን ሙሉ በሙሉ ልታቋርጥ ትችላለሕ ቤተ ክርስቲያን ስለሌለቸ እና ከሌሎቸ የኃይማኖት ቡድኖቸ ጋር ማምለክ ስለማትቸል በምንም መንገድ ትጨነቃለህ? ለችግርህ ግን ይህ መፍትሔ አይሆንም፣ ይልቁንስ ቸግሩን ለመፍታት ማድረግ የምትችለው ነገር እንዳለ መገንዘብ አለብህ።

በህይወትህ ሁሉ በቤትህ ውስጥ ኖረሃል፣ የመፀሐፍ ቅዱስ የመላላክ ትምህርት ኮርስ ወስደሃል ወይም በራድዮ ወንጌል ሲሰበክ ሰምተህ ጌታን ከታዘዝክ አንተ ብቸኛ ክርስቲያን መሆንህ ይታወቃል፣ ወይም ቤተክርስቲያን ካለበት ቦታ ወደ አሁን ያለህበት ተዛውረህ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብትሆንም እዚያ ስለመሆንህ እግዚአብሄርን ማመስገን አለብህ፣ ይህም ባለህበት ቤተክርስቲያን እንድትመሰርት ዕድል ተሰጥቶህ ነውና። አንተ ግን "የጌታን ቤተክርስቲያን ለመጀመር እኔ ማን ነኝ" ልትል ትችላለህ፣ ብዙ ሰበቦችን ማግኘት እንደምትችል ምንም ጥርጥር የለውም፣ ግን እውነታው አንተ እንድታደረገው ከወሰንክ መደረግ ያለበትን ማንኛውንም ነገር ማድረግ ትችላለህ

ቤተ ክርስቲያን በአከባቢህ መኖር አለባት ምክንያቱም እዚያ ላሉት ሁሉ ለመዳን ምክንያት ይሆናልና። አንተ እና ቤተክርስቲያን ክርስቶስን ትወክላላችሁ። ለሰዎች በእውነት እና በስህተት መካከል ያለውን ልዩነት አይተው እንዲመርጡ ዕድል በመስጠት የእግዚአብሄርን እውነት ትወክላላችሁና፣ ቤተክርስቲያን ሌሎች እውነትን እንዲያውቁ ትጠብቃለች፣ የአከባቢው ሰዎች የእግዚአብሄርን ፈቃድ ላያውቁ ይችላሉ፣ ቤተክርስቲያን ይህንን እውነት፣ ይህንን ብርሃን ትወክላለች ታስተምራለችም፣ የለእርሱ ግን ሁሉ ጨለማ ነው።

ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሄርን ማምለክ ብቻ ሳይሆን የክርስቶስን ወንጌል በመስበክና በማስተማር ንቁ ተሳትፎ ማድረግ አለባት፣ ይህ በአምልኮ ውስጥ ሊከናወን ይቻላል ነገር ግን በስብሰባ፣ በግል ሥራ፣ በሥነ ፅሑፍ ወዘተ ሊደረግ ይቻላል፣ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለመስበክ ብዙ መንገዶች፣ ግን ግምባር ቀደም መሆን የቤተክርስቲያን ጉዳይ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሥራ ለመሥራት ምን ያህል ትልቅ መሆን አለባት? ቅዱሣት መፅሐፍት የኢየሱስን ቃል እንዲህ ያስነብበናል "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና" ይላል (ማቴዎስ 18፡ 20)፣ ይህ ማለት የአባላትን ቁጥር በተመለከተ ከራስህ እና ከሌላ አባል ጋር ጉባኤ መጀመር ትችላለህ ከዚያ ወደ ማንኛውም መጠን ማደግ ትችላለህ። የጌታ ቤተክርስቲያን በዳኑት ሰዎች የተዋቀረች መሆኗን አስታውስ፣ እናም ሰዎች

ጌታን ሲታዘዙ እሱ ያድናቸዋል፣ እሱ ከሌሎች የዳኑት ጋር ይጨምራቸዋል፣ በአከባቢው ያለው ጉባኤ የሚጀምረው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አባላትን በመሰብሰብ ለአምልኮ እና ለጌታ በጋራ ለመሥራት እንደሚሰበሰቡ ይስማማሉ፣ በተስማሙበት መንገድ እያደጉም ይሄዳሉ።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በመባል ትታወቃለች፣ ወይም በሌላ አነጋገር በቅዱሣት መፅሐፍት ውስጥ እንደተገለፀው የቅዱሣት መፅሐፍት ስም ትለብሣለች፣ በአምልኮው፣ በትምህርቱ፣ በሥራው እና በሚሠራው ሁሉ በእግዚአብሄር ቃል መሠረት ትመራለጭ ተልዕኮዋም የክርስቶስን ጉዳይ ማስፋፋትና ጌታን ማክበር ብቻ ይሆናል።

ክርስቲያን እና የጌታ ቤተክርስቲያን አባል መሆን ምንኛ አስደሣች ነው፣ የትልቅ አጥቢያ ምዕመናን አባልም ሆኑ ቤተክርስቲያኒቱ በሌለችበት ቦታ ኖራችሁ፣ እውነታው ግን ቤተክርስቲያን እንድታድግ ወይም ባለህበት ጉባኤ እንዲመሰረት አስተዋፅኦ ለማድረግ ትልቅ ሚና መጫወት ትችላለህ።

## ትምህርት 8

## የጌታን ቤተክርስቲያን እንዴት መጀመር እንደሚቻል

ተከታታይ ጥናቶቻችን ያተኮሩበት አንተ ባለህበት የክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንዴት መጀመር በሚለው መሪ ሀሳብ ዙሪያ ሲሆን ይህም በከተማህ፣ በመንደርህ፣ ወይም ባለህበት ቦታ የመውጣት አስፈላጊነት ላይ ያተኩራል። ክርስቲያን ከሆንክ ባለህበት የቤተክርስቲያንን ጉባኤ በመጀመር ላይ መሳተፍ እንደምትችል እናሳስባለን።

በዚህ ትምህርት የጌታን ቤተ ክርስቲያን እንዴት መጀመር እንዳለብን መነጋገር እንፈልጋለን። ቀደም ባሉት ትምህርቶች የመዳን አስፈላጊነትን፣ ጌታን እንዴት መታዘዝ እንዳለብን፣ ቤተክርስቲያንን እንዴት መለየት እንደሚችላል፣ ለምን ባለህበት ቤተክርስቲያን እንደሚያስፈልግ ወዘተ ተወያይተናል።

ወደ ፊት ከመሄዳችን በፊት ደግሜ እላለሁ፣ እያወራን ያለነው ቤተክርስቲያን ስለ መጀመር ብቻ ነው፣ ይህም ገና ስላልነበረች ነው። እዚያ ከነበረ ካለ መቀላቀል ትችላለህ እንጂ መከፋፈል አያስፈልግም፣ ነገር ግን እራሱን የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ብሎ የሚጠራው ቡድን ምናልባት ትምህርቱን፣ አገልግሎቱን፣ አምልኮውን የለበሰውን ስም ማጣራት እና እውነታውን ማየት አለብህ የጌታ መሆን አለመሆኗን መለየት ግድ ይላል። አንድ ሰው “ግን ምን ልዩነት አለው?” ሊል ይችላል ያለው ልዩነት በትክክል እና ትክክል ባልሆነው መካከል ያለው ልዩነት ነው፣ በእርግጥ ጌታ የሚፈልገውን ያውቃል፣ ጌታ የሚፈልገው ያልሆነ ሁሉ ደግሞ ስህተት ነው።

በአንዳንድ ከተሞች ለጌታ የሚታዘዙ በመኖራቸውና በአቅራቢያቸው ካለ የቤተክርስቲያን ምዕመናን ጋር ከማምለክ ይልቅ ቢቤታቸው ወይም

በተከራዩት ቤት ሥራ የሚጀምሩ በመሆናቸው ብዙ ጉባኤዎች አሉን። አንዳንድ ጊዜ ሁለት ወይም ሦስት ጉባኤዎች በአንድ ጎዳና ላይ ይሰበሰባሉ። ይህ መጥፎ ነው። መጥፎ ነው ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ በወንድማማቾች መካከል እንኳ መከፋፈልን ይወክላል፣ ተባብረው የተሻለ ሥራ ለመሥራት እርስ በእርስ መረዳዳትና ማበረታታት ሲችሉ በህይወት ለመኖር የሚታገሉ ብዙ ትናንሽ ጉባኤዎች ሲኖሩም መጥፎ ነው።

ስለዚህ እየተነጋገርን ያለነው በአቅራቢያው አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጉባኤ ስላለበት ጉባኤ ስለ መጀመር አይደለም። ይልቁንም የጌታ ቤተክርስቲያን በሌለበት ከተማ ወይም አከባቢ እንዲጀመር እያበረታታነው ነው። ምናልባት የክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንዴት መጀመር ወይም መምስረት እንደሚቻል ይሆናል። እርግጥ ነው የምንናገረው ስለ ቤተክርስቲያን መመስረት ስንል አዲስ ቤተክርስቲያን ወይም የራሳችን ቤተክርስቲያን ማለት አይደለም ምክንያቱም ክርስቶስ አንዴ የራሱን ቤተክርስቲያን እሠራለሁ ብሏልና (ማቴዎስ 16፡ 18)፣ ይህም በመጀመሪያ በኢየሩሳሌም የተቋቋመው ወንጌል ሲሰበክና ሦስት ሺህ የሚያህሉ ነፍሳት ታዘው ድነዋል፣ እናም ጌታ እነዚህን የዳኑ ነፍሣትን ወደ ቤተክርስቲያኑ ጨምሯቸዋል (የሐዋሪያት ሥራ 2) ከዚያ ቦኃላ ወንጌል በተሰበከበት ሁሉ የሚታዘዙትም ነበሩ፣ የጌታ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ተጀምረ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእዚአብሄር ቃል በተሰበከበት እና ሰዎች በሚታዘዙበት ቦታ ሁሉ ቤተክርስቲያን በዚያ ቦታ ተፈጠረጭ ዛሬም ተመሣሣይ ነው፣ እና አንተ የምትኖርበት ቤተክርስቲያን ስለመጀመር ስንናገር የምንናገረው ይህ ነው፣ የጌታ ቤተክርስቲያን በአንድ ቦታ ልትኖር የምትችለው አንተ እና ሌሎች ጌታን እንደምትታዘዙ ብቻ ነው። ይህንን ያህል ቀላል ነው።

ስለዚህ ሁኔታህ ይህ ነው፣ አንተ ክርስቲያን ነህ ጌታንም ማምለክ ትፈልጋለሕ የአጥቢያ ጉባኤ አባል መሆን ትፈልጋለህ ነገር ግን በከተማህ በአከባቢህ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የለም። ምን ማድረግ ትችላለህ? በመጀመሪያ ደረጃ ብቻህን ብትሆንም በያንዳንዱ የጌታ ቀን በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ማለትም እሁድ እግዚአብሄርን ለማምለክ ቅዱሣት መፅሐፍትን ለማንበብ፣ ለመፀለይ ጊዜ እንድትመድብ እመክርሃለሁ፣ መንፈሳዊ መዝሙሮችን ለመዘመር ጌታ ህዝቡ እንዲያስቡት ስለሚፈልግ በየሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን የጌታ እራት እንዲትበላ፣ ቂጣ እንጀራ ጋግርና ጥቂት የወይን ጭማቂ ውሰድ እናም 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡23_29 መንፈሳዊ ምሣሌን መከተል አለብህ፣ የክርስቶስን ሥጋ ለማሰብ ከቂጣው መካፈል፣ የወይኑም ፍሬ የክርስቶስን ደም ለማሰብ ነው። ከዚያም ከደመወዝህ ላይ መዋጮ ለይተህ ለጌታ ሥራ ልትጠቀምበት ትችላለህ፣ ምናልባት መፅሐፍ ቅዱሶችን እና አዲስ ኪዳኖችን በመግዛት ለሌሎች ለማካፈል፣ ለጌታ እራት ዕቃዎችን መግዛት፣ የተቸገሩትን ለመርዳት ወዘተ። አንድ ሰው ብቻ ብትሆንም ይህ ለአንተ የሚያበረታታ ከመሆኑም በላይ ከአንተ

ጋር ለአምልኮ ለመካፈል ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን እስክታገኝ ድረስ መቀጠል የሚያስፈልግህን ጥንካሬ ይሰጥሃል።

በመቀጠል እኔ አንተን ብሆን ኖሮ ቤተሰሞቼ እና ጓደኞቼ አብረውኝ ለአምልኮ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ እሞክር ነበር። እስከዚያው ድረስ እነርሱን ወደ እውነት ለማምጣት መነጋገር አብሮ ማጥናትን አስባለሁኝ። ከእነሱ ጋር ጊዜ እወስዳለሁ፣ ነገር ግን አንድ ሰው ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለበት ላሳያቸው እሞክራለሁ ፣ ከዚያም መፅሐፍ ቅዱስ ስለጌታ ቤተክርስቲያን የሚያስተምረውን አሳያቸዋለሁ፣ ምናልባት ከጊዜ ቦኃላ አንድ ወይም ተጨማሪ ጌታን ለመታዘዝ ይወስኑ ይሆናል በጌታ በማመን እና ከኃጥያታቸው ንሠሃ መግባት ቀጣዩ ነገር ማድረግ ያለባቸው ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መመስከር እንደሆነ አስረዳቸዋለሁኝ፣ ለዚህ የሐዋሪያት ሥራ 8፡26_39 ከኢትዮጵያ የመጣውን ሰው ንግግር ታሪክ ምሣሌ ውሰድ አንብብ፣ ከዚያም ጌታን ለመታዘዝ የሚፈልጉትን “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ታምናላችሁ?” በእነሱ ምስክርነት ወደ ወንዝ ወይም ወደ ውኃ ለማጥለቅ በቂ ውኃ ወዳለበት ቦታ ወስዳችሁ አጥምቋቸው። ከጥምቀት በፊት አንተ በኢየሱስ ሥልጣን ለኃጥያታቸው ሥርየት በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም ታጠምቃቸዋለህ (ማቴዎስ 28፡18_20)። ግለሰቡን መውሰድ እና በውኃ ውስጥ ማስገባት ትችላለህ፣ ውኃው ሙሉ በሙሉ እንዲሸፍኗቸው እርግጠኛ ሁን፣ ምክንያቱም ጥምቀት የክርስቶስን መቃብር የሚያሳይ እና ከመቀበሩ ጋር የሚመሳሰል ነውና (ሮሜ 6፡3፣4፣ ቆላስያስ 2፡12)

ለጌታ ለመታዘዝ አንድ ወይም ብዙ ሲኖርህ በከተማህ ውስጥ ያለው የጌታ ቤተክርስቲያን ማህበር ተጀመረ ማለት ነው፣ በከተማህ በሚገኘው የጌታ ቤተክርስቲያን ለአምልኮ በቤትህ ውስጥ መገናኘት ትችላለህ፣ በአንዳንድ የህዝብ አዳራሽ ውስጥ ለመገናኘት ማመቻቸት ትችላለህ። ቤተሰብህን፣ ጓደኞችህን እንዲመጡ መጋበዝ ትችላለህ። የመሰብሰቢያ ቦታህን ማስተዋወቅ እና ህዝቡ እንዲመጣ ማበረታታት ትችላለህ ፣ በዚያን ጊዜ ሌሎችን ስለትምህርት፣ፀሎትን መምራት፣ የጌታን ማዕድ መጠበቅ ማደል፣ ዝማሬ መምራት ወዘተ በተመለከተ ማን ምን እንደሚያደርግ ትወስናለህ። ህዝባዊ ተሳትፎ ለማድረግ፣ ነገር ግን ለጌታ እራት ቂጣውን እና የወይኑን ጭማቂ ለማዘጋጀት ሴቶች ይሳተፋሉ፣ ከዚያ ውጪ በመድረክ ላይ አያገለግሉም፣ በተጨማሪም ልጆችን ማስተማር ወይም መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎች ሴቶች ጋር መማማር ይችላሉ።

ስለስብከት ወይም የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት የምንኖረው በአስደናቂ ጊዜ ውስጥ ነው፣ በዚህ ጊዜ ማንም ለመስበክ ዝግጁ ካልሆነ አንዳንድ ጥቅሶችን ሊያነብና ሊዘጋጅ ይችላል፣ እንዲሁም የወንጌል ትራክት ወይም ርዕስ በቦታው ለሚገኙት ማንበብ ይቻላ። ከዚህ ባለፈ ስብከትን በተመለከተ ብትጠይቁን ምናልባት ልንልክልዎት እንችላለን።

ለእኛም ሆነ ለምናውቋቸው ሌሎች ክርስቲያኖች ብትፅፍ ምናልባት ሰባኪው አንዳንድ የወንጌል ስብሰባዎችን ለመምራት ወደ አንተ እንዲመጣ አንዳንድ ጊዜ ሊረዳህ ይችላል።

ወጣት ክርስቲያን ወይም ሴት ከሆንክ (ሽ) ጉባኤ ለመጀመር የበለጠ ሊከብድህ ይችላል ነገር ግን በጉባኤው ላይ የምፀራ ከሆነ ሊረዳህ የሚችል እና ቤተሰብህን አባላትና ጓደኞችህን ሊያስተምር የሚፈቅድ ወንድም ታገኝ ይሆናልና መፃፃፍን አትተው በእርግጠኝነት አንድ ነገር ማድረግ ይቻላል፣ ትንሽ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፣ ግን በእርግጠኝነት ይሳካልሃል፣

እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ የሚመስለውን ያህል ውስብስብ እና አስቸጋሪ አይደለም የሚያስፈልገው አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቁራጥ የሆኑ ክርስቲያኖች ለጌታ ወደ ሥራ እንዲሄዱ የፈቀዱ መኖር ብቻ ያስፈልጋል፣ እናም የቤተክርስቲያን ጅማሬና እድገቷ ይከተላል።

## ትምህርት 9
## እንዴት ማጥመቅ እንደሚቻል

ባለህበት ቦታ የክርስቶስን ቤተክርስቲያንን እንዴት መጀመር እንደሚቻል በሚል መሪ ሀሳብ ላይ የምናቀርበው ተከታታይ ትምህርታችን ይቀጥላል። ቤተክርስቲያኑ በሌለበት ቦታ ከሆንክ ቤተክርስቲያንን እንድትጀምር ልናበረታታህ እና ልንረዳህ እንፈልጋለን። በእርግጥ አንተ እራስህ አባል ካልሆንክ መጀመሪያ ማድረግ ያለብህ ነገር ለጌታ መታዘዝና አባል መሆን አለብህ፣ ከዚያም በአከባቢው ጉባኤ ለመመሥረት የሚያስችል አቅም ይኖርሃል።

በእንደዚህ ዓይነት ነገር ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ነገሮች ስናስብ ወደ ጥምቀት ጉዳይ እና በተለይም እንዴት ማጥመቅ እንደሚቻል ወደ ሚያስተምረን እንመጣለን።

በመጀመሪያ የጥምቀትን ቅዱስ ፅሑፋዊ ትርጉም እና ዓላማውን እንደገና ለማጉላት እንፈልጋለን። መፅሐፍ ቅዱስ ጥምቀት መቀበር፣ መጠመቅ እና በውኃ ውስጥ እንደሚደረግ ይነግረናል። ጳውሎስ እንዲህ ይላል “ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን ? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ህይወት እንድንመላለስ ፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን” ይላል (ሮሜ 6፡3፣4) በሌላ ለቆላስያስ ሲፅፍ “በጥምቀትም ከርርሱ ጋር ተቀብራችሁ ፣ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሄር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ” ይላል (ቆላስያስ 2፡12)። ዮሐንስ ክርስቶስን ሲያጠምቀው “ወዲያው ከውኃው ወጣ” ተብሎ ተነግሮናል።

በሐዋሪያት ሥራ 8 ላይ ፍልጶስ ከኢትዮጵያ የመጣ ሰው ሲያስተምር

እናነባለን። ወደ አንድ ውኃ ሲደርሱ ኢትዮጵያዊው መጠመቅ ይችል እንደሆነ ፈለገ። ፊልጶስ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ከልቡ ቢያምን እንደሚችል ገለፀ። ከዚያም ክርስቶስን መሰከረ ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ ፊልጶስ ጃንደረባውን አጠመቀው። ሁለቱም ከውኃ ወጡ።

ለምን ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ? ፊልጶስ በውኃ ውስጥ አጥልቆ ሊያጠምቀው ነው፣ እናም አጥልቆ አጠመቀው ጃንደረባውም ከተጠመቀ በኃላ ከውኃው ወጡ። ስለዚህ መፅሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ጥምቀት ማለት ውኃ ውስጥ ገብቶ መሸፈንን ነው ማለት ነው።

በመቀጠልም ጥምቀት ለኃጥያት ስርየት እንደሆነ ልንጠቁም እንወዳለን፣ እኛ ጥምቀት ብቻውን ያድናል እያልን ሳይሆን ጥምቀት ያድናል (ኃጥያትን ያስተሰርያል) እያልን ነው፣ እውነትን ሰምቶ በእግዚአብሄር አምኖ ከዚያም ይጠመቃል፣ ክርስቶስ ሐዋሪያትን ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ አዘዛቸው፣ ይህን በማድረግ መስበክ ነበር። “ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፣ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል” አላቸው (ማርቆስ 16፡15_16) ጴጥሮስና ሐዋሪያቶች ለብዙ ህዝቦች በሰበኩበት ጊዜ ሰዎቹ ምን እንዳድርግ ብለው ሲጠይቁ “ጴጥሮስም፣ ንሰሃ ግቡ፣ ኃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ” አላቸው (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38)። ጥምቀት አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ እና ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዲጨመር ያደርገዋል፣ በተመሣሣይ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ በገላቲያ መልዕክት ተናግሯል “በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁና፣ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችዋልና” ይላል (ገላቲያ 3፡26፣27)።

በመጨረሻም በጥምቀት አንድ ሰው የክርስቶስን ሞት፣ መቀበር እና ትንሣኤ ያሳያል። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞተ። ጌታን በመታዘዝ አንድ ሰው ለኃጥያቱ ይሞታል ወይም ከኃጥያቱ ይመለሳል። ክርስቶስ የተቀበረው በመቃብር ውስጥ ነው፣ ጌታን የሚታዘዝ በጥምቀት ውኃ ውስጥ ተቀበረ። ከዚያም ክርስቶስ ከመቃብር ተነሣ፣ በተመሣሣይም በሠማይ ላለው አብ መታዘዝ በአዲስ ህይወት ለመመላለስ ከውኃው መቃብር ይነሣል። ይህ ሁሉ በሮሜ 6 ላይ ተጠቅሷል። አንድ ሰው ሲጠመቅ የጌታን ሞት መቀበር እና ትንሣኤ በታዛዥነት ያሳያል፣ ይህ በጣም ቆንጆ ነገር ነው።

ከተጠመቅክ እና የቤተክርስቲያን አባል ከሆንክ በዙሪያህ ላሉ ሰዎች እውነትን ለማስተማር ተዘጋጅተሃል ማለት ነው። ግን አንድ ሰው መጠመቅ ቢፈልግ ምን ታደርጋለህ? ከአንተ በቀር የሚያጠምቅ ማንም ላይኖር ይችላል፣ ነገር ግን ይህን እንዴት ልታደርግ ትችላለህ? በእውነቱ ሁሉም ነገር በጣም ቀላል ነው። በመጀመሪያ አንድ ሰው ለመጠመቅ የሚያስችል ጥልቀት ያለው

ውኃ ፈልግ ፣ ወንዝ፣ ትንሽ ጅረት፣ ሀይቅ፣ ወይም የሆነ ቦታ ብቻ የውኃ ጉድጓድ ሊሆን ይችላል፣ በባህር ወይም በውቅያኖስ አጠገብ የምትኖር ከሆነ ሁልጊዜ እዚያ ማጥመቅ ትችላለህ። ቀጥሎም ለጥምቀት ጊዜ ውሰዱ፣ ሰውዬው የሚጠመቅበትን ልብስ አምጥቶ ወደ ውኃው እንዲመጣ እና መለወጫ ልብስ ፎጣ ጋር እንዲያመጣ አድርግ። የሚያጠምቀው ሰው ፎጣና ልብስ መቀየር ይፈልግ ይሆናል ምናልባት የቤተሰብ አባላትና ጓደኞች ስለጥምቀቱ ለመመስከር አብረው ቢመጡ ጥሩ ነው።

ምናልባት አንድ ወይም ሁለት መዝሙሮችን መዘመር ትችላለህ፣ አንድ ከመፅሐፍ ቅዱስ ማንበብን ያለጥርጥር አድርግ ምናልባት የሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ 8፡26_39ን ሊሆን ይችላል፣ ይህም እንዴት ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ምስክርነት እንደተቀበለው ለማስተማር ወይም ለማስታወስ ይሆናል፣ ይህንን ምንባብ ካነበብክ በኃላ ወደሚጠመቀው ወንድ ወይም ሴት ተመልሰህ “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ታምናለህ (ሽ)? “ ብለህ ትጠይቃለህ፣ ያ ሰው ወይም ያቺ ሴት “አዎን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን አምናለሁ” ይላሉ

ምስክርነቱ በተሰጠበት መሰረት ግለሰቡን ለማጥለቅ በቂ ውኃ የሆነ ጥልቅ ወደ ሆነበት ውኃ ውስጥ ትመረዋለሕ ነገር ግን ከጥምቀት በፊት እንደዚህ ያለ መግለጫ መስጠት ትፈልጋለህ፣ “ለመታዘዝ ባለህ ፍላጎት መሰረት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ስላመንክ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ለኃጥያትህ ስርየት በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ፣ አሜን” ትላለህ፣ ይህ በማቴዎስ 28፡18_20) ላይ ይገኛል።

ከዚያም የሰውዬውን እጆች ትወስዳለህ፣ አንዱን እጁን በሌላው ላይ አድርግ፣ ከዚያም እጆቻቸውን በአፍንጫቸው ላይ እንደምያስገቡ አድርገው እንዲይዙ ንገራቸው፣ ከዚያ የሚያስፈራ እንደሌለ አስረዳቸው፣ ውኃው በጣም ጥልቅ ካልሆነ አንተ ሰውዬው በቀላሉ ወደ ውኃው ውስጥ እንዲቀመጥ ንገረው ከዚያም እንዲተኛ አድርገው ከዚያም ሌላውን እጅህን ከሰውዬው ጀርባ አኑር እና ሙሉ በሙሉ በውኃ ውስጥ እስኪቀበር ድረስ ቀስ አድርገህ አስቀምጠው ይህ ብቻ ነው፣ ለመስራት በጣም ቀላል ነው፣ ስለውኃው ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም፣ ምክንያቱም አንተ አብረህ ስለአለህና ጥምቀቱም በጣም ጥቂት ሰኮንዶች የሚፈጅ ስለሆነ ነው።

ሌላው የጥምቀት ዘዴ ሰውዬው በውኃ ውስጥ ተንበርክኮ እና ጭንቅላቱን ብቻ ከውኃ ውስጥ በማውጣት ጭንቅላቱን ከውኃው በታች ማድረግ ነው፣ በዚህ መንገድ የሰውን ክብደት ወደ ኃላ በመማር ከዚያም ወደ ላይ ከፍ ማድረግ የለብህም፣ ዋናው ነገር ንሠሀ የገባውን አማኝ ማጥመቅ ነው፣ ይህ ሲደረግ ጌታ ያዘዘውን ታዝዟል፣ እሱ ወይም እሷ በቅዱሣት መፅሐፍት መሰረት ተጠመቁ ማለት ነው።

የመዝሙር መፅሐፍ ይዘው ከመጡ ከጥምቀት በኃላ አንድ ወይም ሁለት መዝሙር ሊዘመር ይችላል፣ የሚጠመቀው ሰው ወንድ ከሆነ እርሱ አሁን አዲስ ክርስቲያን እና በክርስቶስ አዲስ ወንድም ስለሆነ በፀሎት እንዲመራን ዘወትር እጠይቀዋለሁ ። ይህ እንደ ክርስቲያን የመጀመሪያ ፀሎቱ ይሆናል፣ እና ጌታን አሁን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ሲያስብ መስማት እንዴት ድንቅ ነው ጌታን በታዘዙ ሰዎች አንዳንድ የሚያማምሩ ፀሎቶችን ሰምቻለሁ

አሁን ይህ ሰው ከተጠመቀ በኃላ  ጌታ ወደ ቤተክርስቲያኑ ጨመረው፣ በአከባቢህ ውስጥ አንተ ክርስቲያን ስለሆንክ እሱ ደግሞ ውይም እሷ ክርስቲያን ስለሆኑ አሁን ከአንተ ቤተክርስቲያን ሁለት ወይም ሦስት ሆናችሁ ማለት ነው፣ በሌሎች አስተምህሮ ይህ የጥምቀት አገልግሎት በእርግጠኝነት ብዙ ጊዜ ይደጋገማል፡፡

በእርግጥ ውኃ በራስ ላይ መርጨት እና በግንባር ላይ ማፍሰስ መፅሐፍ ቅዱሣዊ ጥምቀት እንዳልሆነ ተረድተሃል፣

አንተ እራስህ በጥምቀት ጌታን ታዘሃልን? ካልሆነ ለዚህ ብርቱ ጉዳይ አሁን እንድትነሣሣ እንፀልያለን፡፡

## ትምህርት 10
## እንዴት ማምለክ እንደሚቻል

ተከታታይ ትምህርታችን ባለህበት እንዴት የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን መጀመር እንደምትችል ነው፣ አንተ ክርስቲያንና የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ካልሆንክ ክርስቲያንና የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል እንድትሆን እናበረታታሃለን፣ ክርስቲያን ከሆንክ እና አንተ ባለህበት አከባቢ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከሌለ በዚያ በአንተ አከባቢ አንተው እራስህ እንድትጀምር እናበረታታሃለን፣ ይህንን የምትጀመረው የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርትን በቤትህ ከቤተሰቦችህ አባልና ከጓደኞችህ ጋር በማጥናት ትችላለህ፣ ሰዎች ትምህርቱን ተቀብለው ወንጌልን ሲታዘዙ አንተ ከእነሱ ጋር ሆነህ እዚያው ቤተክርስቲያን ትተክላለህ ማለት ነው፣

በዚህ ርዕስ እንዴት ማምለክ ይቻላል የሚል ሲሆን ሁላችንም ልናውቀው የሚገባ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ጉባኤ በተተከለች ቦታ እግዚአብሄር መመለክ እንደሚገባውና ይህንን እንዴት መጀመር እንዳለብን ነው፡፡

መፅሐፍ ቅዱስ ስለ አምልኮ ብዙ የሚለን አለ፣ ሰይጣን ኢየሱስን በተፈታተነበት ጊዜ ያለው ቢኖር እንዲሰግድለት እንዲያመልከው ነበር ዳሩ ግን ኢየሱስ የመለሰለት “ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ብቻ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተፅፎልና” አለው (ማቴዎስ 4፡10) እንደዚሁም በሌላ ቦታ ኢየሱስ እንዲህ አለ “እግዚአብሄር መንፈስ ነው፣ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል” አለ (ዮሐንስ 4፡24) ከእኛ የሚፈለገው

ማምለክ ብቻ ሣይሆን እግዚአብሄርን ብቻ ማምለክ፣ በትህትና ማምለክ፣ ቃሉ በሚያዘው ብቻ ማምለክ ይጠበቅብናል።

ብዙዎች ቢያመልኩም አምልኳቸው ያለ እውቀት ነው፣ ይህ ጉዳይ ሐዋሪያው ጳውሎስን በጉዞው ላይ በአቴንስ አጋጥሞታል፣(ሐዋሪያት ሥራ 17፡ 23)፣ ክርስቶስ ብዙዎች ያመልካሉ ነገር ግን አምልኳቸው ከንቱ ነው ምክንያቱም የሰውን ሥርዓት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል፣ በማለት (ማርቆስ 7፡7)፣ ላይ ገልፆታል። ስለዚህ እግዚአብሄር በሚፈልገው መንገድ ልናመልክ ያስፈልገናል። አዲስ በተጀመረቸው ቤተክርስቲያን እንዴት ማምለክ ይቻላል የሚለውን ለማወቅ ወደ መፅሐፍ ቅዱስ እራሱ ሄደን ማየት አለብን ።

የእግዚአብሄር ሰዎች በየትኛውም ጊዜ ተሰብስበው የእግዚአብሄርን ቃል በማንበብ፣ በማጥናት፣ ወደ እግዚአብሄር በመፀለይ፣ በመዘመር ሊያመሰግኑ ይችላሉ ፣ ነገር ግን ጌታ በትክክል ቤተክርስቲያን እነዚህን ነገሮች፣ መፅሀፍ ቅዱስን ማጥናት፣ መዘመር፣ ማምለክ የሚገባትን ቀን አስቀምጧል እሱም ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው በሐዋሪያት ሥራ20፡7፣ ላይ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንደተሰበሰቡ ይነግረናል። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን ገንዘባቸውን በአምልኮ ቀን ሊሰጡ የሚገባቸው በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን መሆን እንዳለበት ደንግጓል፣ (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1፣2)

በብሉይ ኪዳን ህግ የአምልኮ ቀን ከሣምንቱ በ7ኛ ቀን ቅዳሜ ነበር፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶ ከተነሣ ቦኃላ ይህንን ህግ ከመንገድ አስወግዶ አዲስ ኪዳን ወይም የክርስቶስን ህግ አፅድቋል ወይም የተሻለ ህግ አምጥቷል (ዕብራዊያን 8፡13፣ ዕብራዊያን 9፡15_17) በአዲሱ ኪዳን ሌላ የአምልኮ ቀን ሰጠ፣ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ወይም እሁድ ብለን የምንጠራውን ቀን የአምልኮ ቀን ነው።

ስለዚህ ክርስቲያኖች በዚህ ቀን ለአምልኮ ይሰበሰባሉ፣ ጌታ በዚህ ቀን ሁለትምይሁኑሶስትሆነውበስሙ በሚሰበሰቡበትጊዜከእነርሱጋርእንደሚሆን ቃል ገብቶላቸዋል (ማቴዎስ 18፡20) እሱ በቃሉ በኩል መቼ እንደምናመልክ ከጠቀሰልን እኛ እሱን የምናመልክበትን እንዲሁ ተፅፎልናል። በዚህም አምልኮ ላይ እሱን ልናከብር፣ ልናውድስ፣ ልንሰግድለት ከፍ ከፍ ልናደርገው ያስፈልገናል

በዚህ አምልኮ ከምንቀርብበት መንገድ አንዱ ቃሉን በማንበብ ነው፣ ቃሉን ስናነብ ስናጠና እግዚአብሄር ይናገረናል፣ ያስተምረናል፣ ይመክረናል፣ ማድረግ የሚገባንን ያሳውቀናል ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ 5፡39፣ ላይ መፅሐፍን ትመረምራላችሁ እነሱም ስለእኔ ይነግሯቿዋል ብሏል፣ጳውሎስም "የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኃ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሄር ልታቀርብ ትጋ" ይላል (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15) እግዚአብሄር አሁን ለጆሮ በሚሰማ ድምፅ አይናገረንም ነገር ግን በቃሉ ይናገረናል፣ ስለዚህ በአክብሮት እና በትህትና ማዳመጥ እና እሱን መታዘዝ መቀጠል አለብን ።

ያዕቆብ ሲናገር "ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምጸሙ ብቻ አትሁኑ" ይላል (ያዕቆብ 1፡22) ያዕቆብ በ 1፡21 ላይ ይህ ቃል ነፍሳችንን ሊያድን የሚችል መሆኑን ይነግረናል ይቀጥልና "ነገር ግን ነፃ የሚያወጣውን ፍፁሙን ህግ ተመልክቶ የሚፀናበት፣ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሣ ያልሆነውን፣ በሥራው የተባረከ ይሆናል" ብሎ (በ ያዕቆብ 1፡25) ይነግረናል፡፡ ለአምልኮ አንድ ላይ ስንሰበሰብ የእግዚአብሄርን ቃል የማጥናትን ወይም የመስማትን አስፈላጊነት እና ዋጋ ማየት እንችላለን፡፡

ሌላው የአምልኮ መንገድ ፀሎት ነው፡፡ ጌታ በቃሉ ሊናገረን ይፈልጋል እንዲሁም እኛም ወደ እርሱ እንድንፀልይ ይፈልጋል፣ በግል ህይወታችን መፀለይ አለብን፣ ነገር ግን እርሱ እንደ ህዝቡ ጉባኤ እንድንፀልይ ይፈልጋል፣ ቤተክርስቲያን ከተመሰረተ ቦኃላ ስለ ደቀ መዛሙርቱ የምናነበው "በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር" (የሐዋሪያት ሥራ 2፡42)፣ ክርስቶስም ለሐዋሪያት ሳይታከቱ ዘወትር ሊፀልዩ እንደሚገባቸው የሚል ምሣሌን ነገራቸው (ሎቃስ 18፡1) ጳውሎስም ሳናቋርጥ መፀለይ የፀሎት ልምድ ሊኖረን እንደሚገባ ተናግሯል (1 ተሰሎንቄ 5፡17) በሌላ ጊዜም ጌታ ቅርብ ነው፣ በነገር ሁሉ በፀሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሄር ዘንድ ልመናችሁን አስታዉቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ ብሏል (ፊልጵስዩስ 4፡6) ስለፀሎት የሚናገሩትን የቅዱሣት መፅሐፍት ጥቅሶች ሁሉ ልንቀጥል እንችላለን ነገር ግን በግልም ሆነ በህዝብ ፀሎታችን የዮሃንስን አባባል ማስታወስ አለብን "በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፣ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን የሰማናል፣ የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን" ይላል (1ኛ ዮሐንስ 5፡14፣15) እዚህ ጋ ያለው ቁልፍ ሐረግ እንደ ፈቃዱ መፀልለይ አለብን የሚል ነው፡፡ ይህን ስናደርግ ጌታ ፀሎታችንን ሰምቶ ይመልሣል፣ እኛ የሚበጀንን እንደሚያውቅ ልንገነዘብ ይገባናል፡፡

ቀጥሎ በአምልኮ ውስጥ የሚደረግ መዘመር ነው፣ ይህንን ጳውሎስ ሲናገር እንዲህ ይላል "በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በእርሳችሁ ተነጋገሩ፣ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ" (ኤፌሶን 5፡19) በተመሳሳይ ለቆሎስያስም እንዲህ ይላል " "የእግዚአብሄር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፣ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥፁ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በፀጋው በልባችሁ ለእግዚአብሄር ዘሩ" ይላል (ቆልሳያስ 3፡16) በነዚህ ዓረፍተ ነገሮች ላይ መዘመር እንዳለብን እና በልባችን ውስጥ ያለውን ዜማ ለጌታ እንድናደርግ አፅናኦት እንደሚሰጥ አስታውስ ፦ በዕብራዊያን 13፡15 ላይም "እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሄር የምስጋናን መሥዋዕት ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ በእርሱ እናቅርብለት" ይለናል፣ ይህ ሁሉ እግዚአብሄር እርሱን እንድናመሰግው የሚፈልገው በሙዚቃ

መሣሪያ ተጠቅመን ሣይሆን በከንፈራችንና በልባችን መሆኑን ያስተምሩናል እኛ ደግሞ በየሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለጌታ መታሰቢያ የጌታ እራት ልንካፈል ይገባናል (የሐዋሪያት ሥራ 20:7) ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 11 ላይ የክርስቶስን አካል ሥጋ ለማሰብ ከቂጣው መብላት እንዳለብን ተናግሯል የኃጥያታችን ሥርየት ይሆንልን ዘንድ የፈሰሰውን ደሙን ለማስታወስ የወይን ፍሬ ጭማቂ ፅዋ መውሰድ አለብን፣ እንጀራውንና ፅዋውን ስንወስድ እርሱን በማሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ራሳችንን ከመረመርን ቦኃላ መውሰድ እንዳለብን ይነግረናል

እና በመጨረሻም ከገንዘባችን በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን መስጠት አለብን (1ኛ ቆሮንቶስ 16:2)። በልባችን እንዳሰብነው በደስታ ወይም በሃዘን ሣይሆን መስጠት አለብን (2ኛ ቆሮንቶስ 9:7)፣ ይህ የሆነው በንፃ ፈቃድ እንጂ በግድ አይደለም፣ ይህም ስጦታ ለጌታ ሥራ ጥቅም ላይ እንዲውል ነው።

አዲስ ለተቋቋመች ቤተክርስቲያን ጉባኤ ከወንዶች ማን መጽሐፍቅዱስን እንደሚያስጠና፣ ወይም ትምህርት እንደሚሰጥ፣ ማን ፀሎትን እንደሚመራ፣ ማን መዝሙርን እንደሚመራ፣ ማን የጌታን ማዕድ እንደሚጠብቅ፣ በበቂ ሁኔታ አስቀድሞ ፕሮግራም መያዝና ይህንን መምራት አለበት።

## ትምህርት 11
## በጌታ እራት ማገልገል

ተከታታይ ዋና ትምህርታችን ባለህበት ቦታ የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንዴት መጀመር እንደምትችል ነው በዚሁ እንቀጥላለን፣ ይህንን ለማድረግ አንተ እራስህ የዳንክና የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን አለብህ። አባል ካልሆንክ እንድትሆን እናበረታታሃለን። ይህን ማድረግ የምትችለው በእግዚአብሄር በማመን ለኃጥያትህ ንሠሃ መግባት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን በአፍህ መመስከር እና በውኃ ውስጥ በመቀበር በመጠመቅ ነው፣ ይህንን ስታደርግ ጌታ ያድንሃል፣ በቤተክርስቲያኑም ላይ ይጨምረሃል (ማርቆስ 16:16፣ የሐዋሪያት ሥራ 2:47)

በዚህ ትምህርት የጌታን እራት እንዴት እንደምታገለግል እንነጋገራለን፣ ያለህበትን ቤተክርስቲያን ለመጀመር በምታድረገው ጥረት ይመራሃል።

የጌታ እራት የመጣው ከክርስቶስ ነው፣ ከሐዋሪያት ጋር የመጨረሻውን እራት በፋሲካ በዓል ሲበሉ፣ ክርስቶስ በሙሴ ህግ ሥር ነበር ነገር ግን ያ ህግ ከሞቱ ቦኃላ ያልፋል እና በአዲስ ኪዳን ይተካል። በክርስቶስ የተገኘው አዲስ ኪዳንን ለማሳሰብ ከሐዋሪያት ጋር የጌታ እራትን ተጠቅመዋል። ዘገባው እንደሚለው "ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንስቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና ፣ እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፣ ፅዋውንም አንስቶ አመስጭም ሰጣቸው እንዲህም አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፣ ስለብዙዎች ለኃጥያት ይቅርታ የሚፈስ

የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው፣ ነገር ግን እላችኋለሁ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም” አላቸው (ማቴዎስ 26፡26_29) የዚህ ምንባብ የመጨረሻ ጥቅስ በክርስቶስ ቃላቶች ውስጥ ከሞቱ፣ ከመቀበሩ እና ከትንሣኤው እና ከቤተክርስቲያን ምስረታ በኃላ ዳግመኛ እራት እንደማይበላ አመልክቷል። ከዚያም እርሱን በማሳወስ ከእራት ሲካፈሉ እርሱ በመንፈስ ከህዝቡ ጋር ይሆናል። የዚህ እራት ተቋምም በማርቆስ 14፡22_25 እና በሉቃስ 22፡14_20 ላይ ተቀምጧል።

ጳውሎስ ለቆርንቶስ ክርስቲያኖች እንዲህ ብሏል “ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብዬአለሁና ፣ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተስጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሰገነ፣ ቆርሶም፦ እንካችሁ ብሉ፣ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው። ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፣ እንደዚሁም ከእራት በኃላ ፅዋውን አንስቶ፦ ይህ ፅዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፣ ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንንም ፅዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና፣ ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም ይህን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበጥ ሰው ግን ራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ፣ ከጽዋውም ይጠጣ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና” (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡ 23~29)

ከላይ ከተጠቀሱት ቅዱሣት መጽሐፍት ጌታ ህዝቡ ከዚህ መታሰቢያ እራት እንዲካፈሉ እንደሚፈልግ ግልፅ የሆነ ይመስለኛል፣ የክርስቶስን ሥጋና ደም ወይም እንጀራውንና ፅዋውን መውሰድ ለመታሰቢያ መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ግን ለምን ጌታ ይህንን እንድናደርግ ይፈልጋል? እርሱን እና እንድንበት ዘንድ የከፈልውን መስዋዕትነት እንድናስታውስ ነው። ስንካፈል ለራሳችን፣ ለጌታ እና ለዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በህይወት እንዳለ እና አንድ ቀንም ተመልሶ እንደሚመጣ ማመናችንን መግለፅም ጭምር ነው።

ጳውሎስ ከመካፈላችን በፊት ራሳችንን እንመርምር ይላል፣ ይህን ማለቱ ምናልባት ኃጥያት ሠርተን ከሆነ ልባችንን ውስጥ የሚሰማን ካለ ከጌታ ጋር በንሠሃ ተስማምተን ምህረት ጠይቀነው ከዚያ ቦኃላ መውሰድ አለብን እንጂ ንሠሀ ሳንገባ እንዲሁ በድፍረት መውሰድ አደጋ አለው ማለቱ ነው።

የጌታን እራት ማን መብላት ይችላል? እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ የታሰበው ለጌታ ህዝብ ብቻ ነው፣ ነገር ግን በጉባኤያችን ውስጥ ላሉ ሁሉ እናስተላልፋለን፣ ከዚያም መብላቱ ወይም አለመብላቱ የእያንዳንዱ ሰው ውሳኔ ነው። ማንም ሰው መካፈልን መከልከል አንችልም ምክንያቱም እኛ በማናውቀው አንድ ሰው እየጎበኘ ሊሆን ይችላል። እኛ ክርስቲያኖች ናቸው ብለን የምናውቃቸውን ብቻ

የጌታ እራት እንዲካፈሉ ከፈቀድን አንዳንድ ጎብኚ ክርስቲያኖች እንዲካፈሉ ልንፈቅድ እንችላለን፣ ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ማድረግ ያለበት ውሳኔ ነው።

በመቀጠል የጌታን እራት መቼ መካፈል አለብን፣ እናም በየስንት ጊዜስ መካፈል አለብን ? በሐዋሪያት ሥራ 20፡7፣ ላይ የጌታ ሰዎች በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለአምልኮ ሲሰበሰቡ መውሰዳቸሀውን የሚያሳይ ምሣሌ አለን በሌላ ቦታም እንዲህ የሚል እናነባለን "በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር" ይላል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡42) ይህ ጥቅስ ስለጌታ ሰዎች እንጀራን መቁረስ ይናገራል። በሁለቱም ሁኔታዎች ይህ የሚያመለክተው የጌታን እራት መካፈልን ነው። ግን ክርስቲያኖች ለመዘመር፣ ለመፀለይ፣ የእግዚአብሄርን ቃል ለማጥናት፣ እና ከሚያገኙት ስጦታ ለመስጠት ከሣምንቱ የመጀመሪያው ቀን ወይም በየእሁድ ነው፣ ክርስቲያኖች የጌታን እራትንም የሚካፈሉት በዚሁ ቀን ነው፣ ጳውሎስ ሲናገር "ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ፅዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ" (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡26)፣ ምን ያህል ጊዜ ነው? በየሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው።

ብዙ የኃይማኖት ጓደኞቻችን የጌታ እራትን በየሦስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩ ወይም በዓላትን ጠብቀው እንደሚወስዱ እናውቃለን። ቅዱሣት መፅሐፍት በሚያስተምሩት ካልተስማማን፣ በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ የተቀመጡትን ትዕዛዛት እና ምሣሌዎች ካልተከተልን ለምን በኃይማኖት እንጨነቃለን?

ባለህበት ጉባኤ ልትጀምር ከሆነ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን የቅዱሣት መፅሐፍት አምልኮ የጌታን እራት እንደሚጨምር አስታውስ። ሁለት አባላትም ሆኑ ደርዘን ወይም ከዚያ በላይ ቢሆኑ ወንዶች ቅዱሣት መፅሐፍትን እንዲያስተምሩ፣ በፀሎት እንዲመራ፣ በመዝሙር እንዲመራ፣ አንድ ሰው ሹም፣ ከዚያም አንድ ሰው በጌታ ጠረጴዛ ላይ የሚጠብቅ መሾም አለበጥ እራቱን ከመካፈላችሁ በፊት ከቅዱሣት መፅሐፍት የሆነ ጥቅስ ማንበብ አለባችሁ፣ ለምሣሌ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡23~29፣ ወይም በማቴዎስ 26፡26~29 ላይ የሚገኙትን ማንበብ እና ስለነዚህ ጥቅሶች አንዳንድ አስተያየቶችን መስጠት ጥሩ ነው።የክርስቶስን ሞት የሚናገሩትን ሌሎች ጥቅሶችን መጠቀምም ይቻላል። በጊታ ጠረጴዛ ላይ የሚጠብቀው ግለሰብ ስለእንጀራው ምስጋና ማቅረብ አለበት። እያንዳንዱ፣ የክርስቶስን ሥጋ እና የእርሱን መከራ እና የመስቀልን ሞት በማሰብ ይካፈላል፣ እሱ ወይም ሌሎች የምረዱ ከዚያም የተገኙት ከፊለጉ ለመካፈል ዕድል እንዲያገኙ እንጀራውን በዙሪያ ላሉት ማስተላለፍ አለበት ፣ እንጀራው ከተበላ ቦኃላ የውይን ጭማቂውን የክርስቶስ ደም መፍሰስ የሚወክል መሆኑን በማብራራት ለፅዋው መቅረብ አለበት የወይኑ ጭማቂ ብዙውን ጊዜ በትናንሽ ኩባያዎች መሆን አለበት፣ እሱንም

አመሰገኑ በኃላ ማስተላለፍ አለበት።

ብዙውን ጊዜ ሴቶች የጌታን እራት ዝግጅት ይንከበከባሉ፣ ብዙውን ጊዜ በፈቃደኝነት፣ ያልቦካ እንጀራ ይጋገራል፣ ከዚያም ጥቂት የወይን ጭማቂ ካለ መግዛት ይቻላል ወንም ዘቢብ ቀቅለው ጭማቂውን መውሰድ ይችላል ይህንን ዝግጅት ቅዳሜ ምሽት ወይም እሁድ ጧት ማድረግ ይቻላል ቂጣው በአንድ ቦታ ላይ ሊቀመጥ ይችላል፣ እና የወይኑ ፍሬ በትንሽ ኩባያ ወይም ብርጭቆዎች ውስጥ ሊፈስ ይችላል፣ እነዚህ በጠረጴዛ ላይ የተደረደሩ እና ምናልባትም በንፁህ ጨርቅ የተሸፈኑ መሆን አለባቸው፣ በዚህ መታሰቢያ ላይ የሚካፈሉ ሁሉ ይህንን ማድረጋቸው እንደ ክብር ሊቆጥሩት ይገባል።

የቁርባን ዳቦ የምግብ አሠራር

½ ኩባያ ተራ ዱቄት

2 የሾርባ ማንኪያ የወይራ ዘይት

የጨው ነጠብጣብ ፣ ከዚያ ወደ ዱቄት ይጨምሩ፣ ከዚያ በግምት 2 የሾርባ ማንኪያ ቀዝቃዛ ውኃ በትንሹ አንድ ላይ ይደባልቁና በዱቄት ወለል ይሹት በቢላዋ ወደ ትናንሽ ካሬዎች ይቁረጡ። ቀላል ቡናማ እስኪሆን ድረስ በ450 ድግሪ ምድጃ ውስጥ ይቅቡት፣ እንደአስፈላጊነቱ መጠኑ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል። ቂጣው በሚፈለግበት ጊዜ ዝግጁ እንዲሆን ምሽቱን መዘጋጀት አለበት።

የወይን ጭማቂ መመሪያ

ለወይኑ ፍሬ አንድ አቁማዳ የወይን ጭማቂ መግዛት ትችላላችሁ፣ ምንም ከሌለ ዘቢብ ወይም የደረቀ ወይን ገዝተህ አፍልተህ ጭማቂውን ከነሱ ወስደህ በትንሽ ኩባያ ወይም ብርጭቆ ማቅረብ ትችላለህ፣ ወይም ጥቂት ወይን ገዝተህ ጭማቂውን ከነሱ በመጭመቅ ለፅዋዎቹ ማዘጋጀት አለብህ።

## ትምህርት 12
## እንዴት እንደሚጸለይ

አንተ ባለህበት ቦታ የክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንዴት መጀመር እንዳለብን ተከታታይ ትምህርቶቻችንን እንቀጥላለን። ክርስቲያን ከሆንክ እና ቤተክርስቲያን በሌለበት ቦታ ላይ ከሆንክ አንተ ባለህበት ቤተክርስቲያን እንድትጀምር ልንረዳህ እንፈልጋለን። የሚያስፈልግህ ነገር እንዴት መጀመር እንዳለብህ እውቀት እና እሱን ለመሥራት ቅንዓት ተነሣሽነት እና በቀጠል ብቻ ነው። በእርግጥ እዚያ ተቀምጠው ሌላ ሰው እንዲጀምር እየጠበቁ ከሆነ በጭራሽ ላይሆን ይችላል። እንደዚህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ጌታ ሊጠቀምበት የሚችለውን ራስህን አስብ። ከእግዚአብሄር ጋር ለመሥራት ምን ያህል ደስታና ታላቅ ዕድል እንደሆነ አስተውል።

እስካሁን ድረስ ከዚህ ጭብጥ ጋር ተያይዞ በርካታ ጠቃሚ ትምህርቶችን

ሸፍነናል እና አሁን እንዴት መጸለይ እንዳለብን መወያየት እንፈልጋለን።
ጉባኤ ለመጀመር ካሰብክ እና ህዝባዊ አምልኮ ካለህ ስለፀሎት ፣ ስለህዝባዊ ፀሎት፣ ስለ ስብሰባው አስፈላጊነት እና እንዴት ማድረግ እንዳለብህ ማወቅ ይኖርብሃል።

በመጀመሪያ ጸሎት ምን እንደሆነ ላስረዳ፣ በሰማያት ያለውን አባታችንን የምናነጋግርበት መንገድ ነው። በሌላ አነጋገር ጸሎት ለእግዚአብሄር ህዝብ ከተሰጡት በረከቶች እና ልዩ መብቶች አንዱ ነው። ግን የእግዚአብሄር ሰዎች እነማን ናቸው? የእግዚአብሄር ሰዎች እሱን የታዘዙት፣ የዳኑት፣ ክርስቲያን የሆኑ፣ የእግዚአብሄር ልጆች ፣ የጌታ ቤተክርስቲያን አባላት፣ መንፈሳዊ የእግዚአብሄር ቤተሰብ ናቸው። ቅዱሣት መፅሐፍትን ካነበብክ ፀሎት ከአባታቸው ጋር ወንድና ሴት ልጆቹ ያላቸውን ቤተሰባዊ ግንኙነት በዚህ ውስጥም ታያለሕ ነገር ግን ኃጥያተኛው ያልዳነው፣ የእግዚአብሄር ልጅ ያልሆነው በፀሎት ወደ እግዚአብሄር ለመፀለይ ብቁ ሊሆን አይችልም። ኢየሱስ የፈወሰው ዓይነ ስውር ይህንን ተናግሯል "እግዚአብሄርን የሚፈራ ፈቃዱንም የሚያደርግ ቢኖር ያንን እግዚአብሄር ይሰማዋል እንጂ ኃጥያተኞቹን እንዳይሰማ እናውቃለን" አለ (ዮሐንስ 9፡31) ይህ ሰው የእውነትን መርህ ይገልፅ ነበር፣ እግዚአብሄር ኃጥያተኛውን የማይሰማ ቢሆንም ለፀሎቱ መልስ በሚሰጥ መሉ እርሱን የሚያመልኩትንና ትምህርቱን የሚታዘዙትን ይሰማል፣ እና በእርግጥ ይህ የእግዚአብሄር ልጅ የሆነውን ሰው የሚያመለክት ነው፣ ጴጥሮስም ሲናገር "የጌታ ዓይኖች ወደ ፃድቃን ናቸውና፣ ጆሮዎችም ለፀሎታቸው ተከፍተዋልን፣ የጌታ ፊት ግን ክፉ ነገርን በሚያደርጉ ላይ ነው" ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 3፡12) ነቢዩ ኢሳያስም ከዘመናት በፊት እንዲህ ብሏል "እነሆ የእግዚአብሄር እጅ ከማዳን አላጠረችም ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም፣ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች እንዳይሰማም ኃጥያታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል፣ እጃችሁ በደም ጣታችሁም በበደል ረክሳለች፣ ከንፈራችሁም ሐሰትን ተናግሯል፣ ምላሳችሁም ኃጥያትን አሰምቷል" አለ (ኢሳያስ 59፡1~3)

እርሱ እኛን እንዲሰማን የእግዚአብሄር ልጆች መሆን እንዳለብን ለማየት እንዲረዳን ፣ አንድ የውጭ አገር ዜጋ የአገር ውስጥ መንግሥት ለአገር ውስጥ ዜጎች የተጠበቁ መብቶችን እንዲሰጠው እንደጠየቀ አስብ። እግዚአብሄር የእርሱ ለሆኑት የሚሰጣቸውን በረከቶች ልጆቹ ላልሆኑ አይሰጣቸውም ፣ የባዕድ ኃጥያተኛውን ጸሎት ሰምቶ ቢመልስ፣ ለገዛ ልጆቹ እንደሚያደርግ ካደረገላቸው ልጆቹ ምን የተለየ ጥቅም አላቸው? ስለዚህ ልዩነቱን ማየት ትችላለህ፣ ዋናው ነጥብ አንድ ሰው ከእግዚአብሄር የፀሎቱን መልስ ከፈለገ የእግዚአብሄር ልጅ መሆን አለበት።

ስለፀሎት ቅዱሣት መፅሐፍት ብዙ ብለዋል "በሐዋሪያት ትምህርትና

በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር” (የሐዋሪያት ሥራ 2፡42)። ጳውሎስም “ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሄር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ” (ፊልጵስዩስ 4፡6) ዮሐንስም እንዲህ ብሎ አውጇል “በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፣ እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን የሰማናል፣ የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን” (1ኛ ዮሐንስ 5፡14~15)።

ሌሎች በግል ክርስቲያንም ሆነ በጉባኤ ውስጥ ጸሎትን የሚያብረታቱ ብዙ ጥቅስችን መጥቀስ እንችላለን ፣ ሆኖም ግን እኛ ልንወስዳቸው የሚገቡ አንዳንድ መመሪያዎች አሉ፣ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሏቸዋል “እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፣ አብም ስለወልድ እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ፣ ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ” (ዮሐንስ 14፡13~14)፣ በዮሐንስ 15፡16 ደግሞ እንዲህ ብሎ ተስፋ ሰጣቸው “ እኔ መረጥኳችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም ፣ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬያችሁም ሊኖር ሾምኳችሁ” አላቸው 15፡7፣ ላይም “በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል” (ዮሐንስ 15፡7) መጸለይ የሚችሉትን እና ፀሎቶቸን ለመመለስ የተቀመጡትን ሁኔታውች በተመለከተ ነገሮች ግልፅ እየሆኑ መጥተዋል። ጌታ ቃሉን ወደ ደቀመዛሙርቱ፣ እርሱን ለሚታዘዙት እየመራ ነው።፣ በእርሱ ለሚኖሩት በክርስቶስና በቤተክርስቲያኑ ላሉት እየተናገረ ነው፣ እርሱ ጠበቃቸን ስለሆነ ወደ አብ ልመና በስሙ መቅረብ እንዳለበት ተናገረ (1 ኛ ዮሐንስ 2፡1) እንዲሁም በ1ኛ ዮሐንስ 14፡15 ፀሎታችን እንደፈቃዱ መሆን አለበት።

ሌላ ጌታ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሏል “ስትፀልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መፀለይን ይወዳሉና፣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል፣ አንተ ግን ስትፀልይ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝግያህን ዘግተህ በስውር ወዳለው አባትህ ጸልይ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል፣ አህዛብም በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ፣ ስትጸልይ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ፣ ስለዚህ አትመሰሏቸው፣ ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋቸሁን ያውቃልና “ (ማቴዎስ 6፡5~8)።

ደቀመዛሙርቱን ለሰዎች ለመታየት ወይም ለማሳየት መጸለይ እንደሌለባቸው ከነገራቸው ቦኃላ ጌታ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ምሣሌ ሰጣቸው። ይህ በብዙ ኃይማኖተኞች ዘንድ “የጌታ ፀሎት” ተብሎ ይጠራል። ብዙውን ጊዜ በአምልኮ ስብሰባዎች ውስጥ ይደገማል። ነገር ግን የጌታ ጸሎት አይደለም፣ በቀላሉ የናሙና ጸሎት ነው፣ እና ክርስቲያኖች በግላቸው እንዲናገሩ

እንደ ጸሎት ለመጠቀም ታስቦ አልነበረም፣ ጥቅም ላይ ከዋለ የጌታ ሰዎች ለሰዎች እንዲታዩ እና እንዲሰሙ እና ከንቱ መድገም እንዳያደርጉ ይናገራል። በጉባኤው አምልኮ ወቅት መጸለይ ይኖርበታል። አባላት በግልም ሆነ በቡድን መጸለይ ይችላሉ፣ ይሄውም በክርስቶስ የሆነ ወንድም እየመራችሁ በሥርዓት መሆን አለበት ፣ የሚጸልዩት ይሾማሉ፣ ወይም የጉባኤው አባላት ፈቃደኞች ከሆኑ አገልግሎቱን የሚመራው ወንድም ቡድኑን በጸሎት ማን እንደሚመራ ማስታወቅ አለበት፣

በጸሎቱ ውስጥ የሚመሩ ሰው ለጌታ በረከቶች ምስጋና ማቅረብ፣ በአባላት ህይወት ውስጥ መመሪያ እና እርዳታ መጠየቅ፣ የታመሙትን እና ሌሎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ማስታወስ እና የኃጥያት እቅርታ መጠየቅ አለበት ፣ ይህ ጸሎት እና ሁሉም ጸሎቶች በሰማይ ወደ አለው ወደ አባት መቅረብ አለበት እና ሁሉም በክርስቶስ ስም መሆን አለበት። በጸሎት የሚመራ ሰው በግልፅ መናገር ጮክ ማለት ማለትም ሁሉም እንዲሰሙና “አሜን” ማለት እንዲችሉ አድርጎ መጸለይ አለበት።

አባላቶቹ በጸሎት መቀመጥ፣ መቆም፣ መንበርከክ፣ ወይም ቦታ መያዝ ይችላሉ። ይህም ለእነሱ በጣም ምቹ እና ለእግዚአብሄር ያላቸውን ትህትና እና አክብሮት የሚገልጹበት መንገድ ነው። በሚጸልዩበት ጊዜ በቅዱሣት መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሱት አቋሞች ይህንን በግልጽ ያሣያሉ

ጸሎቶች በጌታ እራት ጊዜም ይካሄዳሉ፣ እና መዋጮ ከመወሰዱ በፊት ቤተክርስቲያን በቁሳቁስ ስለተባረከች የምስጋና ቃል ይገለፃል።

በሚቀጥለው ትምህርት እንደምንመለከተው ሴቶች በጉባኤው ውስጥ ህዝባዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ አይፈቀድላቸውም።

## ትምህርት 13
## እንዴት እንደሚዘመር

አሁን እንዴት መዘመር እንዳለብን ወደ አምልኮ ጥናታችን መጥተናል። ስለ ልዩ ልዩ የአምልኮ ክፍሎች ስንወራ ቆይተናል። በተጨማሪም ስለ አምልኮ አስፈላጊነት እና በቅዱሣት መጻሕፍት እንዴት እንደሚደረግ እየተነጋገርን ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ እኛ ክርስቲያኖች እግዚአብሄርን ስናመልክ በመዘመር መካፈል እንዳለብን በእርግጠኘት ያስተምራል። ለእግዚአብሄር የውዳሴ መዝሙር ስንዘምር ልንሰባቸው የምንፈልጋቸው በርካታ ጥቅሶች አሉ፣ ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች እንዲህ ይላል “በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በእርሳችሁ ተነጋገሩ፣ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ” ይላል (ኤፌሶን 5፡19) እንደዚሁም ለቆላስያስ ክርስቲያኖች “የእግዚአብሄር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፣ በጥበብ ሁሉ እርስ በእርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፣ በመዝሙርና

በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባቸሁ ለእግዚአብሄር ዘምሩ” ይላል (ቆላስያስ 3፡16) በእነዚህ ሁለት ማጣቃሻዎቸ ላይ ጳውሎስ መዝሙሮቸን፣ እና መንፈሳዊ መዝሙሮቸን እንዲዘምሩ እና በልባቸው ውስጥ ዜማ እንዲያዷርጉ መናገሩን ታስተውላለህ  ይህ የሚያመለክተው ጌታ ህዝቡ የድምፅ መዝሙር ወይም አካፔላ ሙዚቃ ብቻ እንዲኖራቸው ስለሚፈልግ ነው። በሌላ አነጋገር፣ ከመዝሙሩ ጋር ምንም ዓይነት ሜካኒካል ሙዚቃ አይኖርም። ይህ በእኛ ዘመን እንግዳ ሊመስል ይቸላል፣ ምክንያቱም ብዙ የኃይማኖት ድርጅቶቸ የሙዚቃ መሣሪያ ስለሚጠቀሙና እንደትክክለኛ የአምልኮ ትዕዛዝ እየታሰበ ስለሆነ። ይሁን እንጂ በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በአዲስ ኪዳን ይህንን የሚደግፍና በሙዚቃ መሣሪያ አመለከ የሚል አልተፃፈም።

አየህ በዓለም ላይ ሁለት ዓይነት ሙዚቃዎቸ አሉ። አንዱ ከሌላው ይበልጣል፣ ያም የድምፅ ሙዚቃ ነው፣ ይህ ሙዚቃ የተሠራው በአምላክ በተፈጠረው የድምፅ ቃናዎቸ ታግዞ ነው፣ እናም በዓለም ላይ ካሉ ምርጥ ሙዚቃዎቸ በሰዎቸ ድምፅ ብቻ የሚለቀቅ ነው፣ ሌላው የሙዚቃ ዓይነት በሰዎቸ በተሰሩ መሣሪያዎቸ የሚመረትው መካኒካል መሣሪያ ነው፣ እናም ይህ በሰው ልጅ እጅ የሚመታ ከበሮ፣ ቫዮሊን፣ ወይም ጊታር፣ ፒያኖ ኦርጋን እና ሌሎቸ ብዙ የሙዚቃ መሣሪያዎቸ ናቸው፣ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ህይወት የሌላቸው ናቸው፣ ልብ የላቸውም ድምፅ የሚያሰሙበት ብቸኛው መንገድ  የሰው እጅ ወይም የሆነ ሌላ ኃይል ሲነካቸው ሲያርፍባቸው ብቻ ነው።

አሁን ከነዚህ ዓይነት ሙዚቃዎቸ የትኛውን ነው ጌታ የሚፈልገው? ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ጳውሎስ መዘመር በልባቸን ያለውን ዜማ በማውጣት እንደሆነ ተናግሯል፣ የዕብራዊያን ፀሐፊም እንዲህ ይላል “እንግዲህ ዘውትር ለእግዚአብሄር የምስጋናን መሥዋዕት ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮቸን ፍሬ በእርሱ እናቅርብለት” ይለናል (ዕብራዊያን 13፡15) ይህ የእግዚአብሄር ሰው በከንፈሮቻቸን ፍሬ ጌታን እናመስኝ ይላል። ይህ ማለት ለጌታ ውዳሴ ስንዘምር በድምፃቸን ይሁን ማለቱ ነው። እርሱ የእርሱ ፍጥረታት እንዲያመሰግኑት ይፈልጋል እንጂ እኛ የፈጠርነው ነገር አይደለም። ሕያው የሆነው ሰው ሕያው የሆነውን  እንዲያመሰግነው ይፈልጋል እንጂ የሞተ ህይወት በሌለው በራሱ መናገር በማይቸል አይደለም።

አንዳንድ ሰዎቸ እግዚአብሄርን የምናመልከው የትኛውን ሙዚቃ እንደምጠቀም ምን ለውጥ ያመጣል ብለው ያስባሉ። ዋናው ነገር ጌታ በአምልኮው ውስጥ የሚፈልገውን ያውቃል እና ፍላጎቱን ማከበር  አለብን። እራሳቸንን ወይም ሰውን የማስደሰት ጉዳይ አይደለም፣ ይልቁንም ጌታ ደስ ሊለው የሚገባው እርሱ ነው እንጂ። ጳውሎስ እንዲህ ይላል “እንግዲህ ምንድነው ? በመንፈስ እጸልያለሁ በአዕምሮም ደግሞ እፀልያለሁ፣ በመንፈስ እዘምራለሁ በአዕምሮም ደግሞ እዘምራለሁ” ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡15)።

በታሪክ መረጃ መሠረት የሰው ድምፅ ሙዚቃ ዜማዎች በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያን ለአምላክ አምልኮ ብቻ ትጠቀም ነበር፣ ሆኖም ከመቶዎች ዓመታት በኃላ የኃይማኖት መሪዎች ሜካኒካል ሙዚቃን ወደ አምልኮ አስገቡጥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ጥቅም ላይ ዋለ፣ ነገር ግን ለጌታ ልንሰግድ ከፈለግን እርሱ በገለጸው መሠረት ለምን አንሰግድለትም፣ ያም ማለት በመንፈስና በእውነት (ዮሐንስ 4:24)፡፡

ለምን በመካኒካል ሙዚቃ እንደሚጠቀሙ እና ለምን እንደ ጥቅም የሚያስቡበትን ብዙ ምክንያቶችን ያቀርባሉ፣ ነገር ግን አንዳቸውም ቢሆኑ በእግዚአብሄር ቃል እና ትክክለኛ አመክኞ እና በማስተዋል ላይ የተመሰረቱ አይደሉም፡፡

ክርስትና የመዝሙር ኃይማኖት በመሆኑ ልዩ ኃይማኖት ነው፣ መዝሙር ጌታን ለማመስገን የሚያገለግል ነው፣ ነገር ግን ሰዎች እግዚአብሄርን እንዲታዘዙ እና ወደ ከፍተኛ የአገልግሎት ከፍታ እንዲሄዱ የሚያነሣሣ በመሆኑ ኃይለኛ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡

ስለዚህ ክርስቲያኖች በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ተሰብስበው ጌታን ለማምለክ በሚሰበሰቡበት ጊዜ ዝማሬ ከተሰማሩባቸው ነገሮች አንዱ ነው፣ የጌታን ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ለመጀመር በሂደት ላይ ከሆንክ ሰውዬው ከመካከላቸው አንዱን ይምረጥ፡፡ ጉባኤውን በመንፈሳዊ እና ቅዱስ ጽሑፋዊ መዝሙሮች መምራት የሚችል ሰው ይመረጥ፡፡

መዝሙሮች በሚመረጡበት ጊዜ መሪው የሚታወቁትን መምረጥ አለበት፣ እና በሁሉም መልኩ፣ ቅዱስ የሆነ መዝሙር መሆን አለበት፣ ይኼውም በእነርሱ ውስጥ ያለው መልዕክት ከእግዚአብሄር ቃል ትምህርት ጋር የማይስማማ መሆን የለበትም፡፡ ስህተትን መዘመር ይቻላል፣ እንዲሁም ስህተትን መስበክ እና ማስተማር ይቻላል ፡፡ እንደእውነቱ ከሆነ ስህተትን ስዘምር ስህተትን እያስተማርክ ነው፡፡ አንድ ሰው ሲዘምር የመዝሙሩን መልዕክት ያሰላስላል እና በዙሪያው ያሉትን እያስተማረ መሆኑን በመገንዘብ በመዝምሩ ውስጥ መሳተፍ አለበት፡፡

ጥቅምላይየሚውሉትንመዝሙሮችብዛትበተመለከተ፣ምንምየተወሰነ ቁጥር ይሄ ነው የሚባል የለም፣ ያንን የሚወስነው መዝሙሩን የሚመራው ሰው ነው፡፡ እና ባለው ጊዜ ሁኔታ ወይም ሰዓት ሁኔታ ላይ መመስረት አለበጥ ብዙውን ጊዜ መሪው በተመልካቾች ፊት ይቆማል፣ በምዕራቡ የዓለማችን ክፍል ወንድሞች ብዙውን ጊዜ ማስታወሻ ያላቸውን የመዝሙር መፅሐፍ ይጠቀማሉ ከዚያ እያነበቡ ይዘምራሉ፣ ይህንን መጠቀምም ይቻላል፣ ሌሎቹ መዝሙሮቹን በቃላቸው ስለሚያውቁ ማስታወሻ ላይጠቀሙ ይችላሉ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ምንም የምንለው የለም

መላው ጉባኤው በመዝሙር መሳተፍ ይኖርበታል፣ ምናልባት በዓለም

ላይ ምርጥ መዝሙር ላይሆን ይችላል፣ ነገር ግን ከልብ ከሆነ በእርግጥ ለጌታ ውብ መሆን አለበት። እኛ ራሳችንን ለማዝናናት መዘመር የለብንም፣ ምንም እንኳን መዘመር ብንፈልግም፣ እናም በእርሱ ልንታነፅ እንችላለን። እኛ ብቸኛ መዘምራን ወይም ልዩ ዘማሪያን ቡድን ሊኖረን አይገባም ይልቁንም የጉባኤ መዝሙር ሁሉም የሚሳተፍበት መዝሙር እንጂ፣ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሄርን በአንድነት እንድታመሰግን ነው። አንዳንድ ጊዜ መዝሙራችን የሚፈለገውን ያህል ጥሩ ካልሆነ፣ ለዚህ ልዩ ሥልጠና ክፍለ ጊዜዎች ሊኖሩን ይገባል፣ አንዳንድ ጊዜ መዝሙሮቹን መማር ያስፈልገን ይሆናል፣ እኛ ትርዕት ለማሳየት እየሞከርን አይደለም፣ ነገር ግን ዝማሬያችን ወደ ጌታ የቀረበ ስለሆነ ጥሩ ሥራ ለእግዚአብሄር መሰዊያ ለማቅረብ ነው።

በመፅሐፍ ቅዱስ መሠረት፣ ሴቶች በጉባኤው መዝሙር ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ፣ ነገር ግን መዝሙሩን በምድረክ ላይ ሊመሩ የሚያስችል የተሰጠ ፈቃድም ሆነ ምሣሌ የለም። ትንሽ ቆይቶ የሴቶችን ሚና በቤተክርስቲያን የሚለውን እናያለን።

ወጣቶቻችንን መዝሙር መምራት እንዲማሩ ማበረታታት አለብን። ይህም ምሽት አገልግሎት እንዲመሩ ዕድል በመስጠት ወይም እሮብ ምሽት ከአንዳንድ ታላቅ ወንድም መመሪያ ጋር የሚለማመዱበትት ልዩ ክፍል እንዲኖራቸው ማድረግ ይቻላል።

## ትምህርት 14
## ስጦታ እንዴት እንደሚሰጥ

ባለህበት ቦታ የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንዴት እንድሚጀመር የሚለው ተከታታ ትምህርታችንን እንቀጥላለን፣ ያንን ሀሳብ ይዘን ስጦታን እንዴት መስጠት እንዳለብን በሚል ላይ እንወያያለን።

ባለህበት የጌታን ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር ካሰብክ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እግዚአብሄርን የማምለክ ዓላማ ማድረግ አለብህ። በፀሎት፣ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ መዝሙር፣ እና የጌታ እራት በተጨማሪ ካገኙት ላይ እንደአቅማቸው ለእግዚአብሄር ሥራ ስጦታ በመስጠት ይመለካል፣ እንግዲህ ስጦታን በተመለከተ እንዴት ይሰጣል የሚለውን አስፈላጊነቱን እንዴት እንደሚሆን ከቅዱሣት መፅሐፍት ላይ ጥቅሶችን እናስተውላለን

መፅሐፍ ቅዱስ በትምህርት እና በምሣሌዎች የተሞላ መሆኑን እናውቃለን። እግዚአብሄር እንኳን ልጁን ስለዓለም ሁሉ ኃጥያት በመስቀል ላይ እንዲሞት አሳልፎ ሰጠ (ዮሐንስ 3፡16)፣ ክርስቶስም ነፍሱን ሰጥቶአል (1ኛ ዮሐንስ 4፡14)፣ ከዚህ የበለጠ ምን ምሣሌ ሊኖረን ይችላል? ግን ለጌታ ምን መስጠት እንችላለን? ምን ያህልስ መስጠት እንችላለን?

በአንድ ወቅት ኢየሱስ አንድ ወጣት ለቁሳዊ ነገሮች ከፍተኛ ትኩረት

እንደሚሰጥ ባወቀ ጊዜ ሄዶ ያለውን ሸጦ ለድሆች እንዲሰጥ ነገረው (ማቴዎስ 20፡35) ኢየሱስ የተናገረውን ማስታወስ እንዳለብን ሉቃስ ፅፏል "እንዲሁ እየደከማችሁ ድውዮችን ልትረዱና እርሱ ራሱ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው እንዳለ የጌታን የኢየሱስን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኋችሁ" ይላል (የሐዋሪያት ሥራ 20፡35)

ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንዲህ ብሏል "ለቅዱሣንም ገንዘብን ስለማዋጣት ለገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት እንደደነገግኩኝ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፣ እኔ ስመጣ ይህ ገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን ከእናንተ እያንዳንዱ በየሣምንቱ በፊተኛው ቀን እንደ ቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ" አለ (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2)።

በጳውሎስ መግለጫ ውስጥ በርካታ እውነቶች ተቀምጠዋል። በመጀመሪያ መስጠቱ የሚፈፀምበትን ቀን የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንደሆነ ይገልፃል። በሐዋሪያት ሥራ 20፡7፣ ላይ ደቀመዛሙርቱ ለአምልኮ በተሰበሰቡበት እና በዚህም የጌታን እራት በሉ፣ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለአምልኮ አንድ ላይ መሆናችን በተፈጥሮ ይህ የጌታ ሰዎች ገንዘባቸውን የሚሰጡበት ጥሩ ጊዜ ይሆናል።

ሁለተኛ ሁሉም ሰው መሳተፍ እንዳለበት ተናግሯል። ማለትም ከሣምንት በፊት የበለጸገ ወይም የሚሰጠውን ያገኘ ሰው መዘጋጀት በቤቱ ማስቀመጥ አለበት። አንድ ሰው የሚሰጠው ነገር ከሌለው ባለመስጠቱ እፍረት ሊሰማው አይገባም፣ ምክንያቱም ጌታ እንዲሰጥ ከእርሱ አይጠብቅምና፣ ገቢ ካገኘ ግን መስጠት አለበት፣ ነገር ግን እያላቸው አለመስጠት ጌታን እንደ መዝረፍ ይቆጠራል

በሦስተኛ ደረጃ በቤት ማስቀመጥ አለባቸው ይላል፣ ዛሬ ብዙውን ጊዜ የምናስበው የገንዘብ መዋጮ ማድረግ ነው፣ ነገር ግን የጌታ ሰዎች ሊሰጡ የሚችሉት ገንዘብ ሳይኖራቸው እንስሳትን፣ አትክልቶችን፣ ፍራፍሬዎችን ወዘተ እና ከዚያም በተራው በገንዘብ ሊለወጥ ይችላል። የጌታን ሥራ ለመደገፍ ሊያገለግል ይችላል፣ ዛሬም ቢሆን ባአንዳንድ የዓለም ክፍሎች አንዳንድ ክርስቲያኖች ገንዘብ ሳይኖራቸው ይችላል ነገር ግን የሚሰጡት ሌላ ነገር ሊኖራቸው ይችላል፣ ለምሣሌ ዶሮ፣ እንቁላል፣ ወይም ሌሎች ነገሮችን በመስጠት ሰባኪውን ወንጌላዊውን ለመደገፍ ይረዱ ይሆናል። ያም ስጦታ ነው፣ በጌታ ፊት ተቀባይነት አለው።

አራተኛው እንደበለፀጉ መጠን እንዲሰጡ ተናገረ፣ ይሠሩት ከነበረው ነገር የተወሰነ ክፍል መስጠት ነበረባቸው። ለእያንዳንዱ ግለሰብ ምን ያህል ይቀራል፣ ግን እያንዳንዱ ሰው ምን ያህል እንዳለው ያውቃል፣ አይሁድ ከገቢያቸው አንድ አስረኛውን ይሰጣሉ፣ ተጨማሪ መስዋዕታቸውን ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ከአሥር የሚበልጠውን ይሰጣሉ፣ እኛ እንደ ክርስቲያን በጣም

የሚሻል ህግ አለን፣ አዳኝ አለን፣ እናም የዘላለም ህይወት ተስፋ አለን ስለዚህ በአሮጌው ህግ ከሚኖሩት የበለጠ እንጂ ያነሰ አንሰጥም።

አምስተኛው በዚህ ወቅት የሚሰጠው ስጦታ የቅዱሣንን አንዳንድ ፊላጎቶች ለማሟላት እንዲረዳ ነበር፣ እና ጳውሎስ ሲደርስ ሁሉም ነገር ዝግጁ ይሆን ዘንድ በዚህ ጊዜ መስጠት እንዳለባቸው ተናግሯል። የእግዚአብሄር ሰዎች እንደሚገባቸው ከሰጡ የሥራው ፍላጎቶች ያለ ምንም ችግር ሊሰራ ይችላል። በእርግጠኝነት ጌታ የዓለምን ሰዎች ስራውን እንዲደግፉ አይጠብቅም፣ ክርስቲያን ካልሆነ ሰው የሚሰጠው መዋጮ ውድቅ አይሆንም ወይም እምቢ አይባልም፣ ነገር ግን አይጠየቅም።

በኋላ ላይ ጳውሎስ እንዲህ አለ “ ይህንም እላለሁ፣ በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፣ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል። እግዚአብሄር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፣ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም” ይላል (2ኛ ቆሮንቶስ 9፡6~7)።

እባክህን ጳውሎስ የመዝራትን እና የማጨድ ምሣሌን በመጠቀም የመስጠትን ፅንሰ~ሀሳብ እንደሚያስተምር አስተውል። የዚያን ዘመን አብዛኞቹ ሰዎች ዛሬ እንደሚያደርጉት መርሆውን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ሀሳቡ ብዙ በዘራቻሁ ቁጥር ብዙ ታጭዳላችሁ፣ ትንሽ ከዘራቻሁ ትንሽ ታጭዳላችሁ ፣ ይህ መርህ በእርሻ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የህይወት ዘርፎች እውነት ነው። ለምሣሌ ለጌታ አብዝተህ ከሰጠኸው ጌታ ሊባርክህ ይችላል። ትንሽ ከሰጡ በምላሹ ትንሽ መጠበቅ ይችላሉ፣ በእርግጥ አንድ ሰው የበለጠ ለመቀበል ብቻ ተጨማሪ ከሰጠ የእሱ ዓላማ የተሳሳተ ነው። እና በኢህ ጉዳይ ላይ አይሠራም። ነገር ግን አንድ ሰው ሐቀኛ እና ቅን ከሆነ ፣ ጌታን የሚወድ እና በእውነት የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለማድረግ የሚጥር ከሆነ ብዙ በሰጠ ቁጥር የበለጠ ይባረካል።

ብዙዎች እግዚአብሄርን ስለሚያታልሉ አልተባረኩም። ራስ ወዳድ ናቸው እናም ፍላጎታቸውን ከጌታ ያስቀድማሉ። አባታቸው ለምን አብዝቶ የማይባርካቸው ይገረማሉ። እግዚአብሄርንና እና መንግሥቱን ማስቀደም እና ከዚያ በኋላ ሌሎች ነገሮች ይሟላሉ ይላል (ማቴዎስ 6፡33)። እስቲ ሞክረውና እና ካልሠራ ተመልከት፣

ጳውሎስ በልባችን እንዳሰብነው መስጠት እንዳለብን ተናግሯል። የሠራነውን እናውቃለን እናም ወደ አምልኮ ስፍራው ከመድረሳችን በፊት ልንሰጠው የነበረን ገንዘብ አስቀድመን አስቀምጠን ነበር። ጳውሎስ ሲናገር የምንሰጠውን ነገር መወሰን አለብን ከዚያም በተገቢው ጊዜ ለመስጠት ዝግጁ እንሁን ይላል።

በመቀጠልም መስጠታችን በቁጭት ወይም በግድ መሆን የለበትም ይልቁንም በደስታ መስጠት አለብን። በቦታው እንደተቀመጥን ሊሰማን አይገባም፣ ወይም ደግሞ አስተዋፅኦ እንድናደርግ እንደተገደድን ማሰብ

የለብንም። ነገር ግን በፍላጎት መስጠት በመቻላችን ደስተኞች መሆን አለብን፣ ጸሐፊው እግዚአብሄር እንዲህ ዓይነት ሰጪ እንደሚወድ ተናግሯል።

በጌታ ቀን አንድ ሰው ለአምልኮ ለተገኙት ሰዎች የመሰብሰቢያውን ሣህን እንዲያስተላልፍ መሾም አለበት፣ ይህ በተመረጠው ሰዓት ላይ ነው፣ እና ምናልባትም ለቁሳዊ በረከቶች የምስጋና ፀሎት ይቀድማል፣ ሁሉም የመስጠት እድል ሊሰጣቸው ይገባል ከዚያም ከአገልግሎቱ ቦኃላ ሁለቱ ሰዎች ስብስቡን እንዲቆጥሩ፣ መዝገብ እንዲይዙ እና ምናልባትም በባንክ ስም በባንክ ሂሳብ ውስጥ እንዲያስቀምጡ ማድረግ፣ ከአከባቢ ጉባኤ ከወንድ አባላት አንዱ ገንዘቡን እንዲይዝ እና ቁጥሩን ለቤተክርስቲያን እንዲያሳውቅ ይሾም። ገንዘቡ ወንጌልን ለመስበክ፣ ለቤተክርስቲያን ዕቃዎችን ለመግዛት ፣ ድሆችንና ችግረኞችን ለመርዳት ወዘተ እንዲውል ይደረጋል

መስጠታችን ለእግዚአብሄር የምናቀርበው አገልግሎት በጣም አስፈላጊ የአገልግሎት ክፍል መሆኑን አስታውስ

## ትምህርት 15
## የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍለ ጊዜ

ሌሎችን ወንጌል ስለማስተማር፣ በክርስቶስ ስለማጥመቅ እና ስለአምልኮ መንገድ ተነጋግረናል። የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እና እንዴት እንደምንመራቸው እየተወያየን ጥናታችንን እንቀጥላለን።

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታ ቃሉን እንደሰጠን እናውቃለን። ያንን መፅሐፍ ለማወቅ እና የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለማወቅ ቃሉን ማጥናት ወይም ሲሰበክ ሱያስተምሩት መስማት አለብን ክርስቶስ ሐዋሪያቱን ሄደው ወንጌል እንዲሰብኩ ነገራቸው (ማርቆስ 16፡15)። ጳውሎስ “የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሄር ልታቀርብ ትጋ” ይላል (2ኛ ጢሞተዎስ 2፡15)። እንዲህም ብሏል “እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሄር ቃል ነው” ትላል (ሮሜ 10፡17) እግዚአብሄርም ከሠማይ እንዲህ ሲል ተናገረ “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ” (ማቴዎስ 17፡ 5) በእነዚህ እና በሌሎች በርካታ ጥቅሶች የእግዚአብሄርን ቃል መስማትና ማጥናት አስፈላጊነት ማየት እንችላለን። በዚህ እውቀት ነው ጌታን አምነን የምንታዘዘው፣ ለመዳን እና ወደ ቤተክርስቲያንም ለመጨመር ስንሰማ ሰናጠና ስንታዘዝ ነው።

እርግጥ ነው የእግዚአብሄር ቃል ማስተማርና ማጥናት ለአዋቂዎች ጥሩ ነው፣ ሌሎችንስ? የተለያየ ዕድሜ ያላቸው ልጆችስ? በአዋቂዎች ትምህርት ውስጥ ንግግር ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል፣ እዚያም ክፍሎቻቸው የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን እና የትምህርት ደረጃውችን ይመለከታሉ። ነገር ግን

ወደ ትምህርር ሲመጣ በተለያየ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጆች፣ ሁልጊዜ በተለያዩ የዕድሜ ቡድኖች መከፋፈል አለባቸው፣ በፍፁም ብዙ መቶዎችን የሚያሰባስብ ትምህርት ቤት ሊኖርህ አይገባም። በሁሉም የዕድሜ ደረጃዎች የተለያዩ አስተማሪዎች ሊኖሩና እንደ ዕድሜያቸው ሊሆን ይገባል። ከእንደዚህ ዓይነቱ ዘዴ ምን ዓይነት ትምህርት ሊመጣ ይችላል?

ትምህርት በዓለማዊ ትምህርት ቤታችን ከሆነ ጥበብ ማየት እንችላለን ። ታዲያ ለምንድነው የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የመኖራቸውን ጥበብ ማየት ያልቻልነው? በብዙ ቦታዎች ትንንሽ ጉባኤዎችን ማግኘት በጣም ከባድ እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ። ለረጅም ጊዜ የተገናኙት በቤታቸው ወይም በጥቃቅን ክፍሎች ውስጥ ነው፣ አንዳንድ መዝሙር ፀሎቶችና የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ተሰብስበው ለተገኙት ሁሉ ተሰጥቶአቸዋል፣ እናም በሆነ ምክንያት ይህን ማድረጋቸውን መቀጠል ይፈልጋሉ፣ ነገር ግን ልጆቹን አያስቡም፣ ሰባኪው የሚናገረውን መረዳት ያቃታቸዋል። ለሁሉም ልጆች ሀ ክፍል ቢዘጋጅ ለአዋቂዎችም ትምህርት ለብቻ ቢዘጋጅ ጥሩ ነው፣ ይህ ለሁሉም ሰው ትልቅ ጥቅም ይኖረዋል ትምህርቶቹን ለህፃናት ተዘጋጅተው በየደረጃቸው ሊሰጡ ይገባል ።

መስበክ እና ማስተማር አንድ ሰው የንግግር ችሎታውን ለማሳየት እንደ መዝናኛ ወይም እድል መሆን የለበትም። ይልቁንም ዓላማቸው በቦታው የተገኙት የእግዚአብሄርን ፈቃድ እንዲያውቁ እርሱን እንዲታዘዙ መርዳት ነው፣ በእሱ አዕምሮ፣ የመማሪያ ክፍሎችን ዋጋ በቀላሉ ማየት እንችላለን ለልጆችም ሆነ ለወላጆቻቸው ከስብከት ይልቅ እውነትን መፅሐፍ ቅዱስን ማስተማር የበለጠ በክፍል ውስጥ መሰጠት አለበት።

ባለህበት ጉባኤ የሚቋቋም ከሆነ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ዝግጅትን በአዕምሮህ ያዝ። ከትንሽ ቡድን ጋርም ቢሆን ጥሩው የሥራ መንገድ ለመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት አንድ ሰዓት መመደብ ነው፣ እና በዚያን ጊዜ ወንዶቹ እንዲያጠኑ፣ ካደረጉ ልጆችን በዕድሜ በመከፋፈል ያስተምሩ፣ ይህንን በተለያዩ ቦታዎች ክፍሎች ማስተማር ይችላሉ።

ሌላው ሊሰራበት የሚገባው ጉዳይ ለተለያዩ ክፍሎች መምህራን ነው። ልምድ ባይኖራቸውም የሚሞክሩት ቀስ በቀስ የማስተማር ችሎታቸውን ማዳበር ይችላሉ። ዋናው ነገር መሞከር ነው። አንድ በሣምንቱ ውስጥ ትምህርት ማዘጋጀት ይችላል፣ እና እሁድ ላይ ክፍሉን ለማስተማር ዝግጁ ይሁን፣ በእሁድ ዕለት መምህራን ለክፍል እንዲዘጋጁ ከዚያ በፊት የላቀ ዝግጅት መደረግ አለበት።

ከክፍል ቦኃላ ምዕመናኑ ለአምልኮ ሊሰበሰቡ ይችላሉ፣ ምናልባት ከአከባቢው አባላት አንዱ ትምህርቱን ሊያስተምር ይችላል። ወይም ደግሞ የወንጌል ሰባኪ በአከባቢው ሰባኪ ሆኖ እንዲሰራ ሊጋበዝ ይችላል። ከእነዚህ

ውስጥ አንዳቸውም ቢሆኑ ካልተቻለ ወንዶቹ ተራ በተራ ጥቅሶችን ወይም የውንጌል ትራክቶችን ማንበብ ይችላሉ። ጌታን የመታዘዝ ፍላጎት ካለ ሁሉም ነገር ይቻላል።

ሁሉም ዓይነት ነገሮች በመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ዝግጅት ሊዳብሩ ይችላሉ። በተለይ ጉባኤው ሲያድግ እና ተጨማሪ የትምህርት ክፍሎች ሲይስፈልጉ ማደግ ይከተላል

ለመጠቀም ብዙ ዓይነት ርዕሰ ጉዳ አሉ። ክፍሉ ብሉይ ኪዳንን፣ አዲስ ኪዳንን፣ በተለይም የመፅሐፍ ቅዱስን መጽሐፍትን፣ የክርስቶስ ምሣሌዎችን፣፣ የርስቶስን ህይወት፣ የክርስቶስን ወንጌል፣ የአዲስ ኪዳን አምልኮን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን፣ የክርስትና ህይወትን ሊያጠኑ ይችላሉ ወይም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ጥናቶቹ አዲስ ኪዳንን ጀምሮ ለመቀጠልም ሊሆን ይችላል።

ልዩ የጥናት ክፍሎች ሊኖሩ ሊዘጋጁ ይችላሉ፣ አንዳንድ አዲስ ተቀያሪዎች ካሉህ አዲስ የተለወጡ ሰዎችን በተመለከተ ክፍል እንዲኖርህ ትፈልግ ይሆናል፣ በዚያ ክፍል ውስጥ ወንጌልን፣ ቤተክርስቲያንን፣ ክርስቲያናዊ ኑሮን እና ሌሎች አዳዲስ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ እንዲያድጉ ሊረዷቸው የሚፈልጓቸውን ርዕሰ ጉዳዮችን መመልከት ትችላላቸሁ።

አንዳንዱ ለወንዶችና በተለይም ለወጣቶች የሚሰጡ የስልጠና ክፍሎች አሉ፣ ንግግር እንዴት እንደሚማሩ፣ መዝሙር እንዲመሩ፣ እንዲፀልዩ፣ ወዘተ እንዲማሩ ይሰጣል።የእንደዚህ ዓይነት ፍሎች ዓላማ እነዚህን ሰዎች ለማዘጋጀት ነው፣ በቤተክርስቲያኑ መደበኛ አገልግሎት ውስጥ ለመሳተፍ ሀሳቡ ፕሮፈሽናል ለመሆን እየሞከርን አይደለም። ነገር ግን ጥሩ ሥራ ለመሥራት መሞከር እንፈልጋለን ለጌታ እየተሠራ ስለሆነ እና ተሳታፊው ጌታን እና ቤተክርስቲያኑን ስለሚወክል ነው።

አንዳንድ ጊዜ ወንድሞች ለታናናሾች ልጆ የልጆች ክፍል እንዲኖራቸው እፈልጋሉ፣ እና በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን ያህል መጽሐፍት እንዳሉ ይጠይቁ፣ መፅሐፎቹን እንዲያስተውሱ፣ በስም እንዲሰጧቸው የሐዋሪያትን ስም እንዲዘረዝሩ እና ሌሎች ብዙ መፅሐፍ ቅዱሶችን ይስጧቸው፣ እውነታው ይህ ለእነሱ ጥሩ ሥልጠና ነው፣ አንዳንድ የልጆች መዝሙሮች እና ዝማሬዎች ብዙውን ጊዜ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገለግላሉ።

እንደሚታወቀው በሁሉም ክፍሎች መፅሐፍ ቅዱስ ወይም አዲስ ኪዳን ዋና የፅሑፍ መፅሐፍ ይሆናል፣ ነገር ግን አንዳንድ አስተማሪዎች የትምህርታቸውን ዝርዝር ለማዘጋጀት እንዲገለብጡ እና ከዚያም ለክፍል አባላት ቅጂዎችን ለመስጠት ይፈልጉ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ሌሎች ለአገልግሎት ዝግጁ የሆኑ ቁሳቁሶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፣ እነዚህ የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አንዳንዶቹን ለማውጣት እንዲረዷቸው ታስበው የተዘጋጁ ናቸው፣ ነገር ግን በሁሉም ሁኔታዎች መምህሩ እየተማረ ያለው የአምላክ እውነት

ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ትምህርቱን በጥንቃቄ መመርመር ይኖርበታል፡፡

## ትምህርት 16
## ወንጌልን እንዴት መስበክ እንደሚቻል

ከዚህ ጭብጥ ጋር በመስማማት ወንጌላዊ መሆን የምንችለ እንዴት እንደሆነ እንወያያለን፡፡ አዲስ ጉባኤ ለመጀመር እንኳን የክርስቶስን ጉዳይ በማስፋፋት ላይ የሚገኘውን የስብከት ወንጌል አገልግሎትን ያካትታል፡፡ እጋ በዚህ ታላቅ አማኞች ነን፣ እና አንተም እንድትጸሰትበት እንፈልጋለን፡፡

የወንጌል አገልግሎትን አስፈላጊነት ለማሳየት ከሚችሉት ምርጥ መንገዶች አንዱ ታላቁ ተልዕኮ መጀመር ነው፣ ጌታ ከሞተ፣ ከተቀበረ እና ከመቃብር ከተነሣ ቦኃላ እና ወደ ሰማይ ወደ አባቱ ከመመለሱ በፊት ለሐዋሪያቱ እንዲህ አላቸው "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፣ እኔሆም እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" አላቸው (ማቴዎስ 28፡19~20)

ሉቃስም እንዲህ ብሎ አስነብቦናል "እንዲህም አላቸው ክርስቶስ መከራ ይቀበላል፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፣ በስሙም ንሠሀ እና የኃጥያት ሥርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአህዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተፅፏል እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ፣ እነሆም፣ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፣ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳለም ከተማ ቆዩ" አላቸው (ሉቃስ 24፡46~49) በመጨረሻ ኢየሱስ የተናገረው " ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማሪያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ" (የሐዋሪያት ሥራ 1፡8)

ከላይ የተጠቀሱት ቅዱሣት መጽሐፍት ጌታ ወንጌሉ ለዓለም ሁሉ፣ ለዓለም ህዝብ እአ ለዓለም ሁሉ ፍጥረት ሁሉ እንዲደርስ እየተናገረ ነው፡፡ ወንጌል በመጀመሪያ በኢየሩሳሌም ከዚያም በይሁዳ፣ በሰማሪያ በመጨረሻም ለምድር ሁሉ ይሰበካል ብሏል፡፡ እርሱም፣ ይህን ሥራ እንዲሠሩ ሐዋሪያት እንዲመሯቸው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እንደሚሰጣቸው ተናግሯል፡፡ አየህ፣ እነሱ የኖሩት አዲስ ኪዳን በተጠናቀቀ መልክ ከመሰጠቱ በፊት ነው፣ ስለዚህ ጌታ መንፈስ ቅዱስን ወደ እውነት ሁሉ እንዲመራቸው ልኮ ነበር፡፡ በእርግጥ አዲስ ኪዳን ዛሬ እንዳለን ሲሰጥ፣ ተአምራዊው የመንፈስ ቅዱስ መሪነት አያስፈልግም ነበር፡፡

የሐዋሪያት ሥራ 2ን ስናነብ ሐዋሪያት በኤሩሳሌም ከተማ እንደተሰበሰቡ እናያለን፡፡ በእውነት ወንጌል ገና አልተሰበከም ነበር፣ ቤተክርስቲያንም

አልነበረቸም፣ ነገር ግን በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሐዋሪያትን እንዲመራቸው በአከባቢው ሰዎች ቋንቋ እንዲናገሩ እና ተአምራት እንዲያደርጉ በሐዋሪያት ላይ ፈሰ። ይህ ኃይል የተሰጣቸው ህዝቡ የሐሰት አስተማሪዎች እንዳልሆኑ ነገር ግን በእውነት የእግዚአብሄር መሆናቸውን ለማሳመን ነው። ይህ የሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ቦኃላ አይሁድ ይህን በዓለ ለማክበር ከመላው ዓለም በተሰበሰቡበት በመጀመሪያው በጴንጤቆስጤ ዕለት ነበር። ጌታ ይህንን ጊዜ የመረጠው ወንጌል እንዲሰበክ ነው፣ በዚህም ምክንያት ሦስት ሺህ ያህሉ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሲጠይቁ “ጴጥሮስም ንሠሃ ግቡ ኃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ በብዙ ሌአ ቃልም መሰከረና ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ ብሎ መከራቸው፣ እግዚአብሄርንም እያመሰገኑ በህዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፣ ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር” (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ 40፣ 47) በዚህም የጌታችን ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም ተቋቋመ፣ ጌታን የበለጠ በመታዘዝ ወንጌል ደጋግሞ ተሰበከ።

ቦኃላ ፊልጶስ ያንን አስደናቂ የወንጌል መልዕክት ለመስበክ ወደ ሰማሪያ ወረደ፣ ብዙዎች አምነው ተጠመቁ፣ በተጨማሪም በሐዋሪያት ሥራ 8 ላይ ፊልጶስ ከኢትዮጵያ ለመጣ ሰው ሄዶ እንዲሰብክ የጌታ መልዓክ እንዳዘዘው እናነባለን። በዚህ ስብከት ያ ሰው ጌታን ታዘዘ፣ እናም ወደ ሀገሩ ተመልሶ የክርስቶስን ጉዳይ በሀገሩ እንደሚተክል ጥርጥር የለውም።ስለዚህ ወንጌል እየተሰበከ ነበር፣ ቤተክርስቲያንም በብዙ ቦታዎች እየተቋቋመች ነበር።

በሐዋሪያት ሥራ 9 ላይ ስለ አገልግሎቱ እናነባለን፣ እናም በተለያዩ ሚሲዮናዊ ጉዞዎቹ ያደረገውን እናውቃለን። በመላው እስያ፣ አልፎ ተርፎም ወደ አውሮፓ ወንጌልን ወሰደ በቆላስያስ 1፡23 ወንጌል ከሠማይ በታች ላሉ ፍጥረት ሁሉ እንደተወሰደ ተናግሯል። እንዲሁም በሮሜ 10፡18 ላይ ወንጌል እስከ ዓለም ዳርቻ እንደሄደ ተናግሯል፣ እስቲ አስቡት ! ወንጌል ለመጀመሪያ ጊዜ ከተሰበከ ሠላሣ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መልዕክቱ ለዓለም ሁሉ ደረሰ ማለት ይቻላል፣ አዎን ቤተክርስቲያን የተመሰረተችው በኢየሩሣሌም ባአንጾኪያ፣ በቆሮንቶስ፣ በኤፌሶን፣ በፊልጵስዩስ፣ በተሰሎንቄ፣ በቤሪያ፣ በቆላስያስ፣ እና በሮም እንዲሁም በዓለም ዙሪያ በሽዎች በሚቆጠሩ ሌሎች ቦታዎች ነው።

ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ሐዋሪያት ሥራውን የጀመሩት በኢየሩሳሌም ሲሆን በቀሪው የህይወት ዘመናቸው በሄዱበት ሁሉ የጌታን ቤተክርስቲያን ሰብከው ተክለዋል። ግን መደረግ ያለበትን ሁሉ ማድረግ አልቻሉም። ስለዚህ ወንጌል የታዘዙት እንሱን አግዘዋል፣ ፊልጵ፣ ስትቪን፣እና ሌሎቹም በመቶ እና በሺዎች የሚቆጠሩ ነበሩ። ሐዋሪያቱ ወይም የታዘዙት ሐዋሪያቶች ሌላ ቦታ በሄዱ ጊዜ እነዚህ ይሰብኩ ነበር፣ ከሰሙትም መካከል አምነው ከኃጥያታቸው ንሠሀ ገብተው ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መስክረው ሲጠመቁ

ጌታ ያድናቸዋል ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምራቸዋል። እናም ሌላ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አጥቢያ ይፈጠራል፣ በዚያ ከተማና አከባቢ ወንጌል መሰበክ ሲቀጥል የበለጠ ጌታን የሚታዘዙ ሲኖሩ አጥቢያው እያደገ ይሄዳል፣ ከጊዜ ቦኃላ እነዚህ አማኞች ክርስቲያኖች በዙሪያቸው ወደ ሚገኙ ከተሞችና መንደሮች በመሄድ ወንጌልን በመስበክ ብዙ ጉባኤዎች ያቋቁማሉ። ስለዚህ የክርስቶስ ወንጌል ምድርን እስኪሸፍን ድረስ ቀጠለ።

ጌታ አሁንም እስከዛሬ ድረስ ፣ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ እንድናደርስ ያዘናል። ጌታን ከታዘዝክ ድነሃል፣ እናም አንተ የእርሱ ቤተክርስቲያን አባል ነሕ ገና አንተ ባለህበት አከባቢ ጉባኤ ላይኖር እችላል፣ ካልሆነ እንዴት እዚያ ይጀመራል? በዙሪያህ ላሉ ሰዎች በራስህ የወንጌል ስብከት፣ ከቤተሰብህ አባላት እና ከጓደኞችህ ጋር ልትጀምር ትችላለህ፣ ያ ለወንድ ቀላል ሊሆን ይችላል፣ ግን ስለ ሴት ወይም ወጣጽ ? እንደዚያ ከሆነ ትምህርትህን በግል ደረጃ ማድረግ አለብህ ፣ ወይም ምናልባት አንድ ሰው መጥቶ አንዳንድ ስብሰባዎችን እንድታደርግ ሊረዳህ ይችላል። የጌታ ቤተክርስቲያን እዚያ እንዲኖር በእውነት ከፈለግክ ይህን ለማድረግ ይህን ለማድረግ እንደሚቻላ እርግጠኛ ነኝ።

ወንጌልን ለማስተማር የወንጌል ትራክቶችን መፅሄቶችን እና ፅሑፎችን መጠቀም ይቻላል። የግል ጥናት ማሰማራት ይቻላል። እንዲሁም የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሊዘጋጁ ይችላሉ። በምሣሌ እና በአፍ ቃል እያንዳንዱን አማኝ፣ እና የራሳችንን ልጆች እና ወጣቶች፣ የወንጌል አገልግሎትን በተመለከተ የግል ኃላፊነቶችን መወጣት አለብን።

የእግዚአብሄር ቃል በበቂ ሁኔታ ከተማሩ የተሰወሰኑ ለውጦችን ያመጣል፣ ማለትም በዚያ ያሉ ክርስቲያኖች በቤት፣ በትምህርት ቤት፣ በአዳራሽ፣ ውስጥ፣ ወይም ከዛፍ ሥር እንኳን በመገናኘት ሊጀምሩ ይችላሉ። ዋናው ነገር አንተ እንዲገናኙ፣ እንዲሰግዱ፣ የእግዚአብሄርን ቃል እንዲያጠኑ ማስተማር መቀጠልህ ነው። ወንጌላዊ ሁን ሁልጊዜ ሌሎችን ለማስተማር ዕድሎችን ፈልግ፣ ሥራው እያደገ ሲሄድ፣ ጊዜ ላይ ሊሆን ይችላል። በአከባቢው ላሉ ከተሞችና መንደሮች ምሥራቹን ለመስበክ አንዳንድ ጥረቶች ሊደረጉ ይገባል ጌታ ባለን ነገር ላይ እንድረካ እንደማይፈልግ፣ ነገር ግን እንድንሄድ እንድንሰብክ፣ እንድንለወጥ፣ እና የእርሱን ዓላማ እንድናሰአጭ እንደሚፈልግ አስታውስ። እርሱ እንድንሰራው የሚፈልገው ሥራ ይህ ነው፣ እርሱን ስንታዘዝ ከእኛ ጋር ይሆናል፣ ጥረታችንንም ይባርካል።

## ትምህርት 17
## እንዴት ማደራጀት እንደሚቻል

የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሲጀመር ልብ ሊሉት የሚገባቸው በጣም አስፈላጊ ነገሮች አንዱ እንዴት ማደራጀት እንደሚቻል ነው። ስለዚህ በዚህ ጊዜ

ለጥያቄው ትንሽ ማሰብ እንፈልጋለን።
ሁላችንም እንደምናውቀው፣ ለማንኛውም ነገር በሚሆነው ነገር ሁሉ ድርጅት አለ። ትምህርት ቤቶቹን፣ ንግድን፣ መንግሥትን እና ወታደራዊን አስብ። እነዚህ ሁሉ አንድ የጋራ ነገር አላቸው፣ ማለትም ታቅደው፣ ተደራጅተው፣ እና እንደ ድርጅታቸው በብቃት ይሠራሉ፣ በደንብ ካልተደራጀ ግራ መጋባት፣ ምርታማነት ማጣት እና መጨረሻው ወደ ውድቀት ይደርሳል።

በታይማኖትም እንዲሁ መደራጀት አለበት፣ ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን እንደሚገነባ ቃል ገብቷል (ማቴዎስ 16፡18)፣ ና የገባውን ቃል ጠብቋል፣ በሐዋሪያት ሥራ 2 መሠረጥ በእንደዚህ ዓይነት የሰዎች ስብስብ መካከል በሥርዓት እና በማስተዋል እንድፀራ ያሰፈልጋል።

ቅዱሣት መፅሐፍት ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ ይነግሩናል (ቆላስያስ 1፡18፣ ኤፌሶን 1፡22~23)፣ እና አካል ወይም ቤተክርስቲያን እርሱን የታዘዙትን ያቀፈች ናት፣ ምንም እንኳን ቤተክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ብትኖርም በአጥቢያው በጉባኤዎች መልክ አለ፣ ክርስቶስ አሁንም ራስ ነው ጉባኤውም በዳኑት ሰዎች የተዋቀረ ነው፣ ቤተክርስቲያን ምንም ዓይነት ሁለንተናዊ የሰው ድርጅት ባይኖራትም፣ አደረጃጀት ግን አላት።

በጉባኤ አጀማመር ላይ ወዶች ፍላጎኦቶችን የሚመለከቱ እና ሊመጣ የሚችለውን ማንኛውንም ሥራ የሚከታተሉ ናቸው፣ ከአባላቶቹ መካከል ሰባኪዎች፣ አስተማሪዎች ፣ የመዝሙር መሪዎች ወዘተ ሊኖሩት ይችላሉ። አሁን ሽማግሌ እና ዲያቆናት ሆነው የሚሾሙ በይፋ መሪዎች ሊኖሩት ይችላሉ

ይህንን በማስመልከት ጳውሎስ ለጢሞተዎስ ሲናገር እንዲህ ይላል “ማንም ኤጵስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው፣ እንግዲህ ኤጵስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገበዋል፣ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ እንደሚገባው የሚሰራ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ለማስተማር የሚበቃ፣ የማይሰክር፣የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ ገንዘብን የማይወድ፣ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፣ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሄርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል? በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን፣ በዲያብሎስ ነቀፋና መጥመድም እንዳይወድቅ ፣ በውጭ ካሉት ሰዎች ደግሞ መልካም ምስክር ሊኖረው ይገባዋል፣ እንዲሁም ዲያቆናት ጭምቶች፣ በሁለት ቃል የማይናገሩ፣ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጎመጁ፣ ነውረኛ ረብ የማይወዱ፣ በንፁህ ሕሊና የኃይማኖትን ምስጢር የሚይዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል። እነዚህም ደግሞ አስቀድሞ የፈተኑ፣ ከዚያም ቦኋላ ያለ ነቀፋ ቢሆኑ በዲቁና ሥራ ያገልግሉ፣ እንዲሁም ሴቶች ጭምቶች፣ የማያሙ፣ ልከኞች በነገር ሁሉ የታመኑ ሊሆኑ ይገባቸዋል፣ ዲያቆናት ልጆቻቸውንና የራሳቸውን ቤቶች፣ በመልካም እየገዙ

እያንዳንዳቸው የአንዲት ሴት ባሎች ይሁኑ፣ በዲቁና ሥራ በመልካም የገለገሉ ለራሳቸው ትልቅ ማዕረኛ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው እምነት ብዙ ድፍረት ያገኛሉ" (1ኛ ጢሞተዎስ 3፡1~13)

አሁንም ጳውሎስ ለቲቶ " ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም ፣ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፣ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ ፣ የማይነቀፍና የአንዲት ሚስት ባል የሚሆን፣ የሚያምኑም ልጆች ያሉት፣ ስለመዳራትም ወይም ስለ አለመታዘዝ የማይከሰስ ማንም ቢኖር ሹመው፣ ኤጵስ ቆጶስ እንደ እግዚአብሄር መጋቢ የማይነቀፍ ሊሆን ይገበዋልና፣ የማይኮራ፣ የማይቆጣ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ ነውረኛ ረብ የማይወድ ፣ ነገር ግን እንግዳ ተቀባይ፣ በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ ጠንቃቃ፣ ፃድቅ፣ ቅዱስ፣ ራሱን የሚገዛ ይሁን፣ ህይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ ሊመክር ተቃዋሚዎችንም ሊወቅስ ይችል ዘንድ እንደተማረው በታመነ ቃል ይፅና፣ የማይታዘዙና ከንቱ የሚናገሩ የሚያታልሉ ይልቁንም ከተገረዙት ወገን የሚሆኑ ብዙ ናቸውና፣ እነዚህም ስለነውረኛ ረብ የማይገባውን እያስተማሩ ቤቶችን በሞላው ስለ ሚገለብጡ አፋቸውን መዝጋት ይገባል" (ቲቶ 1፡5~11)

የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሆነው የተሾሙት እንደ ኤጵስ ቆጶሳት፣ እረኞች፣ ቀሳውስት፣ እና መጋቢዎች ተብለው በተጠሩት ቅዱሣት መፅሐፍት ውስጥም እንዳሉ መጠቆም አለበት፡፡ (ኢቶ 1፡7፣ 1ኛ ጴጥሮስ 5፡1~5፣ 1ኛ ጢሞተዎስ 4፡14፣ ኤፌሶን 4፡11)፣ በተጨማሪም ሽማግሌዎች እንዲሾሙ ቢያንስ ሁለት ሰዎች እነዚህን ብቃቶች ማሟላት አለባቸው፣ ከዚያም ጉባኤው እንዲያገለግሉ ሊሾማቸው ይችላል፡፡ በዚያ ሥልጣን እነሱ በሚያደርጉትና በሚናገሩት ሁሉ በእግዚአብሄር ቃል የሚተዳደሩ ከክርስቶስ በታች ይሆናሉ፡፡ መንጋውን ለመመገብ ማለትም የቤተክርስቲያን አባላት የእግዚአቢሄርን ፈቃድ በትክክል እንደ ተማሩ እና በሳል መንፈሳዊ አመራር እንዳላቸው ለማሳየት አለባቸው፡፡

ቀደም ሲል በተገለፁት ቅዱሣት መፅሐፍት መሠረት የሚፈለጉትን መመዘኛዎች በተመለከተ፣ ከሦስት ነጥቦች በስተቀር ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት እነዚህን ማሟላት መቻል አለባቸው፣ እነዚህ የማይካተቱት ፣ አንድ ሰው አዲስ አባል ከሆነ ሽማግሌ ሆኖ ሊሾም አይችልም፣ ሽማግሌዎችም አንዲት ሚስት ብቻ ሊኖራቸው ይገባል፣ እንዲሁም የራሳቸው የሆኑ ልጆች ያመኑ ክርስቲያን የሆኑ መሆን አለባቸው፣ በዚህም ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አመራር የመስጠት ችሎታቸውን ያሳያሉ፣ ራስ ወዳድ ያልሆኑ፣ የማይቆጡ፣ ለወይን ጠጅ ያልተገዙ፣ ፣ እንግዳ ተቀባዮች የሆኑ፣ ሰውን የሚወዱ፣ ልከኞች፣ ፃድቅ፣ ቅዱሣን ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡

የአንዱ ጉባኤ ሽማግሌዎች ማገልገል የሚችሉበት በዚህ የክርስቲያን በድን ላይ ብቻ ነው ኃላፊነታቸው፣ በሌላ እህት ጉባኤ ላይ ሥልጣን የላቸውም፣

የሌሎች ጉባኤ ሽማግሌዎችም ሊገዟቸው አይችሉም።

ዲያቆናትንም በተመለከተ በሽማግሌዎች ሥር ሆነው ረዳት ወይም አገልጋይ ሆነው የሚያገለግሉ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወንዶች ሊኖሩ ይገባል፣ እንዳነበብነው ለእነሱም መመዘኛዎች አሉ። እንዲሁም ሚስቶች የተወሰኑ መመዘኛዎችን ማሟላት መቻል አለባቸው።

በአጠቃላይ ሽማግሌዎች ለጉባኤው መንፈሳዊ መመሪያ ሲሰጡ ዲያቆናት ሥጋዊ ፍላጎቶቻቸውን ሲከታተሉ የሁለቱም አከባቢዎች ኃላፍነቶችን ሊሸከሙ እንደሚችሉ አድርገን እናስባለን። ማህበሩ በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ያለ ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ሊኖሩ ይችላሉ። ከጊዜ ቦኃላ ግን እግዚአብሄር ሲያበስላቸው ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ሊኖሯቸው ይችላል። ሁሉም አባላት ክርስቶስን እንደሚከተሉ መሪዎቻቸውን መውደድ እና ማክበር እና መመሪያዎቻቸውን መከተል አለባቸው፣

ከዚያም ወንጌላዊያን ወይም ሰባኪዎች አሉ። ሰባኪ ግን የቤተክርስቲያን ፓስተር አይደለም ወይም ቤተክርስቲያንን የሚያሰተዳድር እሱ አይደለም። ይልቁንም ሽማግሌዎች ካሉ በእነሱ ሥር ሆኖ ያገለግላል፣ ሽማግሌዎች ከሌሉ ከጉባኤው አባላት ጋር ይሠራል። በሥነ ምግባር የቀና መሆን አለበት እና ጤናማ ትምህርት መስበክ አለበት። ጳውሎስ ለወጣት ጢሞተዎስ እንደነገረው “በእግዚአብሄር ፊት በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት፣ በመገለጡና በመንግሥቱም እመክርሃለሁ፣ ቃሉን ስበክ፣ በጊዜውም አለ ጊዜውም ፅና፣ ፈፅመህ እየታገስህና እያስተማርህ ዝለፍና ገሥፅ ምከርም” አለው (2ኛ ጢሞተዎስ 4፡1~2) በቅዱሣት መፅሐፍት ውስጥ ያሉ ብዙ መግለጫዎች ለጌታ እና ለሌሎች ሰዎች የእግዚአብሄርን መልዕክት በማወጅ ያላቸውን ኃላፊነት እንዲያስታውሷቸው ወደ ሰባኪዎች ይመራሉ። ጉባኤው ትንሽም ይሁን ትልቅ አንዳንድ ሥራዎች መከናወን አለባቸው፣ አንድ ሰው መዝሙሩን መምራት አለበት፣ ገንዘብ ያዥ ያስፈልጋል፣ ሌሎች የጌታን እራት ማዘጋጀት አለባቸው፣ እንዲሁም ሌሎች የሌሎችን የሚያስፈልጋቸውን ፍላጎት መንከባከብ አለባቸው።

ስለዚህ የበለጠ ውጤታማ ለመሆን እና ነገሮችን በሰላማዊና በሥርዓት ለማከናወን የቤተክርስቲያን ሰዎች እነዚህን ኃላፊነቶች ለመጠበቅ ረገድ የተደራጀ እና ሥርዓታዊ መሆን አለባቸው፣ ቤተክርስቲያን መሪዎቿን ለእግዚአብሄር ቃል ታማኝ እስከሆኑ ድረስ ማክበር እና መታዘዝ አለባት።

## ትምህርት 18
## መሰብሰቢያ ቦታ

ለትምህርታችን በዚህ ጊዜ ዬት እንደምንሰበሰብ መወያየት እንፈልጋለን። ብዙ ሰዎች በየሣምንቱ ጌታን ለማምለክ የሚሰበሰቡ ከሆነ የሚሰበሰቡበት

የተወሰነ ቦታ መኖሩ የታወቀ ነው። ለዚህ የተለያዩ አማራጮች አሉ። ነገር ግን በመጀመሪያ የጥንቷ ቤተክርስቲያንን እኛ እና ስለመሰብሰቢያ ቦታ ያደረጉትን እንመልከት።

ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም ከተማ በጴጤቆስጤ ቀን ስትጀምር ሐዋሪያት ለብዙ ሰዎች እንደሰበኩና ሦስት ሺህም ጌታን እንደታዘዙ እናውቃለን (የሐዋሪያት ሥራ 2፡41) ይህ ዬት እንደተፈፀመ ምንም አልተነገረም። ክፍት የሆነ ቦታ፣ በመድረክ፣ ቢቤተመቅደስ ውስጥ፣ ወይም በሌላ ቦታ ላይ፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡42፣ የሚለን በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር" ይላል፣ በመቀጠልም "በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፣ እግዚአብሄርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር" (የሐዋሪያት ሥራ 2፡46~47)

በሐዋሪያት ሥራ 3 ላይ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ውብ በሆነው በቤተ መቅደሱ በር ላይ አንካሣ ሰው ሲፈውሱ እና ይህም ጴጥሮስ በሰለሞን በረንዳ በቤተመቅደሱ ላይ ለተሰበሰቡት ብዙ ሰዎች እንዲሰብክ ዕድል ሰጠው። ጴጥሮስ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከነገራቸው በኃላ እንዲህ እናነባለን "ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ፣ የወንዶችም ቁጥር አምሥት ሺህ ያህል ሆነ" (የሐዋሪያት ሥራ 4፡4) ስለዚህ ቤተክርስቲያን በቁጥር እያደገች ነበር። ግን አሁንም እነዚህ ሁሉ ሰዎች ለአምልኮ የተገናኙት ዬት ነበር? ምናልባት በቤተ መቅደሱ ውስጥ መሰባሰቡን ቀጠሉ፣ ነገር ግን ያ ውሎ አድሮ ችግሮች እንደሚገጥማቸው ጥርጥር የለውም፣ ምክንያቱም እነሱ በሙሴ ህግ ሳይሆን በክርስቶስ ትምህርት ያመልኩ ነበርና።

ስለ መሰብሰቢያ ቦታ ብዙም አናስብም ። ስለወንጌል ትምህርት እንጂ፣ ያ መሰብሰብ በሁሉም ቦታ ሊከናወን ይችላል። ለምሣሌ ፊልጶስ ከኢትዮጲያዊው ሰው ጋር በምድረ በዳ ተገናኝተዋል። በሠረገላውም ከእርሱ ጋር ሊተባበር ዕድል አግኝቶ በመንገድም ሲሄዱ ሲያስተምረው እናነባለን እሱ መሰብሰቢያ ቦታ መሆኑ ነው (ሐዋሪያ 8፡26~39)። በሐዋሪያት ሥራ 9 ሐናኒያ ሳኦልን በመንገድ ላይ ጌታ ጠርቶት እንዳገኘውና ለመታዘዝ ምን ማድረግ እንዳለበት እንደነገረው እና ከዚያም በታዛዥነቱ እንደረዳው እናነባለን። ጳውሎስና ሲላስ የእስር ቤቱን ጠባቂና ቤተሰቡን ወንጌልን አስተምረው እንዲታዘዙ አድርገዋል (የሐዋሪያት ሥራ 16)

ወንጌሉ የተሰበከባቸው ብዙ ቦታዎች ለምሣሌ ጳውሎስ ብዙ ጊዜ ሄዶ አይሁዶችን በሚያስተምራቸው የተለያዩ ምኩራቦች ውስጥ መጥቀስ እንችላለን፣ በኤፌሶን ሳለ "ወደ ምኩራብም ገብቶ ስለ እግዚአብሄር መንግሥት እየተነጋገረና እያስረዳቸው ሦስት ወር ያህል በግልጥ ይናገር ነበር፣ አንዳንዶች

ግን አልከኞች ሆነው በህዝብ ፊት መንገዱን እየሰደቡ ባላመኑ ጊዜ፣ ከእነርሱ ርቆ ደቀ መዛሙርትን ለየ፣ ጢራኖስም በሚሉት በትምህርት ቤት ዕለት ዕለት ይነጋገር ነበር፣ በእሲያም የኖሩት ሁሉ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም የጌታን ቃል እስኪሰሙ ድረስ ሁለት ዓመት ያህል እንዲህ ሆነ" (የሐዋሪያት ሥራ 19፡8~10) አሁን አንድ ትምህርት ቤት የሆነ የሚሰበሰቡበት ህንፃ ሳይኖረው አይቀርም ጳውሎስም እዚያ ያስተምር ነበር ነገር ግን እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ይህ ምናልባት ክርስቲያኖች የሚያመልኩበት ላይሆን ይችላል፣ ታዲያ የጌታ ሰዎች ለአምልኮ የሚሰበሰቡበት ዬት ነው?

ምንም እንኳን በአዲስ ኪዳን ስለ ቤተክርስቲያን ህንፃዎች ባናነብም፣ ክርስቲያኖች በዚያን ጊዜ የየራሳቸው ቤት ነበራቸው ጳውሎስም ቤት ለቤት አገልግሎትን በሐዋሪያት ሥራ 20፡20 ፣ ተናግሯል፣ ሌላው ጳውሎስ ስለተከራየውም ቤት እንዲህ እናነባለን "ጳውሎስም በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፣ ወደ እርሱም የሚመጡትን ሁሉ ይቀበል ነበር፣ ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሄርን መንግሥት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር" (የሐዋሪያት ሥራ 28፡30~31) ጳውሎስ በገዛ ቤቱ ውስጥ ሆኖ ለሁለት ዓመት ያህል ታስሮ መቆየቱ በዚያ እሰግድ እንደነበር ይነግረናል፡፡ጳውሎስ በጵርስቅላና ባአቂላ ቤት ስለተሰበሰበቸው ቤተክርስቲያን ተናሯል (ሮሜ 16፡5፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡19)፣ እና በፍልሞና 1፡2፣ በቆላስያስ 4፡ 15፣ እና ሮሜ 6፡23ም እናነባለን

ግን የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ዬት ነው የሚሰበሰቡት? የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያንስ? ጳውሎስ ወደዚያች ከተማ በገባ ጊዜ ሊድያንና ቤተሰቧን እንዳገኛቸውና ሲያስተምራቸው ወደ ጌታ እንደመለሳቸው እናውቃለን፡፡ ቦኃላም የእስር ቤቱን ጠባቂ እና ቤተሰቡንወደ ጌታ እንደመለሳቸው እናውቃለን፡፡ ቤተክርስቲያን በዚያ እንዳደገች እናውቃለን፡፡ ሽማግሌዎችና ዲቆናት የሚሆኑ ሰዎች ይኖሯት ነበር፣ ምክንያቱም ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ላለችው ቤተክርስቲያን ከተወሰነ ጊዜ ቦኃላ በፊልጵስዩስ ለሚገኙ ቅዱሣን መልዕክት ፅፏልና፣ ግን ለማምለክ የሚገናኙት ዬት ነበር?

በቅዱሣት መፅሐፍት ውስጥ ጌታ ቤተክርስቲያንን ለአምልኮ የተለየ ህንፃ እንዳላት የሚቃወመው ቃል ባይኖርም ቅዱሣት መፅሐፍት ም በዚህ ጉዳይ ላይ አይናገሩም፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሄር ህዝቡ ከእነርሱ ጋር የሚገናኝበት ድንኳን እንዲሠሩ እንዳዘዛቸው እናውቃለን፡፡ ሰለሞንም እግዚአብሄር ከህዝቡ ጋር የተገናኘበት በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስን ሠራ፣ ኢየሱስ ግን ለሳምራዊቷ ሴት እግዚአብሄር በተራሮች ላይ መስገድ እነደሚቀርና ባሉበት በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል ብሏታል (ዮሐንስ 4፡1~30)

ስለዚህ ጌታ ቤተመቅደስ ወይም "ቅዱስ ሥፍራ"እንዳይለወጥ በህንፃ

ላይ አፅናኦት ለመስጠት እንዳልፈለገ ግልፅ ነው፣ ክርስቲያኖች በራሳቸው የመሰብሰቢያ ቦታ ማዘጋጀት እንደሚችሉ ያውቃል። በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው ይህ በህንፃ ጉዳይ ህግ ማውጣት ለእግዚአብሄር አስፈላጊ አልነበረም

ዛሬስ ? ቤተክርስቲያን ዬት ትሰበሰባለች ? በቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ህንፃ ውስጥ፣ ወይም በተከራዩት ህንፃ ውስጥ መሰብሰብ ይችላሉ፣ ያንን ጌታ ለህዝቡ ይተወዋል፣ በፈለግንበት ቦታ መሰባሰብ እንችላለን። እርግጥ ነው፣ ጉባኤው እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለራሱ የሚጠቀመው ፊላጎት እየጨመረ ይሄዳል፣ ሌላው ቀርት ንብረት መግዛት እና የራሱን መሰብሰቢያ ህንፃ ቤት መገንባት ይችላል።

ነገር ግን ሁል ጊዜ የቤተክርስቲያን መሰብሰቢያ ቤት ወይም ህንፃ ግንቡ ቤተክርስቲያን አለመሆኑን አስታውስ። እሱ ቅዱስ ሥፍራም አይደለም፣ በቀላሉ የጌታ ሰዎች ለአምልኮ የሚሰበሰቡበት፣ የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን የሚማሩበት ቦታ ነው፣ ህንፃው ወይም መሰብሰቢያው ያን ያህል የተለየ ቦታ የሚሰጠው አይደለም። እዚያ የሚያመልኩ ሰዎች ግን አስፈላጊዎች፣ ዋጋ ያላቸው ክርስቲያኖች ናቸው።እንግዲህ የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ባለህበት ቦታ ብትጀምር የመሰብሰቢያ ቦታ እንዲኖራት ዝግጅት ማድረግ ይቻላል።

## ትምህርት 19
## የሴቶች ሚና

አሁን በቤተክርስቲያን ውስጥ የሴቶችን ሚና ጥያቄን ማጥናት እንፈልጋለን። ባለህበት ቤተክርስቲያንን ስለመጀመር ስናገር፣ ከአንዲት ሴት ወይም ልጃገረድ ጋር እያወራሁ ሊሆን ይችላልና፣ እንዲህ ከሆነ ምን ማድረግ ትችላለህ (ሽ)? እንደምናየው ብዙ ማድረግ ይችላል፣ ነገር ግን በመጀመሪያ ወደ ቅዱሣት መፅሕፍት እንሂድ እና ስለ ሴቶች ሚና በቤተክርስቲያን ምን እንደሚሉ እንይ !

በዚህ የሴቶች የነፃነት ንቅናቄ ጊዜ ሴት ማድረግ በምትችለው ነገር ላይ መገደቧን መናገር ቂምን መቀየምን ይፈጥራል፣ ይህ ደግሞ በኃይማኖትም ሆነ በሌሎች ሥራ ዘርፎች ላይም እውነት ይሆናል።አንዳንድ የኃይማኖት ጓደኞቻችን ሴቶቻቸውን በቤተክርስቲያናቸው ውስጥ ኤጵስ ቆጶስ፣ ሰባኪ ወዘተ እንዲሆኑ ፈቅደዋል። ነገር ግን እኛ የምንፈልገውን ወይም የማንፈልገውን ወይም ዓለም እንዴት እንደሚከፋፍለን፣ ወይም ለእውነት ያለን አቋም ምን ምላሽ ሊሰጠን ይችላል የሚለው ጥያቄ ላይ ሳይሆን ዋናው ነገር መፅሐፍ ቅዱስ በዚህ ላይ የሚያስተምረው ምን ነገር ነው የሚል መሆን አለበት ዋናው ነገር መፅሕፍ ቅዱስ ስለ ሴቶች ሚና የሚናገረውን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን አለብን።

አስታውስ እግዚአብሄር ወንድ እና ሴትን ፈጠረ፣ ልዩ አደረጋቸው። አንዱን

ወንድ ሌላዋን ሴት አደረገ፣ ወንዱን አባት ሴቷን እናት እንዲሆኑ አደረገ። አሁን እነዚህን እውነታዎች እና ሚናዎች መቀበል አለብን። አይደል ? አንዲት ሴት ልጅ ማስወለድ ስትፈልግ፣ አንድ ወንድ ደግሞ እንደሴት ልጅ መውለድ ሲፈልግ ምን ዓይነት አስቂኝ ነው? እግዚአብሄር ለእያንዳንዳቸው ሚና ሰጣቸው እና ምንም ያህል ቢፈልጉ መለወጥ አይችሉም፣ እውነታው ግን እግዚአብሄር በሰጠን ሚና ደስተኞች መሆን አለብን፣ የወንዱ ሥራ አስፈላጊ ነው፣ የሰቲቱም ሥራ እንዲው አስፈላጊ ነው፣ አንዱ ያለሌላው ማድረግ አይችልም።

ቅዱሣት መጽሐፍት ስለ አባት እግዚአብሄር እሱ ብሎ ሲናገር "እሷ" ብሎ መጥራት ምንኛ ሞኝነት ነው። ኢየሱስን የመውለድ የማሪያም ሚና እግዚአብሄር ካደረገው ይህንን ማን ሊለውጥ ይችላል? በእውነቱ እነዚህ የሞኝነት ጉዳዮች ናቸው እና ሰይጣን ወንድና ሴትን እርስ በእርስ ለማጋጨትና በዚህም ምክንያት ሁለቱንም ለመጉዳት እነዚህን ዘዴዎች በመጠቀም በጣም ይደሰታል

እርግጥ ነው፣ ምንም ልዩነት ሳይደረግባቸው ወንዶችና ሴቶች በእኩልነት መታየት ያለባቸው ብዙ ቦታዎች አሉ፣ በብዙ የዓለም ክፍሎች በዋና ዋና ኃይማኖቶች መካከል እንኳን ሴቶች በደል ሲፈፀምባቸው፣ ከበስተጀርባ ተጠብቀው እንዲቆዩ እና እንደ አገልጋይ ወይም እንደ መጫወቻ መያዛቸው ያሳዝናል፣ ወንድ ከምንም በላይ በብዙ ሁኔታዎች ነፃ ሴቲቱ ግን ነፃነት አጥታ ከእይታ ተለይታም የምትታይበት አለ፣ መብት የላትም፣ ከባልዋና ከልጆቿ ጋር ወደ አምልኮ ቦታ እንኳን እንድትሄድ አይፈቀድላትም፣ በጣም ትንሽ ስሜት ያላቸው ፍጡራን

ወደ መፅሐፍ ቅዱስ ስንሄድና ወንድና ሴትን በመንፈሳዊ ሁኔታ ስንመለከት፣ እግዚአብሄር ለእያንዳንዱ የተወሰነ ድርሻ እንደሰጣቸው እና እነዚህ ሚናዎች እኩል አስፈላጊ እንደሆኑ እናገኛዋለን። እግዚአብሄር ግን ወንድና ሴትን እርስ በእርሳቸው አላጣላም፣ እርስ በእርሳቸው ለመሪነት ፣ ለኃላፊነት እንዲወዳደሩ አላቋቋማቸውም።

ለምሣሌ ኢየሱስ ታላቁን ተልዕኮ ሲሰጥ በመጀመሪያ ለሐዋሪያት (ሁሉም ሰዎች) ወንጌሉን በደፋ ለዓለም ለማወጅ እንዲወጡ ሥራ ሰጣቸው (ማርቆስ 16፡15~16) ምንም እንኳን በተከታዮቹ መካከል ራሳቸውን ለአምላክ የወሰኑ ብዙ ሴቶች ቢኖሩም የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን ለመመስረት እና አመራር ለመስጠት የመንፈስ ቅዱስ አመራር ቃል የተገባላቸው ሐዋሪያት ናቸው (የሐዋሪያ ሥራ 2) ቦኃላ ጳውሎስ ለሽማግሌዎች እና ለዲያቆናት መመዘኛዎችን በቤተክርስቲያን አጥቢያ ጉባኤ ሰጠ (1ኛ ጢሞተዎስ 3፣ ቲቶ1) እንደገና በእነዚህ ኃላፊነቶች ውስጥ ወንዶች ብቻ ማገልገል ነበረባቸው።

አሁን ይህ ማለት እግዚአብሄር ሴቶችን በቤተክርስቲያን ዝቅ ያደርጋል ወይስ በአጠቃላይ ሴቶችን ያሳንሣል ? በፊፁም አይደለም፣ በእውነቱ የሴቶች

ሥራ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምናልባትም ለብዙዎች ከሚገነዘቡት የበለጠ አስፈላጊ ነው። አንዲት ሴት አስፈላጊ እንድትሆን ወንድ የሚያደርገውን ሁሉ ማድረግ አለባት ብለህ ስትደመድም ማንኛውም ገደቦች በአሉታዊ እይታ ይታያሉ። ይህ በራሱ የሴቲቱን ዋጋ በብዙዎች ዓይን ይቀንሣል፣ ምክንያቱም እግዚአብሄር ያዘጋጀውን ተመሣሣይ አስፈላጊ ሥራ ፈፅሞ ችላ ይላሉ።

"ህፃን የሚያናውጥ እጅ ዓለምን ይገዛል" የሚል አባባል አለ። ያም ማለት ሴትየዋ ልጆቿን ትወልዳለች፣ እነሱን በማሠልጠን ረገድ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል። እና በልጆቿ አማካኝነት ዓለምን ልትገዛ ትችላለች ማለት ነው። እያንዳንዱ ጠቅላይ ሚንስተር፣ ፕሬስዳንት፣ ወይም መሪ በእርሱ ላይ ተፅዕኖ የምታደርግ እናት ነበራጥ በጣም ጥሩ ቢሆንም ልጆቿን እንደእግዚአብሄር ፈቃድ የምታሳድግ እናት ክርስቲያን፣ መሪዎች እና የቤተክርስቲያን ሠራተኞች እንዲሆኑ ተፅዕኖ ሊያሳድርባቸው ይችላል። ዓለምን በተሻለ ሁኔታ ሊለውጡ ይችላሉ፣ እና ነፍሳትን ለዘላለም መለወጥ ይችላሉ፣ ከዚህ የበለጠ ምን ትልቅ ሥራ አለ

እውነት ነው ሴት በቤተክርስቲያን ውስጥ ሰባኪ፣ ሽማግሌ፣ ወይም ዲያቆን ልትሆን አትችልም። እሷም በአምልኮ ውስጥ ዝም ማለት አለባት ማለትም እሷ ስልጣንን በወንድ ላይ አደኖራትም (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡34~38፣ 1ኛ ጢሞተዎስ 2፡11~12)፣ ይህ ማለት ግን  በጉባኤ መዝሙር መሳተፍ አትችልም ወይም ጥያቄ መጠየቅ አትችልም ወይም የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ የተወሰነ ነጥብ መስጠት አትችልም ማለት አይደለም፣ ነገር ግን በአገልግሎቱ ወይም በስብሰባ ላይ ያሉትን ማክበር አለባት ማለት ነው።

ጳውሎስ በመንፈስ ሆኖ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ብሎ ፅፏል "እንግዲህ ቆነጃጅት ሊያገቡ ልጆችንም ሊወልዱ ቤቶቻቸውንም ሊያስተዳድሩ ተቃዋሚውም የሚሳደብበትን አንድን ምክንያት ስንኳ እንድይሰጡ እፈዳለሁ" አለ (1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡14) እንደገና ለቲቶም "እንዲሁም አሮጊቶች ሴቶች አካሄዳቸው ለቅዱስ አገልግሎት የሚገባ፣ የማያሙ፣ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገዙ፣ በጎ የሆነውን ነገር የሚያስተምሩ ይሁኑ፣ ቆነጃጅትም የእግዚአብሄር ቃል እንዳይሰደብ ባሎቻቸውን የሚወዱ ልጆቻቸውን  የሚወዱ ፣ ራሳቸውን የሚገዙ ንፁሆች ፣ በቤት የሚሠሩ፣ በጎዎች፣ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ ይምከሯቸው" ይላል (ቲቶ 2፡3~5)

ጴጥሮስም እንዲህ ይላል "እንዲሁም ሚስቶች ሆይ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ በፍርሃት ያለውን ንፁሁን ኑሯችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው፣ ለእናንተም ጠጉርን በመሸረብና ወርቅን ባማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ  በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁኑላችሁ፣ ነገር ግን በእግዚአብሄር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ  ያለውን የማይጠፋውን

ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ። እንዲህ በቀድሞ ዘመን በእግዚአብሄር ተስፋ ያደረጉት ቅዱሣት ሴቶች ደግሞ ለባሎቻቸው ሲገዙ ተሸልመው ነበርና፣ እንዲሁም ሣራ ለአብረሃም ፦ ጌታ ብላ እየጠራቸው ታዘዘችለት፣ እናንተም ከሚያሰደነግጥ ነገር አንዳች እንኳ ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆቿ ናችሁ፣ እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከሚስቶቻቸሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፣ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል፣ አብረው ደግሞ የህይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሯቸው፣ በመጨረሻው ሁላችሁ በአንድ ልብ ሁኑ የሌላው መከራ ለእናንተ እንደሚሆን አድርጉ እንደ ወንድሞች ተዋደዱ፣ ርኅሩኆችና ትሁታን ሁኑ ክፉን በክፉ ፋንታ ወይንም ስድብን በስድብ ፋንታ አትመልሱ በዚህ ፋንታ ባርኩ እንጂ በረከትን ልትወርሱ ለዚህ ተጠርታችኋልና" (1ኛ ጴጥሮስ 3፡1~9)

ጳውሎስ ቤተክርስቲያንና ክርስቶስን ከባልና ሚስት ጋር ሲያወዳድር እንዲህ ይላል "ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፣ ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና፣ ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንድሁ ሚስቶች ደግሞ ለባሎቻቸው ይገዙ፣ ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ " (ኤፌሶን 5፡22~25)

አሁን አንተ ካለህበት ጋር በተያያዘ ሴቷ የምትጫወተው ሚና ምንድነው? ሴት ከንሸ እና ባለሸበት ቤተክርስቲያን መጀመር ትፈልጊያለሽ ፣ አንድ ወይም ብዙ ለእግዚአብሄር እንደሚታዘዙ ተስፍ በማድረግ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ማጥናት ትፈልጊያለሽ እንደ ሴት እና ሌሎች ሴቶችን ወደ ክርስቶስ መለወጥ ትችይያለሽ፣ መሰብሰብና በአንድነት ማምለክ ትችላለሕ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ወንዶች ከታዘዙ በአምልኮ ውስጥ የህዝብ አመራርን መውሰድ የወንዶቹ ኃላፊነት ይሆናል ፣ ክርስቲያን ሴት ሴቶችን እና ልጆችን በግልም ይሁን በኅብረት እንድታስተምር በጌታ ተፈቅዶላታል (የሐዋሪያ ሥራ 18፡26) በእርግጠኝነት ወንዶችንም ሴቶችንም በግል ልታስተምር ትችላለች እና በጥረቷ የጌታ ቤተክርስቲያን ሊቋቋም ይችላል።

## ትምህርት 20
## ወንጌላዊያንን እንዴት መደገፍ እንደሚቻል

በዚህ ትምህርት ሰባኪዎችን እንዴት መደገፍ እንዳለብን እንነጋገራለን። ባለህበት ጉባኤ ከጀመርክ ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ ወንድሞች የአከባቢውን ሰባኪ እንዴድ መደገፍ እንደሚችሉ ጥያቄ ያነሣሉ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ማድረግ አለብህ?

ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ የፃፈውን እንመልከተ "እኔ ነጻ አይደለሁም? ሐዋሪያስ አይደለሁምን? ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን

አላየሁትምን? እናንተስ በጌታ ሥራዬ አይደላችሁምን? የሐዋሪያነቴ ማህተም በጌታ እናንተ ናችሁና ለሌሎች ሐዋሪያ ባልሆን ለእናንተስ ምንም ቢሆን ሐዋሪያ ነኝ። ለሚመረምሩኝ መልሴ ይህ ነው፣ ልንበላና ልንጠጣ መብት የለንምን? እንደሌሎቹ ሐዋሪያትና እንደጌታ ወንድሞች እንደ ኬፋም እህት ሚስታችንን ይዘን ልንዞር መብት የለንምን? ወይስ ሥራን ለመተው መብት የሌለን እኔና በርናባስ ብቻ ነን?ከቶ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማን ነው? ወይስ ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ማን ነው? ወይስ መንጋ እየጠበቀ ከመንጋው ወተት የማይጠጣ ማን ነው? ይህን በሰው ሥልጣን ብቻ እላለሁን? ሕግስ ደግሞ ያን አይልምን? የሚያበራየውን በሬ አፉን አጸር ተብሎ በሙሴ ሕግ ተፅፎልና ፣ እግዚአብሄርን ስለ በሬዎች ይገዷዋልን? ይህን የሚለው ፈፅሞ ስለእኛ አይደለምን? የሚያርሱ በተስፋ ሊያርስ የሚያበራይም እንዲካፈል በተስፋ ሊያበራይ፣ ስለሚገባው በእውነት ስለእኛ ተጽፎል። እኛ መንፈሳዊን ነገር የዘራንላችሁ ከሆንን የእናንተ የሥጋዊን ነገር እኛ ብናጭድ ትልቅ ነገር ነውን? ሌሎች በእናንተ ላይ ይህን መብት የሚካፈሉ ከሆኑ እኛማ ይልቁን እንዴታ ! ነገር ግን የክርስቶስ ወንጌል እንዳንከለክል በሁሉ እንታገሳለን፣ እንጂ በዚህ መብት አልተጠቀምንም። በመቅደስ ነገር የሚያገለግሉ ከመቅደሱ የሆነውን ነገርን እንዲመገቡ በመሠዊያውም የሚጸኑ ከመሰዊያው እንዲካፈሉ አታውቁምን? እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጓል። እኔ ግን ከእነዚህ ሁሉ ምንማልተጠቀምኩም ፣ እንዲሁ እንዲሆንልኝ ይህን አልጽፍም፣ ማንም ትምክህቴን ከንቱ ከሚያደርግብኝ ሞት ይሻለኛልና ወንጌልን ብሰብክ እንኳን የምመካበት የለኝም፣ ግድ ደርሶብኝ ነውና፣ ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ፣ ይህን በፈቃዴ ባደርገው መጋቢነት በአደራ ተስጥቶኛል እንግዲህ ደመወዜ ምንድነው? ወንጌልን እየሰበኩ በወንጌል ካለኝ መብት በሙሉ እንዳልጠቀም ወንጌልን ያለዋጋ ብናገር ነው” (1ኛ ቆሮንቶስ 9፡1~18)።

በዚህ ሁኔታ ጳውሎስ እንደ ሐዋሪያ እና የጌታ አገልጋይ የነበረውን ነፃነት እያሳየ ነው። ወንጌልን ለመስበክ ከወንድሞች ድጋፍ ሊወድይችል ነበር፣ በዚህ ሁኔታ ግን አላደረገም። በሁኔታዎች ውስጥ ይህ ለበጎ ላይሆን እንደሚችል ተሰምቶት ነበር፣ ሆኖም የቤተክርስቲያን ድጋፍ የተቀበለባቸው ሌሎች አጋጣሚዎች ነበሩ፣ ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ባጻፈው መልዕክቱ እንዲህ አለ “ የፍልጵስዩስ ሰዎች ሆይ፣ ወንጌል በመጀመሪያ ሲሰበክ ከመቄዶኒያ በወጣው ጊዜ፣ ከእናንተ ብቻ በቀር ሌላ ቤተክርስቲያን በመስጠትና በመቀበል ስሌት ከእኔ ጋር እንዳልተካፈለች እናንተ ደግሞ ታውቃላችሁ፣ በተሰሎንቄ እንኳ ሳለሁ፣ አንድ ጊዜና ሁለት ጊዜ ያስፈለገኝን ሰዳችሁልኝ ነበርና። በስሌታችሁ የሚበዛውን ፍሬ እንጂ ስጦታውን ፈላጊ አይደለሁም፣ ነገር ግን ሁሉ አለኝ ይበዛልኝማል፣ የመዓዛ ሽታና የተወደደ መስዋዕት የሚሆነውን ለእግዚአብሄርም ደስ የሚያሰፕውን ስጦታችሁን ከአፍሮዲጡ ተቀብዬ ተሞልቼአለሁ” (ፍልጵስዩስ 4፡15~18)

ጳውሎስ ለሠራተኛ ደመወዙ መከፈሉ ትክክል እንደሆነ ገልጿል፡፡ በተጨማሪም ካህናቱ ወደ መሠዊያው በሚቀርቡት መሥዋዕቶች እንዴት ተካፋዮች እንደነበሩ አንባቢዎችን ያስታውሳል፡፡ ወንጌልን የሚሰብኩም በወንጌል መኖር አለባቸው ሲል ይደመድማል፡፡ በሌላ አነጋገር ሰባኪው በሥራው መደገፍ አለበጥ

በሌላ ጊዜ ደግሞ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ፅፏል "መፅሐፍ፣ የሚያበራየውን በሬ አፉን አጸር፣ ደግሞ ለሰራተኛ ደመወዙ ይገባዋል ይላልና" (1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡18)፣ በዚህ ሁኔታ በጌታ ሥራ ሙሉ ጊዜውን የሰጠ ሽማግሌ እጥፍ ክብር የሚገባው መሆኑን ያሳያል፣ (1ኛ ጢሞተዎስ 5፡17)፣ እሱ ድጋፍ ይገበዋል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ቅዱሣት መጽሐፍት ለጌታ ለሚሠሩ ሰውች ድጋፍ እንደሚሰጡ በጣም ግልፅ ነው፡፡ እውነት ነው አገልግሎቱን የሚያከናውን ሰው ከሌላ ምንጭ ድጋፍ ሊኖረው ስለሚችል አገልግሎቱ ያለ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል ነገር ግን የጌታን ሥራ ሙሉ ጊዜውን ለሰጠ ሰው ከቤተክርስቲያን ደመወዝ መሰጠቱ ምንም ስህተት የለበትም፡፡ ምንም እንኳን አንድ ሰው ከቤተክርስቲያን ጋር የትርፍ ጊዜ ሥራ ብቻ እየሠራ ቢሆንም ለጥረቱ በመመለስ ድጋፍ ማግኘት ይችላል፡፡

እንደተለመደው ዛሬ ተቀጣሪዎች  እንዳሉ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ እነዚህ የሚሠሩት ለደመወዝ ብቻ ነው እንጂ የሚያደርጉትን ስላመኑ ወይም ጌታን ለማገልገል ባላቸው ፍላጎት አይደለም፣ ድጋፍ ለማግኘት ብቻ እንዲሰበክ የተጠየቀውን ሁሉ የሚሰብኩት እነሱ ናቸው፡፡ አየሱስ ይህን በተመለከተ እንዲ ብሏል "እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ የሸሻል፣ ተኩላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል፣ ሞያተኛ ስለ ሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል" (ዮሐንስ 10፡12~13)፡፡ በሌላ አነጋገር ተቀጣሪው ሐቀኛ እና ቅን አይደለም፣ እሱ በሚያደርገው ነገር አያምንም፡፡ እሱ የሚሠራው ለገንዘቡ ብቻ ነው እንጂ ወደ ፊት ጌታ ይመጣል ብሎ አይደለም፡፡ በቤተክርስቲያንም ሆነ በማህበረሰቡ ላይ ከሚያደርሱት ከፍተኛ ጉዳት የተነሣ የዚህ ዓይነት ሰባኪ እንዳይሆን መጠንቀቅ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ኃላፊነት ነው፡፡

አሁን ሰባኪን ለመደገፍ እያሰብክ ነው እንበል  አንድን ሰው ለመምረጥ እንዴት ታደርጋለህ ? በጉባኤ ውስጥ ሊሆን ይችላል ወይም ከሌላ የሀገሪቱ ክፍል ሊመጣ ይችላል፡፡ ለአንድ ሰው በከፍል ወይም በሙሉ ጊዜ ልትደግፈው ነው ማለትም ከፊል ድጋፍ ወይም ሙሉ ድጋፍ ጸጠዋለህ? በመቀጠል ምን ያህል ወርሃዊ ድጋፍ ልታቀርብ ትችላለህ? በቂ ከሌለህ ምናልባት መጀመሪያ ላይ አንዳንድ የእህት ጉባኤ ሊረዱህ ይችላሉ፡፡

ወጣት ሰባኪ ወይም ትልቅ ሰባኪ ትፈልጋለህ? ያገባና ቤተሰብ ያለው ወይስ ያላገባ ትፈልጋለህ? ልምድ ያለው ሰው ትፈልጋለህ? ምን ያህል ልምድ? እርሱን መመርመር ጥሩ ነው፣ ዬት እንደኖረ፣ የሠራው ሥራ ወዘተ ታማኝ

ክርስቲያን ነውን? ዕዳዎቹን ይከፍላል? እሱ ጥሩ የሞራል ሰው ነው?

የመጨረሻውን ምርጫ ከማድረግህ በፊት ሲሰብክ መስማትም ጥሩ ነው። ምን ዓይነት ሰባኪ ነው? ከሰዎች ጋር መግባባት ይችላል? ምክር ሊቀበል ይችላል? ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የመለወጥ ችሎታ አለው? እሱ መሪ ነው? ስለአስተምህሮው ንፁህና እና ጤናማነጽ? በተለያዩ ዶክትሪን ጉዳዮች ላይ ዬት እንደቆመ ማወቅ አለብህ።

ለራሱ እና ለቤተሰቡ ምን ያህል ድጋፍ ያስፈልገዋል? እሱን መደገፍ ከቻልክ እና እሱ የምትጠብቀውን ነገር ከለካ መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው ነገር ላይ ተመሰርተህ መቀጠል ትችላለህ።

የሰባኪው ድጋፍ ከሰባኪውም ሆነ ከማህበረ ቅዱሣን አንፃር ምክንያታዊ መሆን እንዳለበት መጠቆም አለበት። ሰባኪን ከሚገባው በላይ አይከፈለው፣ ከአከባቢው ክርስቲያኖች ለሥራቸው ከሚያገኙት እጅግ የሚበልጥ ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም።

## ትምህርት 21

## የተቸገሩትን እንዴት መርዳት ይቻላል

ጥናታችንን ስንቀጥል ማህበራዊ ጉባኤን የሚመለከት ሌላ ጉዳይ እንመረምራለን፣ የተቸገሩትን መርዳት የምንችለው እንዴት ነው? ሰዎች ሁሉ ከኃጥያታቸው  መዳን ስለሚያስፈልጋቸው ጌታ እንደሚይስፈልጋቸው እናውቃለን። ግን አንድ ጉባኤ ከተቋቋመ እና ማደግ ከጀመረ ቦኃላ አንዳንድ ጊዜ አካላዊ ፍላጎት ያላቸው አባላት ይኖራሉ። በከተማው ውስጥ በተለይ በህይወታቸው ውስጥ ልዩ ችግሮች የሚያጋጥማቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህም የአደጋ ጊዜ ፍላጎቶችን ያስከትላል ቤተክርስቲያን ወንጌልን የመስበክ ተቀዳሚ ሥራ ያላት ቢሆንም አሁንም  በሰው ልጆች መካከል ተገኝታለች እናም ከቤተርስቲያን ውጭ ከሰዎች ጋር እያለች ስለዚህም ልትፈፅማቸው ለምትችለው ሥጋዊ ቀውሶች ደንታ ቢስ ሆና ዓይኗን መጨፈን አትችልም፣ መርዳት አእባት።

ኢየሱስ እንዲህ አለ “የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሣን መላዕክቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፣ አህዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፣ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል፣ በጎችን በቀኙ ፍዬሎችንም በግራው ያቅማቸዋል፣ ንጉሱም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፣ እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፣ ተርቤ አብልታችሁኛልና ፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና ታርዤ አልብሳችሁኛልና ታምሜ ጠቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና ፃድቃንም መልሰው ይሉታል ፡ ጌታ ሆይ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ ? ወይስ ተጠምተህ አይተን

መቼ አጠጣንህ ? እንግዳ ሆነስ አይተን መቼ ተቀበልንህ ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ ? ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን? ንጉሱም መልሶ ፡ እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁ ለእኔ አድረጋችሁት ይላቸዋል፣ በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላዕክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ሂዱ፣ ተርቤ አላበላችሁኝምና ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና ታርዤ አላለበሳችሁኝምና ፣ ታምሜ አልጠየቃችሁኝምና እነርሱ ደግሞ ይመልሱና ጌታ ሆይ ተርበህ

ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገንህም ? ይሉታል። ያን ጊዜ እውነት እላችኋለሁ፣ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል፣ እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ህይወት ይሄዳሉ” ማቴዎስ 25፡31~46)

የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስና የዮሐንስ የአዲስ ኪዳንን አንብበህ ከሆነ ኢየሱስ ርኅሩኅ ሕመም ያለባቸውን እና ሌሎችን የአካል ችግር ያለባቸውን ለመርዳት ፈቃደኛ እነደነበረ ታውቃላችሁ። አሁን ካነበብናቸው ቅዱሣት መጻህፍት የምንረዳው ይመስለኛል፣ ኢየሱስ ህዝቡ ሲጎዱ እንዲራራላቸው ይፈልጋል፣ የተቸገሩትን በመርዳት በእውነቱ ለእርሱ ተመሣሣይ ነገር እናድርግ ብሏል። በአንፃሩ ለጋስ ርህራሄያችንን ጥገኞች ለሆኑት ቸል ካልናቸው ክርስቶስን ራሱ እየናቅነው ነው፣ እንደተመለከትነው የነፍሳችን ዕጣ ፋንታ የሚወሰነው በዙሪያችን ላሉት ፊላጎቶች በምንሰጠው ምላሽ ላይ ነው።

ቤተክርስቲያን በተመሰረተችበት ወቅት፣ አይሁድ የጴንጤቆስጤ በዓልን ለማክበር ከመላው ዓለም እንደመጡ ዘገባው ይገልጻል፣ ወንጌል ተሰብኮ ነበር፣ እናም ሦስት ሺህ የሚያህሉ ጌታን ታዘዙ፣ እነዚህ አዲስ የተለወጡ ሰዎች የክርስቶስን መልዕክት የበለጠ ለመማር እና እርስ በእርሳቸው ለመስማማት ቀጠሉ፣ አንዳንዶቹ በዕለት ተዕለት ፍላጎታቸው እርዳታ ይፈልጉ ነበር፣ የአከባቢው ወንድሞች ምላሽ ሰጡ እና ዘገባው ሲናገር እንዲህ ይላል “ያመኑትም ህዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሯቸው፣ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደሆነ ማንም አልተናገረም፣ ሐዋሪያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፣ በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው፣ በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና፣ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና በሐዋሪያትም እግር አጠገብ ያኖሩ ነበር፣ ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር” (የሐዋሪያት *ሥራ* 4፡32~35) በተለምዶ ክርስቲያኖች መሬታቸውንና ቤታቸውን ሸጠው በፈቃደኝነት እርስ በርሳቸው ይረዳዱ ነበር፣ ያላቸው እየሸጡ ለሌላቸው አካፍለዋል።

ሌላው የምናነበው ደግሞ እርዳታ ባስፈለጋቸው ጊዜ እንዲህ ይነበባል "በዚህም ወራት ደቀመዛሙርቱ እየበዙ ሲሄዱ ከግሪክ ሀገር መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ኖረው በነበሩት አይሁድ አንጎራጎሩባቸው፣ በየቀኑ በተሠራው አገልግሎት መበለቶቻቸውን ቸል ይሉባቸው ነበርና፣ አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርቱ ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሏቸው፣ የእግዚአብሄር ቃል ትተን ማዕድን እናገልግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም፣ ወንድሞች ሆይ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፣ እኛ ግን ለፀሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን" አሉ (የሐዋሪያት ሥራ 6፡1~4) ሐዋሪያት አሥራ ሁለቱ ብቻ ነበሩ ግን ብዙ ደቀመዛሙርት ነበሩ፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለሐዋሪያት የተወሰነ ሥራ እንዲሠሩ ተሰጥቷቸው ነበር፣ የህዝቡ ሥጋዊ ፍላጎት ሲያሳስባቸው ሐዋሪያት እውነትን የተራቡትን ቃሉን ለማስተማር ጊዜያቸውን ሲጠቀሙ ያንን ሥራ ደግሞ ሌሎች እንዲሠሩ ሾሟቸው።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2፣ ጳውሎስ ከገላቲያና ከቆሮንቶስ ወንድሞች በኢየሩሳሌም ላሉ ድሆች ቅዱሣን የሰበሰበውን ስብስብ ሲወስድ እናገኘዋለን። በኋላም በቤተስባቸው ውስጥ ያሉ መበለቶች እንድንከባከቧቸው ነገር ግን በጉባኤ ውስጥ መበለቶች እንደነበሩ ፃፈ አንዲት መበለት የሚረዳት ከሌላትና ዕድሜዋ ስድሳ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናት ከሆነ፣ እና ታማኝ ከሆነች ቤተክርስቲያን ልትረዳት ይገባታል (1ኛ ጢሞተኦስ 5)፣ ነገር ግን ጳውሎስ ለሥጋዊ እርዳታ ወደ ቤተክርስቲያን ከመመለሱ በፊት ሁሉም ሰው ሊያስብበት የሚገባውን መሠረታዊ ሥርዓት አውጥቶአል። "ነገር ግን ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ኃይማኖት የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው" (1ኛ ጢሞተዎስ 5፡8) በሌላ ጊዜ ደግሞ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል " ደግሞ ከእናንተ ጋር ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበር" (2ኛ ተሰሎንቄ 3፡10)።

አሁን በአጥቢያ ጉባኤ ወጣትም ሆነ ሽማግሌ ጥቂቶቸም ሆኑ ብዙ ቤተክርስቲያን የተቸገሩትን እና እርዳታ የሚገባቸውን፣ ሽማግሌዎች ሆነ ወጣት ጥቂቶቸም ሆኑ ብዙ ለመርዳት መሞከር አለባት፣ ይህም ለጊዜው ሥራ የሌለውን፣ አደጋ ያጋጠመውን ሰው፣ ብዙ የህክምና ዕዳ ያለበትን ክርስቲያን ቤቱ የተቃጠለበትን ሰው ወዘተ ሊያካትት ይችላል። ነገር ግን በአከባቢው ያሉ ወንድሞች አባላት ሙሉ ገንዘቡን ስላላቸው ብቻ መስጠት ይችላሉ። ድንገተኛ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንድታግዝ አትጠብቅ። አንዳንድ ቸግሮቻቸውን እንዲረዱ ሌሎች ጉባኤዎቸን ለመጥራት በሚደረግበት ጊዜ ይህ መደረግ ያለበት የህይወትና የሞት ሁኔታ ወይም አንዳንድ የተስፋፋ ጥፋት ከሆነ ብቻ ነው። በማህበሩ ቅዱሣን ውስጥ ያሉ ሰዎች የቤተክርስቲያን ፍቅራዊ አሳቢነት እንዲገነዘቡ

በፀሎት በቤተክርስቲያን ስም መስጠት አለባቸው። ግለሰቦች በእርግጥ ይህን ማድረግ ቢችሉ በግልም ሊረዱ ይችላሉ።

## ትምህርት 22
## እንዴት አብሮ መሥራት እንደሚቻል

ከጭብጡ ጋር በጠበቀ መልኩ፣ አሁን እንደ የጌታ ቤተክርስቲያን አባላት እንዴት በጋራ መስራት እንዳለብን እነወያያለን፣ በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ አንድነትን እንደሚያስተምር ሁላችንም በክርስቶስ አንድ መሆን እንዳለብን ልንረዳ ይገባል። ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ሠራ፣ አንዲት ቤተክርስቲያን ናት፣ እናም ያንን አካል እንድናስተዋውቅ ይፈልጋል፣ (ዮሐንስ 17፡20~23) አንድነትን ለሐዋሪያት እንዲሁም የእነርሱን ትምህርት ለተቀበሉት ሁሉ አንድነትን ፀለየ እንዲህ ብሎ " ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለእነዚህ ብቻ አልለምንም አንተ እንደላክከኝ ዓለም ያምን ዘንድ  አንተ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ፣ እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆን ዘንድ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቼአቸዋለሁ፣ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክከኝ በወደድከኝም መጠነነርሱን እንደወደካቸው ያውቃል" (ዮሐንስ 17፡20~23)

የእግዚአብሄር ህዝብ እርሱን በመታዘዝ ማለትም በመዳን፣ የቤተክርስቲያን አባል በመሆን፣ ስሙን በመልበስ፣ በማምለክና በአንድነት በመሥራት ለእርሱ ታማኝ በመሆን ከተባበር የበለጠ የሚያምር እና ደስ የሚል ነገር የለም። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንዲህ ብሎ ነበር "ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ ሀሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ  መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችዋለሁ" ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡10) መዝሙረኛው ዳዊትም ከዘመናት በፊት እንዲህ ብሎ ነበር "ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው እነሆም ያማረ ነው" (መዝሙር 133፡1)

አንድነት የሚያምር ሲሆን መለያየት ደግሞ አስቀያሚና አጥፊ ነው ፣ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል "ኢየሱስም ግን አሳባቸውን አውቆ እንዲህ አላቸው እርስ በእርሷ የምትለያይ መንግሥት ሁሉ ትጠፋለች፣ እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም" አለ (ማቴዎስ 12፡25)፣ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን ሲወቅስ '"ክርስቶስ ተከፍሎአልን ? ጳውሎሥ ስለእናንተ ተሰቀልን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?" አላቸው (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡13) ለጥያቄዎቹ ሁሉ መልስ "አይደለም" እንደሆነ ያውቃሉ፣ ሰዎችን ከመከተል ክርስቶስን መከተል ትክክል እንደሆነም ያውቃሉ፣ እንደገና ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች እንዲህ ይላቸዋል "ነገር ግን ወንድሞች ሆይ

እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችዋለሁ፤ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፤ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፤ በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ" (ሮሜ 16፡17~18)

አንዳንድ ጊዜ ወንድሞች በአከባቢው ጉባኤ ውስጥ እርስ በእርሳቸው አይግባቡም። ይህ በአስተምህሮ ጉዳዮች ላይ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ችግሮች በግለሰቦች፣ በጥቃቅን ነገሮች፣ በቅናት በምቀኝነት ላይ ሆነው ይከሰታሉ። አንዳንድ ጊዜ ማን ይሰብካል በማለት የበለጠ የሚታይ ትኩረት የሚስብ ወይም ሌላ አስፈላጊ ያልሆነ ነገር ላይ ቁጣ ይነሣል። ይህ የሚያሣዝነው በጉባኤ ውስጥ ያለውን ሥራ ይጎዳል፣ አባል ያልሆኑ ሰዎች በክርስቲያኖች መካከል ያለውን ልዩነት ስለሚያዩ የቤተክርስቲያንን ገፅታን የተበላሸ ያደርጉታል፣ አባላቱ እስከ ተከፋፈሉ ድረስ ሰዎችን ማግኘት ሌላውን ማዳን አስቸጋሪ ይሆናል፣ ጌታ እንድንወደው፣ እንድንዋደድ፣ እርስ በእርሳችን እንድንመሰገን እንድንረዳዳ እና ለሁሉም አባላት እንድንፀልይ ይፈልጋል።

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በአንድ አከባቢ ያሉ ጉባኤዎች እርስ በእርሳቸው አይግባቡም፣ አይተባበሩም እና አብረው አይሠሩም። በወንጌል ስብሰባዎች እርስ በእርሳቸው አይደጋገፉም እና ሌሎች መልካም ሥራዎች ላይ አይደናነቁም እና ብዙውን ጊዜ እንደሂ ዓይነት ሰባኪዎች ይህንን መሰል ነገር በመምራት ጥፋተኞች ናቸው፣ እርስ በእርስ የሚፎካከሩ ያህል ናቸው፣ ይህ መጥፎና ስህተት ነው። እነዚህ የፉክክር ስሜቶች እስካሉ ድረስ ቤተክርስቲያን እንዴት ልታድግ ትችላለች? ይልቁንም ጌታ እነዚህ ጉባኤዎች እና ሰአባኪዎች እርስ በእርሳቸው እንዲተባበሩ እርስ በእርሳቸው እንዲረዳዱ፣ በሚቻልበት ጊዜ እርስ በእርሳቸው በስብሰባ ላይ እንዲገኙ እና በሁሉም መንገድ እንዲተባበሩ ይፈልጋል። ማንም ማህበረ ቅዱሣን ሌሎችን ጉባኤዎች ለመግዛት መሞከር የለበትም እንዲሁም ማድረግ የሚችለውን ወይም የማይችለውን እንገራቸው፣ ግን አንዳቸው የሌላውን የራስ ገዝ አስተዳደር እስከሚያከብሩ ድረስ በእርግጥ ተገቢ ነው እና አብረው እንዲሠሩ ይፈለጋል። ይህንን ትምህርት በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናገኘው ነው።

ከሌላ ጉባኤ ጋር አንዳንድ አለመግባባቶች ቢያጋጥሙን ጉዳዩን ለመፍታት ፍላጎት ይዘን ወደዚያ ግለሰብ ወይም ጉባኤ መሄድ አለብን ክፍፍሉ በአንዳንድ የአስተምህሮ ጥያቄዎች ላይ ከሆነ የሚያስተምረውን ለማየት ወደ መፅሐፍ ቅዱስ መሄድ አለብን፣ ይህንንም በጸሎትና በአምላክ ፊት ትክክል ለመሆን በመፈለግ በጌታ ህዝብ መካከል ያለውን አንድነት ለመጠበቅ የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ እንጣር፣ በአንድም ነገር ልንቆጣና አንድን ሰው ለመጉዳት ወይም ሆን ብለን የሌላ ጉባኤን ለመቃወም መሞከር የለብንም። ብሚፈጠረው

ትንሽ ነገር ሁሉ አኩርፈን ጌታንና ቤተክርስቲያንን መተው የለብንም፣ ከሁሉም በላይ የሚያሳስበን ነገር ጉዳዩን ማስተካከል እና በመንፈሳዊ ሠላም መፍጠር መሆን ይገበዋል።

በጉባኤ ውስጥ ያሉ ወንድሞች አብረው እንዲሠሩና በአከባቢው ያሉ ወንድሞችም እንዲሠሩ ማበረታታት አለብን። እኛ በክርስቶስ ወንድሞች እና እህቶች ነን እና ከዓለም ሰዎች ሁሉ ጋር ስንወዳደር በቁጥር ጥቂቶች ነን። ለእግዚአብሄር በምናደርገው ጥረት አንድ መሆን አለብን። እኛም ልንገነዘበው የሚገባን ትልቅ ሥራ ከፊታችን እንዳለን ማለትም ለጌታ መኖርና ወንጌልን ለዓለም ማድረስ ነው። አንድ ከሆንን ያንን ሥራለመሥራት ጥንካሬ ይኖረናል። በተጨማሪም ፈቃዱን በቅንነት ለመፈፀም ስንጥር ጌታ ከእኛ ጋር ሊሆን የሚችለው አንድ ስንሆን ብቻ ነው።

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እየተወያየን ስለሆነ በዚህ አጋጣሚ ሁላችሁንም ስለአንድነት ኀዛቤ ምን እንደሆነ ልጠይቃችሁ። ሁሉን ኃይማኖተኛ ሰውች የሚፈልጉትን የማመን መብት እንዳላቸው ታምናለህ ነገር ግን በአጠቃላይ አንድ መሆን አለባቸው፣ የክርስቶስ ተከታይ ነህ? የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ነህ? የኃይማኖት ድርጅት አባል ነህ? ስለ አለህበት ቤተክርስቲያን መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያነበብከው ነው? ምናልባት "በክርስቶስ ካመንክ በቂ ሌላው ምን ለውጥ ያመጣል?" ትል ይሆናል ። በጥናታችን ክርስቶስ ስለአንድነት መፀለዩን እናስታውሳለን፣ ጌታ መከፋፈልን እንደሚያወግዝ ከቅዱሣት መፅሐፍት አይተናል። ታዲያ ክርስቶስን አምነን እሱ ካወገዘው ጋር እንዴት እንስማማለን? የቤተክርስቲያኑ አባል ካልህንን እንዴት በክርስቶስ እናምናለን? በዚህ ምድር ላይ የቤተስቡ አባል ካልሆንን እንዴት ወደ ሰማይ እንሄዳለን? በክርስቶስ ካመንን እንዴት በተለያዩ ስሞች ከሚጠሩ ቤተክርስትያን ጋር አብረን እናመልካለን? እነዚህን ጉዳዮች እና የመሳሰሉትን እንደገና እንድታስብባቸው እለምንሃለሁ ቤተክርስቲያኔን፣ ኃይማኖቴን እንድትቀበል እየገፋፋሁህ አይደለም ነገር ግን ከመፅሐፍ ቅዱስ የተማርከውን ሁሉም አንድ ጌታ እንዲታዘዙ፣ በጥንቷ የክርስቶስ የራሱ ቤተክርስቲያን ላይ እንዲጨመሩ፣ ለአንድነት በፀለየው መሠረት አንድ እንድንሆን ለማበረታታት እየሞከርኩ ነው።

ክርስቲያኖች እና የጌታ ቤተክርስቲያን አባል ለሆናችሁ በአጥቢያም ሆነ በሌላ መንገድ መከፋፈል እንደማንችል እና በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት እንዳናጣ እላቸዋለሁኝ። ሁላችንም አንድ ዓይነት ነገር እንድንናገርና ተመሣሣይ ነገር እንድንሠራ ይፈለጋልና እርሱ ጌታ፣ አንድ እንድንሆን፣ የእርሱ መንፈሳዊ የአካሉ ብልት፣ መንፈሳዊ ቤተሰቡ በሀሳብ፣ በንግግር በሥራ አንድ እንድንሆን ይፈልጋልና።

ጳውሎስ ያለውን አስታውስ "እንግዲህ በጌታ እስር የሆንኩ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንዲሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችዋለሁ፣

በትህትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስ በእርሳቸሁ በፍቅር ታገሱ፣ በሠላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ፣ በመጠራታቸሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራቸሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፣ አንድ ጌታ አንድ ኃይማኖት አንዲት ጥምቀት ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ" (ኤፌሶን 4፡1~6)

በአምልኮ፣ በስብከትና በግል ግንኙነታቸን በዓለም ላይ ካሉት ሥራዎቸ ሁሉ የላቀ በሆነው ሥራ አብረን መሥራት እንዳለብን አስታውስ፡፡

## ትምህርት 23

## እንዴት ይቅር ማለት እንደሚቻል

አንተ ባለህበት የክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንዴት መጀመር እንዳለብን በዚህ ጊዜ አጠቃላይ የጥናት መርሆያቸንን እንቀጥላለን፡፡ በዚህ ተከታታይ ትምህርትምክንያት የጌታ ቤተክርስቲያን በብዙ አዳዲስ ስፍራዎቸ እንድትጀምር እጸልያለሁ፡፡ በእርግጥ በዚያ ሥራ እንድትረዱት በአንተ ተስፋ አድረጋለሁ ፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎቸ እንደተናገርኩኝ ጌታን እራስህ ካልታዘዝክ ድረስ ሌላውን መርዳት አትቸልም፣ ይህን ለማድረግ አስቸጋሪ አይደለም የወንጌልን የድነት እቅድ ብዙ ጊዜ እንደተነጋገርን ታውቃለህ ፡፡ መጀመሪያ በእግዚአብሄር ማመን አለብህ (ዕብራዊያን 11፡6)፣ ቀጥሎ ከኃጥያትህ ንሰሃ እንድትገባ፣ ወይም ከኃጥያት መመለስ (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9)ቀጥሎ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን በአፍህ ተናግረህ መመስከር (ማቴዎስ 10፡32) የመጨረሻው ለሓጥያትህ ሥርየት በመቀበር መጠመቅ አለብህ (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38)፣ ያንን ካደረግክ ጌታ ያድንሃል፣ ቤተክርስቲያኑም ላይ ይጨምርሃል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47)፣ እንደ ክርስቲያንና የቤተክርስቲያን አባል እንደመሆንህ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እግዚአብሄርን ማምለክ ትጀምራለህ፣ እንደዚሁም በጌታ ሥራ ትረዳለህ፣ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አንተ ባለህበት ከሌለ አንተው እራስህ እዚያ መጀመር ትቸላለህ ያንን እንደምታደርግ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

አሁን ይቅር ማለት የምንቸ ልበትን ጠቃሚ ርዕስ በመወያየት ተከታታይ ጥናታቸንን እንቀጥላለን

ኃጥያተኞቸ ስለሆንን እንድንበት ዘንድ ጌታ ይቅር እንዲለን አስፈላጊ ነበር፣ ራሱን በመስቀል ላይ መስዋዕት አድርጎ ሰጠ፣ ለዚያም እግዚአብሄርን እናመሰግነዋለን፡፡ ነገር ግን ጌታ ካለፈው ኃጥያት ቢያድነንም፣ እኛ ሰዎቸ ነን ለኃጥያት የተገዛን ነን፣ ስለዚህም ይቅርታን እንፈልጋለን፣ እኛም የበደሉንን ይቅር ማለት አለብን፣ ይህንን እንዴት ማድረግ እንዳለብን ካልተማርን እና ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆንን እራሳቸንን ይቅር ማለት አንቸልም፣ ይቅር መባልም አንቸልም፡፡ ይህ ትምህርት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ማየት ይቸላሉ፡፡

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ሲያስተምር እንዲህ አለ "እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን" በሉ አለ (ማቴዎስ 6፡12) ማስተማሩን ሲቀጥል "ለሰዎች ኃጥያታቸውን ይቅር ብትሉ፣ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችዋልና፣ ለሰዎች ግን ኃጥያታቸውን ይቅር ባትሉ፣ አባታችሁም ኃጥያታችሁን ይቅር አይላችሁም" አለ (ማቴዎስ 6፡14~15)
ጌታ ይቅር እንዲለን መጠበቃችን እና የበደሉንን ይቅር ለማለት ፈቃደኛ አለመሆናችን እንግዳ ነገር አይደለምን? ጌታ በዚህ መንገድ የማይሠራ መሆኑን ልናውቅ ይገባል ብሏል። ይቅር ካላልን ይቅር አይለንም። ስለዚህ እግዚአብሄር ይቅር እንዲለን ከጠበቅን የበደሉንን ይቅር ማለት አለብን። በቃ ቀላል ነው፣ ይቅርታ የአንድ ወገን ብቻ መሆን የለበትም።

ጳውሎስ ለቆላስያስ ክርስቲያኖች እንዲህ ይላል "እንግዲህ እንደ እግዚአብሄር ምርጦች ቅዱሣን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፣ ምህረትን፣ ርኅራኄን ቸርነትን፣ ትህትናን፣ የዋህነትን፣ ትዕግሥትን ልበሱ፣ እርስ በእርሳችሁ ትዕግሥት አድርጉ፣ ማንም በባለንጀራው ላይ የሚነቀፈው ነገር ካለው ይቅር ተባባሉ፣ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ" አለ (ቆላስያስ 3፡12~13)።

እኔ እንደማስበው ሌሎች በእኛ ላይ ኃጥያት ከሠሩ እና እኛን ይቅርታ ከጠየቁ እኛ ይቅር ልንላቸው ይገባል። እነሱ ባጠይቁንም እኛ በእርግጥ ይቅር ለማለት ፈቃደኛነት አለንና በእነሱ ላይ ቂም መያዝ የለብንም።
ነገር ግን በእግዚአብሄር እና በባለንጀራችን ላይ ኃጥያት ከሠራንስ ? እንዴት ይቅርታ ሊኖረን ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ በግልም ኃጥያት ከሠራን ማለትም ኃጥያቱን የምናውቀው እኛና እግዚአብሄር ብቻ ከሆነ ከዚያ ኃጥያት ንሠሀ ገብተን እግዚአብሄር ይቅር እንዲለን ልንጠይቀው እንደሚገባ ያስተምራል። በዚህ ሁኔታ ከዚህ በላይ ምሄድ አያስፈልግም።

በአንድ ሰው በደል ከሠራን ወይም ካጠፋን እርሱ ጋ ሄደን መጸጸታችንን ጠይቀን ይቅርታ መጠየቅ አለብን፣ ምህረቱን ይቅር ባይነቱን መጠየቅ አለብን እና ይኼው ነው።

ነገር ግን በይፋ ኃጥያትን ከሠራን እና በጌታ እና በቤተክርስቲያኑ ላይ ውርደትን ካመጣን፣ ከቤተክርስቲያን በፊት ሄደን ለኃጥያታችን ንሠሀ በመግባት ስህተታችንን በአደባባይ መናዘዝ አለብን። በሐዋሪያት ሥራ 8 ላይ ጠንቋይ የነበረለመዳን ጌታን የታዘዘ እና የቤተክርስቲያን አባል የሆነው ስምኦን የሚባል ሰው፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለሳማርሪያዊያን ክርስቲያኖች እጅ በመጫን ኃይል ሲሰጡ ባዌ ጊዜ ለዚህ ኃይል ገንዘብ ሊሰጣቸው ተፈተነ፣ ዘገባው ሲናገር እንዲህ ይላል "ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው፣ የእግዚአብሄርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ ፣ ልብህ በእግዚአብሄር ፊት ቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፋንታ የለህም። እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ

ንሰሀ ግባ ምናልባትም የልብህን ሀሳብ ይቅር ይልህ እንደሆነ ወደ እግዚአብሄር ለምን በመራራ መርዝና በዓመፅ እስራት እንዳለህ አይሃለሁና ። ሲሞንም መልሶ ፦ካላችሁት አንዳች እንዳይደርስብኝ እናንተው ወደ ጌታ ለምኑልኝ" (የሐዋሪያት ሥራ 8፡20~24) ስለዚህ ስማኦን ተፀፅቶ ተመለሰ፣ ነገር ግን ኃይሉን አላግባብ እንዲጠቀምበት እንዳይፈተን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደተሰጠው የሚጠቁም ምንም መረጃ የለንም

ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ስለነበረው ወጣት ታሪክ ተናገረ ሁሉንም ነገር ስላለው ነገር ግን ርስቱን ወስዶ ለመሄድ ወሰነ፣ እንዳሰበውም አደረገ ርስቱን ሁሉ አባክኖ ባዶ ሆነ፣ እናም እራሱን ለማዳን የእሪያን ምግብ ሁሉ ተመኘ ዘገባው እንዲህ ይላል "ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ፣ እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ፣ ተነስቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና፣ አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፣ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፣ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ፣ ተነስቶም ወደ አባቱ መጣ፣ እርሱም ገና ከሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፣ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው፣ ልጁም አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፣ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም አለው፣ አባቱ ግን ባሪያዎቹን አለ፣ ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፣ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ የሰባውን ፊሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፣ እንብላም ደስም ይበለን፣ ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፣ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም። ደስ ይላቸው ጀመር" (ሉቃስ 15፡ 17~24) ይህ ታሪክ የሚያሳየው ከእግዚአብሄር የምንርቅ ከሆነ፣ ንሠሀ ከገባንና ጥፋታችንን ከተናዘዝን፣ አባታችን ይቅር ሊለንና ሊመልሰን ፈቃደኛ መሆኑን ነው፣ ያዕቆብ ሲናገር "እርስ በእርሳችሁ በኃጥያታችሁ ተናዘዙ፣ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለሌላው ይፀልይ፣ የፃድቅ ሰው ፀሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች" (ያዕቆብ 5፡16)

አሁን በሌ በኩል ስናይ አንድ ሰው ቢበድለንስ ? በዚህ ጉዳይ ክርስቶስ እንዲህ ይላል "ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው፣ ቢሰማህ ወንድምህን ገንዘብ አደረግከው፣ ባሰማህ ግን በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲፀና ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ፣ እርሱንም ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገራት፣ ደግሞም ቤተክርስቲያንን ባይሰማት እንደአረመኔና እንደቀራጭ ይሁንልህ፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል" አለ (ማቴዎስ 18፡ 15~18)

አንድ ሰው በእሱ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ከተፈለገ ኃጥያት በጌታ ተፀፅቶ ይቅር ሊለው ይገባል። ቤተክርስቲያን በተቻለ መጠን ንጹህ እንድትሆን እነዚህን እውነቶች በአጥቢያው ጉባኤ በመጀመር ልታስታውሱ ይገባል።

## ትምህርት 24
## ንፁህ አስትምህሮ እንዴት እንደሚኖር

አንተ ባለህበት የክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንዴት መጀመር የሚለውን መሪ ሀሳብ በመጠቀም አንተን ሊረዱ የሚችሉትን መረጃ ልንሰጥህ ዓላማችን መሆኑን እንድታስተውል እንፈልጋለን፡፡

እንደ መረጃው አካል እዚህ ያለው ትምህርታችን የአስተምህሮ ንጽህናን እንዴት እንዲኖር ማድረግ እንዳለብን ከማወቅ ጋር የተያያዘ ነው፡፡
የአስተምህሮ ንጽህና ስንል ምን ማለታችን ነው እና ለምንስ አስፈላጊ ነው? እየተናገርን ያለነው አንድ ሰው እንዲድን ስለሚያስችሉ ስለ ትምህርቶቹ፣ ትምህርቱ ስለእነዚያ እውነት በመስበክ ላይ ነው፡፡

እግዚአብሄር እንደ ተናገረ እናውቃለን (እብራዊያን 1፡1~2) ክርስቶስ ቃል ነው ተብሏል (ዮሐንስ 1፡1~2) መንፈስ ቅዱስ ሐዋሪያቶቹን የጌታን መልዕክት እንዲፅፉ መርቷቸዋል ( 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16~17፣ 2ኛ ጴጥሮስ 1፡21) በሌላ አገላለፅ እግዚአብሄር ፈቃዱን እንድናውቅ ፈልጓል፣ እናም ይህንን ፈቃዱን በመፅሐፍ ቅዱስ ገፆች እና በተለይም በዘመናችን በሚሠራው በአዲስ ኪዳን ገጾች ላይ ሰጠን፡፡

ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም ከተመሰረተች ቦኋላ የምናነበው እንዲህ የሚል ነበር "በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር" ይላል (የሐዋሪያት *ሥራ* 2፡42) የሐዋሪያቶቹ ትምህርት ምን ነበር ? ከክርስቶስ የተማሩት ነበር፣ ስለዚህም ደቀመዛሙርቱ በዚህ ትምህርት ተይዘዋል፣ ስለዚም በሐዋሪያት ትምህርት በኅብረትም እንጀራውንም በመቁረስ በየ ፀሎቱም ይተጉ ነበር ይለናል፡፡

ጳውሎስስለጤናማአስተምህሮበተለያዩአጋጣሚዎችተናግሯል፡፡የዓለም ኃጥያት ከእውነተኛ ትምህርት ጋር የሚቃረኑ ናቸው ብሏል (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡10) በሌላ ጊዜ ደግሞ ሰዎች ጤናማ ትምህርት የማይታገሱበት ጊዜ ይመጣል ብሏል (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1)፣ ስለ ሽማግሌዎች ወይም ጳጳሳት መመዘኛዎች ሲናገር እንዲህ ብሏል፡፡ "ኤጵስ ቆጶስ እንደ እግዚአብሄር መጋቢ፣ የማይነቀፍ ሊሆን ይገበዋልና፣ የማይኮራ፣ የማይቆጣ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ፣ ነውረኛ ረብ የማይወድ፣ ነገር ግን እንግዳ ተቀባይ፣ በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ ጠንቃቃ፣ ጻድቅ፣ ቅዱስ፣ ራሱን የሚገዛ ይሁን፣ ህይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ ሊመክር ተቃዋሚዎችንም ሊወቅስ ይችል ዘንድ እንደተማረው በታመነ ቃል ይጽና" (ቲቶ 1፡7~9)
አስተውል ለሽማግሌዎች መመዘኛዎች መሳተፍ በእምነት ጤናማ መሆን ወይም ባመኑት ነገር ጤናማ ለመሆን መፈርቱ ነው፡፡ ነገር ግን በእምነት ጥጤናማ ለመሆን ጤናማ ትምህርት (የእግዚአብሄር ፈቃድ) ሲሰበክ

መስማት ይኖርበታል፣ እምነት የሚመጣው የእግዚአብሄርን ቃል መስማት ነው (ሮሜ 10፡17)፣ በቲቶ 2፡7~8ላይ ጳውሎስ እንዲህ ይላል "የሚቃወም ሰው ስለእኛ የሚናገረውን መጥፎ ነገር ሲያጣ እንዲያፍር፣ በነገር ሁሉ መልካምን በማድረግህ ምሣሌ የሚሆን ራስህን አሳይ፣ በትምህርትህም ደህንነትን፣ ጭምትነትን፣ ጤናማና የማይነቀፍ ንግግርን ግለጥ" (ቲቶ 2፡7~8)።

ያነበብናቸው ቅዱሣት መጻሕፍት ሁሉ በአፅናኦት የሚያተኩሩት "ጤናማ ትምህርት" "ታማኝ ቃል" እና "ጤናማ ንግግር" የሚሉ ናቸው፣ እነዚህ አስፈላጊ የሆኑበት የጌታን ትምህርት፣ በመጀመሪያ እንደተሰጠ እንድንጠብቅ እና ከሐሰት ትምህርት እንድንጠብቅ ለማስታወስ ነው፣ ጳውሎስ በመቀጠል እንዲህ ይላል "ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችዋለሁ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፣ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፣ በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ" ይላል (ሮሜ 16፡17~18)

ጳውሎስ ወጣቱን ሰባኪ ጢሞቴዎስን ሲያበረታታ እንዲህ ይላል "እንግዲህ ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ፣ ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሉ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ" ይለዋል (2ኛጢሞተዎስ 2፡1~2) ይቀጥልና "በእግዚአብሄር ፊት በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በመገለጡና በመንግሥቱም እመክርሃለሁ፣ ቃሉን ስበክ፣ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፣ ፈፅመህ እየታገስህና እያስተማርህ ዝለፍና ገስፅ ምከርም፣ ህይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣልና፣ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ፣ እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ" አለው (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1~4)። ጴጥሮስም እንዲህ ይላል "ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን እንደእግዚአብሄር ቃል ይናገር ፣ የሚያገለግልም ቢሆን፣ እግዚአብሄር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፣ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሄር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ አሜን" ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 4፡11)

እነዚህን ማስጠንቂቃዎች እንደ ዳራ በመያዝ የእውነትን፣ ጤናማና የታማኝነትን ትምህርት አስፈላጊነት በማሳየት፣ ባለህበት ጉባኤ ልታቋቋመው ከሆነ እንደ እግዚአብሄር ቃል ትምህርት መከናወን እንዳለበት ልንገርሕ በአንተ ኅብረት ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የተማሩ እና የታዘዙትን ብቻ ማለትም በእግዚአብሄር ያመኑ፣ ከኃጥያታቸው ንሠሀ የገቡ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ያላቸውን እምነት የመሰከሩ፣ እና ለኃጥያታቸው ሥርየት የተጠመቁ (ማርቆስ 16፡15~16፣ ሮሜ 10፡10፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡38)፣ የሐዋሪያት ሥራን በምታነብበት ጊዜ ብዙ

የመመለስ ወይም የለውጥ ጉዳዮችን ታገኛለህ። ሁሉም ለእነዚያ ተመሣሣይ እውነቶች ታዘዙ እና በውጤቱም ጌታ አዳናቸው እና ወደ ቤተክርስቲያኑም ጨምሮአቸዋል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47)፣ በዮሐንስ 3፡3~5፣ መለወጥ እንደ አዲስ ልደት ተመስሏል፣ በሮሜ 6፡3~4፣ እና 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13፣ አንድ ሰው እነዚህን ትዕዛዛት ሲፈፅም ወደ ክርስቶስ እና ወደ ቤተክርስቲያኑ እነደሚገባ ተናግሯል።

በአጥቢያው ምዕመናን የመዳንን ወንጌል እቅድ ያስተምራሉ፣ እና ደግሞ አንዲ ቤተክርስቲያን እንዳለች ያስተምራሉ፣ ክርስቶስም የሠራት ኢየሱስ ራስ የሆናት፣ በእርሱም ላይ የታነጸች፣ ስሙን የለበሰች ክርስቶስ ስለእርሷ የሞተላት አዳኝ የሆናት፣ አንድ ቀንም ተመልሶ የሚወስዳት (ማርቆስ 16፡15~16፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 3፡1፣ ሮሜ 16፡16፣ የሐዋሪያት ሥራ 20፡28፣ ኤፌሶን 5፡23~27፣ ኤፌሶን 4፡4~6) እነዚህን መግለጫዎች የገለፅኳቸው የቅዱሣት መፃሕፍት ማጣቀሻዎች ናቸው።

በአከባቢው ያለው ጉባኤ ወይም ማህበር በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን በመሰብሰብ፣ ለመዘመር፣ ለመፀለይ፣ ቃሉን ለማጥናት፣ የጌታን እራት ለመካፈል እና ጌታ እንዳበለፀጋቸው ካገኙት ላይ ስጦታ በመስጠት ያመልካሉ (የሐዋሪያት ሥራ 20፡7፣ ኤፌሶን 5፡19፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡23~29፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2)

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባላቱን በቅድስና እንዲኖሩ ትመክራለች "ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሄር ጸጋ ተገልቶአልና፣ ይህም ጸጋ ኃጥያተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፣ ራሳችንን በመግዛትና በፅድቅ እግዚአብሄርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፣ መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዡን መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ህዝብ ለራሱ እንዲያነጻ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል ይህን በሙሉ ሥልጣን ተናገርና ምከር ገስርዝም፣ ማንም አይናቅህ" ብሏል።(ቲቶ 2፡11~15)

ቤተክርስቲያን፣ ጉባኤ፣ ወይም የአከባቢ ማህበር መጽሐፍ ቅዱስ በሚናገርበት ቦታ መናገር እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ዝም ሲል ዝም ትላለች በእግዚአብሄር ቃል ላይ መጨመር ወይም ከዚያ ላይ መቀነስ፣ ወይም የተፃፈውን በሌላ ላለ መተካት ጥረት ታደርጋለች (ራዕይ 22፡18~19፣ ገላቲያ 1፡6~9)

የጌታን ትምህርት ወይም ዶክትሪን ንጹህ ሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ ምርጡ መንገድ እያንዳንዱ አባል የእግዚአብሄርን ቃል ማንበብና ማጥናት እና በደንብ ማወቅ ነው (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15)። በዚህ መንገድ አምላክ ከእነሱ የሚፈልገውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ከማንኛውም የሐሰት ትምህርቶችም ሊጠበቁ ይችላል፣ በዚህም እውነትን ያውቃሉ እውነትም አርነት ያወጣል

(ዮሐንስ 8፡32)፡፡

## ትምህርት 25
## የክርስትና ህይወት እንዴት መኖር እንዲሚቻል

አጠቃላይ ጭብጣችን የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ባለህበት እንዴት መጀመር እንጋለብህ ነው ይህም ይቀጥላል፣ ቤተክርስቲያን ምን እንደሆነች እና ምንስ እንዳልሆነች ማወቅ አስፈላጊ ነው፣ ቤተክርስቲያን የዳኑ ሰዎች ስብስብ ናት፣ በእግዚአብሄር በማመን፣ ከኃጥያታቸው ንሰሀ በመግባት፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መስክረው እና ለኃጥያት ሥርየት የተጠመቁ እና የዳኑ ሰዎች ስብስብ ናት ቤተክርስቲያን ይህቺ ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በክርስቶስ ነው፣ እርሱ ራሷ ነው፣ እናም እርሱ አዳኟ ነው፣ ቤተክርስቲያንና አማኞቹ ክርስቲያኖች የለበሱት ያዳቸውን ያወቃቸውን የክርስቶስን ስም ነው፡፡ በሌላ በኩል ቤተክርስቲያን ግንብ ወይም ህንፃ ሳትሆን የዳኑ ሰዎች ናት ፣ ቤተክርስቲያን ሰው ሰራሽም አይደለችም፡፡

በዚህ ተከታታይ ትምህርት ስንቀጥል፣ አሁን እንዴት የክርስትናን ህይወት መምራት እንዳለብን እንወያያለን/ የቤተክርስቲያን አባላት ልንሆን እና ባለንበት ቤተክርስቲያን እንዲኖረን ከፈለግን የክርስትናን ህይወት መምራት አለብን፣ የክርስትናን ህይወት በታማኝነት እስካልመራን ድረስ ክርስቲያን መሆን እንኳን አያስፈልግም፣

ክርስቲያን ለመሆን አንድ ሰው በክርስቶስ ያለውን እምነት የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መመስከር አለበት፡፡ በሐዋሪያት ሥራ 8 ላይ ከኢትዮጵያ ሰው ጋር ስለ ተደረገ ውይይት እናነባለን እና ከመጠመቁ በፊት ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ ብሏል ፡፡ ሮሜ 10፡10 ጳውሎስ ይህ መስክርነት ለመዳን እንደሚያገለግል ይናገራል ነገር ግን አንድ ሰው ለመዳን በህይወት ዘመኑ ሁሉ የክርስቶስን ስም መመስከር ብቻ አይጠበቅበትም፣ ማለትም እርሱ ክርስቶስን በአፉ ለመመስከር ዝግጁ ብቻ ሳይሆን በአኗኗሩም ክርስቶስን በየቀኑ መመስከር አለበት፡፡

አንድ ሰው ክርስቶስን በመታዘዙ ድኗል እናም ወደ ቤተሰቡ ማለትም ወደ ቤተክርስቲያን ተጨምሯል፣ አሁን ዳግም የተወለደ ነው፡፡ (ዮሐንስ 3፡3~5)፣ ስለዚህም እርሱ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነው፣ ጳውሎስ ሲናገር "ስለዚህም ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፡፡ አሮጌው ነገር አልፏል፣ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል" (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17)
ነገር ግን በክርስቶስ መሆን እና የእርሱ መሆን ምን እንደሚመስል እንመርምር፡፡ ጳውሎስ ለቆላስይስ ወንድሞች ሲፅፍ እንዲህ ይላል "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣ ክርስቶስ በእግዚአብሄር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ፣ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም፡፡ ሞታችኋልና

ህይወታችሁም በእግዚአብሄር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሯልና፣ ህይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ፣ እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፣ እነዚህም ዝሙትና ርኩሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣኦትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው። በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሄር ቁጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣል፣ እናንተም ደግሞ ትኖሩባቸው በነበራችሁ ጊዜ በፊት በእነዚህ ተመላለሳችሁ፣ አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቁጣንና ንዴትን ክፋትንም ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ። እርስ በእርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፣ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፣ የፈጠረውንም ምሣሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታልና፣ በዚያም የግሪክ ሰው አይሁዳዊም የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፣ ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው፣ በሁሉም ነው፣ እንግዲህ እንደ እግዚአብሄር ምርጦች ቅዱሣን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፣ ምህረትን፣ ርኅራኄን ፍርሃትን፣ ትህትናን፣ የዋህነትን፣ ትዕግሥትን ልበሱ። እርስ በእርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፣ ማንም በባለንጀራው ላይ የሚነቀፈው ነገር ካለው ይቅር ተባባሉ፣ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፣ በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍፃሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት፣ በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ፣ የምታመሰኙም ሁኑ፣ የእግዚአብሄር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፣ በጥበብ ሁሉ እርስ በእርሳችሁ አስተምሩና ገሥፁ፣ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሄር ዘምሩ። እግዚአብሄር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ፣ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት" (ቆላስይስ 3፡1~17)።

ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለዘመኑ ክርስቲያኖች ሲናገር እና እንዴት በተአምራዊው ኃይል ላይ ተመርኩዘው ቤተ ክርስቲያን እንድትጀመር እና ወደ በሳልነት እንድታድግ የረዳቸውን የጳውሎስን ቃላት ማንበብ ስንቀጥል "እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋሪያት ሌሎቹም ነቢያት፣ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፣ ሁላችን የእግዚአብሄርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፣ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፣ የክርስቶስም ሙላት ልክ እስከንደርስ ድረስ ቅዱሣን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንፃ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ፣ እንደ ስህተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ህፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም፣ ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፣ ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፣ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ ራሱን በፍቅር በማነፅ አካሉን

ያሳድጋል። እንግዲህ አህዛብ ደግሞ በአዕምሯቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትመላለሱ እላለሁ በጌታም ሆኜ እመሰክራለሁ። እነርሱ ባለማወቃቸው ጠንቅ በልባቸውም ደንዳናነት ጠንቅ ልቦናቸው ጨለመ፣ ከእግዚአብሄርም ራቁ ፣ ደንዝዘውም በመመኘት ርኩሰትን ሁሉ ለማድረግ ራሳቸውን ወደ ሴሰኝነት አሳልፈው ሰጡ፣ እናንተ ግን ክርስቶስን እንዲዚህ አልተማራችሁም፣ በእርግጥ ሰምታችሁታልና፣ እውነትም በኢየሱስ እንዳለ በእርሱ ተምራችኋል። ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፣ በአዕምሯችሁም መንፈስ ታደሱ፣ በእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሄር ምሣሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ። ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፣ እርስ በእርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባለንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ፣ ተቆጡ ኃጥያትንም አታድርጉ፣ በቁጣችሁ ላይ ጸሐይ አይግባ፣ ለዲያብሎስ ፈንታ አጽጡት፣ የሰረቀ ከእንግዲህ አይስረቅ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም፣ ለሚሰሙት ጸጋን ይሰR ዘንድ፣ እንደሚያስፈልግ ለማነፅ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ፣ ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሄርን መንፈስ አታሳዝኑ፣ መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ፣ እርስ በእርሳችሁም ቸሮችና ርሳሮኆች ሁኑ እግዚአብሄርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ” (ኤፌሶን 4፡11~32)

በእነዚህ ከላይ ባየሃቸው ቅዱሳት መጽሐፍት ክርስትና እግዚአብሄራዊ ኑሮ እንዴት እንደሚኖር፣ እግዚአብሄርን እንዴት እንደምናገለግል እና ሌሎችን እንዴት መርዳት እንደምንችል ያስተምረናል

ለጌታ በመታዘዛችን ላይ የክርስቶስን ስም ይዘናል (የሐዋሪያት ሥራ 11፡ 26፣ 1ኛ ጴጥሮስ 4፡16)፣ ይህንን በአድረግ እናከብረዋለን፣ እናም እንደ ጌታችን እና አዳኛችን እንሰብከዋለን እኛ በእርሱ እንደምንኖር እርሱ ደግሞ በእኛ እንደሚኖር ነው የምንናገረው፣ ስለዚህ የጌታን ስም ልንወስድ ብቻ ሳይሆን በየቀኑ ክርስቶስን በተግባራችን ልንመሰክር ይገባናል
ወጣት ጉባኤ አባላትም ሆንን የሽማግሌዎች ጉባኤ አባላት ብንሆን፣ ወይም በቁጥር ትንሽም ሆንን ብዙ አሁንም ማን እንደሆንን እና የምንወክለውን ማስታወስ አለብን።

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያን እንድንሆን በሰጠነው ምክንያት ሁሉ ካለው ሁኔታ የተነሣ ልናዝን ከባድ እንደሆነም አስበን “ባልሆንኩ” ብለን እናስብ ይሆናል። ነገር ግን ጌታ ተስፋ እንድንቆርጥ አልነገረንም ነገር ግን ከመጥፎና ስህተት ከሆነ ነገር በንሠሀ እንድንመለስ ነው የነገረን። ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ህይወታችን ጌታ ይሠራል፣ ከእኛ ጋር እንደሚሆን እና ሊረዳን ቃል የገባልን ጌታ

አለን፣ አባታችንን ለእርዳታ የምንጠራበት ፀሎት አለን፣ ወድሞቻችን ይረዱናል ያበረታቱናል፣ ስለዚህ ክርስትና ከዬትኞቹም የበለጠና የተባረከ ነው፡፡

## ትምህርት 26

## ችግሮችን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል

ለዚህ ሁሉ ተከታታይ ትምህርት ከእኝዝ ጋር የነበራችሁ ሰዎች በአሁን ጊዜ የጌታችንን ቤተክርስቲያን እንዴት አባል መሆን እንደሚችሉና አንተ ባለህበት ጉባኤ እንዴት ቤተክርስቲያን መጀመር እንደምትችል በደንብ እንዳወቃችሁ አምናለሁ፣ ይህንን እያሰብኩኝ ስንቶቻችሁ በቁምነገር በዚህ ጉዳይ እንደምታናግሩን ስገምት ያስደንቀኛል፣ ብዞቻችሁ እንደምትሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ፣ እናም በእነዚህ ጥናት ውጤት በዓለም ዙሪያ ብዙ የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ይፈጠራሉ ብዬም ተስፋ አደርጋለሁኝ

አሁን ወደ አንድ ትምህርት ደርሰናል ይህም ችግሮችን እንዴት መቋቋም እንደሚቻላ የሚመለከት ነው፡፡ አዎን በመንገዱ ላይ የሚነሱ ችግሮች ይኖራሉ፣ መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች ይነሣሉ፣ ምናልባት ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹን በማሰላሰል እና አንዳንድ መልሶችን ለመስጠት መሞከር አብረው ሲመጡ ይጠቅማቸኋል

ከብዙ ዓመታት በፊት ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ ነበር "ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባቸሁ ቀድሱት፣ በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፣ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን" (1ኛ ጴጥሮስ 3፡15)

ቅዱሣት መፃሕፍትን በራሳችን የመተርጎም መብት አለን? ጴጥሮስ ሲናገር እንደገና ስማው "ይህንን በመጀመሪያ እወቁ፣ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፣ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ዳሩ ግን በእግዚአብሄር ተልከው ቅዱሣን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" (2ኛ ጴጥሮስ 1፡20~21)

መጽሐፍ ቅዱስ መዳን በእምነት ብቻ እንደሆነ ያስተምራል? እኛ የዳንነው በእምነት ቢሆንም በእምነት ብቻ ግን አይደለም፡፡ አንድ ሰው በእውነት ካመነ ወይም የሚያድን ዓይነት እምነት ካለው፣ ጌታ እንዲያደርግ የጠየቀውን ያደርጋል፣ እንደዚህ ዓይነት እምነት ከሌለው መዳን አይቻልም ፣ ክርስቶስ እንዲህ አለ "ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈርድበታል" (ማርቆስ 16፡16) ክርስቶስ ሲናገር የአባቱን ፈቃድ ማድረግ እንዳለብን ገልጾአል (ማቴዎስ 7፡21)፣ ያዕቆብ ሲናገር "ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ" ይላል (ያዕቆብ 1፡22)፣ ይቀጥልና "እንዲሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው" ይላል (ያዕቆብ 2፡17)

ጥምቀት እንዴት ያድናል? እንደ እምነት እሱም ብቻውን አያድንም፣

ጥምቀት የሚመጣው በጌታ ካመነ፣ ንሠሀ ከገባ ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ከመሰከረ ቦኃላ በውኃ ውስጥ በመቀበር ይጠመቅና ይድናል (ዕብራዊያን 11፡6፣ ሉቃስ 13፡3፣ ማቴዎስ 10፡32፣ ሮሜ 6፡3~4)

ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ ብዙ መንገዶች አሉን? ክርስቶስ እንዲህ አለ "ኢየሱሥም እኔ መንገድና እውነት ህይወትም ነኝ፣ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለ" አለ (ዮሐንስ 14፡6) ሌሉ ቦታም እንዲህ ብሏል "እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንብዴም ነው" አለ (ዮሐንስ 10፡1) ጌታ በዚህ ላይ ራሱን ከገለፀ ቦኃላ፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ስንት መንገዶች አሉ ብለህ ታስባለህ? ሌሎች መንገዶች ካሉ ጌታ ለምን እኔ ብቻ ነኝ መንገድ ይል ነበር?

የዬትኛውም ቤተ ክርስቲያን አባል ሳይሆን መዳን እና መንግሥተ ሰማይ መሄድ አይቻልም? እውነት ነው አንድ ሰው የኃይማኖት ድርጅት እና ሰው ሰአሽ አቢያተ ክርስቲያናት አባል ሆነው ድነናል ማለት ይችላሉ፣ነገር ግን በዚህ ዓለም እና በሚመጣው ዓለም ለመዳን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን አለበጥ ነገር ግን የክርስቶስ ቤተክርስቲያንም አታድንም፣ ታድናለች ? አይደለም ክርስቶስ የቤተክርስቲያን አዳኝ ነው (ኤፌሶን 5፡23) ስለዚህ አንስ ሰው ለመዳን በቤተክርስቲያን ውስጥ መሆን አለበት ፣ ኖህ የሰራው መርከብ አዳኝ አልነበረም፣ ነገር ግን ኖህ እና ቤተሰቡ ለመዳን በመርከቡ ውስጥ መሆን ነበረባቸው። ጳውሎስ በመጨረሻ ክርስቶስ የእግዚአብሄርን መንግሥት ወይም ቤተክርስቲያንን ለአባቱ አሳልፎ እንደሚሰጥ ተናግሯል (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡24) እንግዲህ ለእግዚአብሄር አሳልፎ የሚሰጥ ከሆነ አባላት ያልሆኑት ምን ይሆናሉ? ይህንን ትረዳለህ ብዬ አስባለሁ።

የሙሴ ህግ ዛሬ በክርስቲያኖች ላይ ይሠራል? ከሆነስ ክርስቶስ ለምን በመስቀል ላይ ሞቶ የሚሻል ቃል ኪዳን ህግ ሊሰጠን ቻለ? ህጉ ሁሉ እስኪፈፀም ድረስ (ማቴዎስ 5፡18) የእብራዊያን ጸሐፊ ሲናገር የፊተኛውን ኪዳን አስወግዶ ሁለተኛውን አዲስ ኪዳንን በኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕትነት አቋቋመ (ዕብራዊያን 10፡9~10)፣ እኛ ግዲያን፣ ስርቆትን፣ ሁሉ በተመለከተ በአዲስ ኪዳን ውስጥም ስለሚገኙ ያለ ሕግ አልተተውንም።

በአምልኮ ውስጥ መካኒካል ሙዚቃ ምን ችግር አለው? መካኒካል ሙዚቃ ለምሣሌ በመዝናኛ፣ ቤት ውስጥ፣ ወዘተ ስህተት ላይኖረው ይችላል። ነገር ግን ወደ አምልኮ ሲመጣ ያ ሌላ ጉዳይ ነው። ጌታ በድምፃችን እንድናመሰግነው እንደሚፈልግ ገልፁአል (ኤፌሶን 5፡19፣ ቆላስይስ 3፡16) በሜካኒካል ሙዚቃን ማምለክን ገልጾ ቢሆን ኖሮ ያ ጥሩ ነበር። ግን አልገለፀም። ስለዚህ ጌታን ለማስደሰት ወይም ራሳችንን ለማስደሰት የምንሄድበትን ማወቅ አለብን። የሚገርመው ነገር የሰው ልጅ ስለሁሉም ነገር የራሱን መንገድ ለማግኘት የመፈለግ ዝንባሌ እንዳለው እና እሱን ለማጽደቅ የሚጓዘው ሙከራ መንገድ

ረችሆም ነው

ክርስቲያኖች የጌታን እራት ምን ያህል ጊዜ መካፈል አለባቸው? በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ የተገናኙበትን ምሣሌ አለን (የሐዋሪያት ሥራ 20፡7)። ክርስቲያኖች ለአምልኮ የሚሰበሰቡት ስንት ጊዜ ነው? በሣምንት አንዴ ወይም ሁልጊዜ ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እሁድ አይደል? በትክክል ሁልጊዜ ክርስቲያኖች የጌታ እራትን በየሣምንቱ እሁድ ይካፈላሉ።

የጌታ ቤተክርስቲያን ጉባኤ ያለ ሽማግሌዎችና ዲያቆናት በቅዱሣት መጻህፍት ሊሠራ ይችላል? አዎን ፣ ምክንያቱም ወንዶቹ ሽማግሌዎች እና ዲያቆናት ለመሆን ብቁ ለመሆን ጊዜ ስለሚወድ ነው (1 ኛ ጢሞቴዎስ 3፣ ቲቶ 1) ብቁ የሆኑ ሽማግሌዎች እስከሚፈገኙ ድረስ አባላቱ ለቤተክርስቲያን አመራር መስጠት አለባቸው። ሽማግሌዎች እና ዲያቆናት ቢኖሩ ጥሩ ነው ያበረታታል፣ ነገር ግን ብቁ የሆኑ ከሌሉ የሽማግሌ ሹመት ባይኖራቸው ይሻላል። ጉባኤው ብቁ ሣይሆኑ መሾም ማለት ከጥቅሙ ጉዳቱ ይበልጣል።

አንድ ሰው የጌታን ቤተክርስቲያን እንዴት ሊጀምር ይችላል? አንድ ሰው ኀባር ቀደም መሆን አለበጥ አባል ከሆንክ እና አንድ ወይም ብዙ የምታስተምር ከሆነ እና ጌታን ለመታዘዝ ከወሰኑ ከእንሰሱ ጋር ለጉባኤ መጀመሪያ አስኳል ነህ። በዙሪያህ ተቀምጠህ ምንም ነገር ካላደረግክ ምንም ነገር መጀመር አትችልም። ነገር ግን ጌታን የምትወድ ከሆነና ባለህበት ጉባኤ ማየት የምትፈልግ ከሆነ ተነስተህ ጥረት የምታደርግ ከሆነ፣ መጀመር ትችላለህ።

ምናልባት ቀጥለን ለጥያቄዎች መልስ መስጠት እንችል ይሆናል ነገር ግን ትምህርታችንን ከመዝጋታችን በፊት ከሐሰት ትምህርት እንድትጠነቀቅ አበረታታሃለሁ። አንድ ነገር ሲመጣ ከወንድሞችም ቢህን ጉዳዩን በማስተዋል መርምረው መጽሐፍቅዱስ ውስጥ ትክክል የሆነ መንገድ እንዳለ ያስተምራልና ይህንን ትክክል የሆነውን የጌታን መንገድ ለመከተል የተቻለህን ሁሉ ማድረግ አለብህ።

ይህምአንተእናሌሎችየጉባኤውአባላትቅዱሣትመጻሕፍትንጠንቅቀው ለማወቅ ልዩ ጥረት እንድታደርጉ ሀሳብ አቀርባለሁኝ። እግዚአብሄርን ማወቅ፣ እሱን መተዋወቅን፣ ፈቃዱን ማወቅን ስታጠና በቀላሉ አትታለልም።

ባለህበት ጉባኤ ለመመስረት በምታደርገው ጥረት ስኬታማ እንድትሆን እፀልያለሁኝ። ተስፋ አትቁረጥ፣ አትተው፣ ነገር ግን ከእሱ ጋር ቆይ እና በእርሱ ላይ መሥራትህን ቀጥል ፣ ለጌታ ታማኝ ሁን፣ እና እሱ ይባርክሃል።